# የአብክመ ከተ ሞችና መሰረተ ልማት ቢሮ

# የ2015 በጀት ዓመት አመታዊ እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

*ሰኔ/2015 ዓ.ም* *ባህር ዳር*

## I. መግቢያ

ሀገራችን ብሎም ክልላችን ለውጡን ተከትሎ ከነበረው የግብርና መር ስተራቴጅ ማሻሻያወችን በማድረግ አገር በቀል /Home grow economic stratage/ እና ባለብዙ ዘርፍ የልማት ስትራቴጅ ተግባራዊ በማድረግ በቀውስ ወቀትም ሁነን አለም በኮቪድ ወረርሽኝና ተመሳሳይ ምክንያቶች በኢኮኖሚ ቀውስ ሲታመስ ችግሩ ሳይከፋ መቋቋም መቻላችን ዋነኛ ምክንያት መሆን ችሏል፡፡ የለውጡና ልማቱ ዋናኛ መዳረሻ የስኬት መገለጫ ያደገ የበለጸገ ህዝብ በመፍጠር በዘመናዊ መንገድ የሚከትምና የመከተም ፍላጎቱ ያደገ ህዝብ መፍጥር ነው፡፡

ስለሆነም የምንፈጥራቸው ከተሞችና የምንመራ መሪወች ይህን ፍላጎት መሸከም አቅማችን ያደገና በየጊዜው የሚያድግ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ የምንመራው የአብክመ ከተሞችና መሰረተ-ልማ ቢሮ በከተሞች ጉዳይ ላይ ቁልፍ ሚና ያለውና ከተሞች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ ሞተርና ማዕከል፣ ውብና ጽዱ፣ ለኑሮ ተስማሚ እንዲሆኑ በማስቻል ለክልላችን ብሎም ለአገራችን ብልፅግና ወሳኝ የሆኑ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡ በመሆኑም ቢሮው የክልሉ ከተሞች ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የተከተሉ፣ በፕላን የሚመሩ፣ መሰረተ ልማት የተስፋፋባቸው፣ ፅዱ፣ ውብ፣ የልማትና የአገልግሎት ማዕከል እንዲሆኑ በማስቻልና የዳበረ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን እንደ ተልዕኮ ይዞ የከተሞችን ልማት በማስፋፋት የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ባከናወናቸው ተግባራት በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

ይሁን እንጅ በአሁኑ ሰዓት በክልላችን በየአካባቢው አዳዲስ ከተሞች በመፈጠራቸው ምክንያት የከተማ ቁጥር መጨመር፣ ነባር ከተሞችም ወደ ጎን መስፋት፣ በዚህም የከተሞች ህዝብ ብዛት በፍጥነት የጨመረበት እና የክትመት ምጣኔውም በፍጥነት እያደገ የመጣበት ሁኔታ አለ፣ ይህንኑ ተከትሎም በከተሞች የሥራ አጥነት መበራከት፣ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት በእጅጉ መጨመር፣ የመሰረተ ልማት ፋላጎትና ጥያቄ ማደግ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ተደራሽ እና አርኪ አለመሆን፣ የፕላን ጥሰትና ህገ-ወጥ የመሬት ወረራ የተበራከተበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡ በተለይም የከተማ ነዋሪውን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በከተሞች የሚታየውን ሌብነት በመታገል እና ተቋማዊ አፈፃፀምን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር በመፍጠር በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት ልዩ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው በክልላችን የትህነግ አሸባሪና ወራሪ ሃይል ወረራ በፈፀመባቸው ዞኖች ውስጥ ባሉ በርካታ ከተሞች የደረሰውን ውድመት መልሶ በመገንባት ከተሞችን ወደ ቀደመ ነባራዊ ሁኔታቸው ለመመለስ ቢሮው ከተለመደው ሁኔታ ወጣ ብሎ ኢጋር አካላትንም ጭምር በማስተባበር በስፋትና በልዩ የኃላፊነት መንፈስ በመስራት ላይ ይገኛል፣ ቀጣይም አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በመሆኑም እነዚህንና ሌሎች በከተሞች የሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ከተቋሙ የ10 ዓመት (2013-2022) መሪ የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ የተቀዳ የ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ ታቅዶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በበጀት አመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና የዝግጅትና የተግባር ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## II. የቁልፍ እና አበይት ተግባራት እቅድ አፈፃፀም

### 1. የቁልፍ ተግባራት እቅድ (የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች) አፈፃፀም

#### ግብ 1፡- በየደረጃው ያለውን አቅም ግምት ውሰጥ ያስገባ፣ የተለጠጠ እና በውጤት የሚለካና ተጠቃሚውን ያሳተፈ እቅድ ማቀድና በመነሻ ሁኔታውና በሚከናወኑ ተግባራት ላይ መግባባት መፍጠር፣

## 1.1. እቅድ ዝግጅት

በዝግጅት ምዕራፉ ከሚከናወኑ ዋና ተግባሮች ውስጥ አንዱ እቅድን በጥራትና በወቅቱ ማቀድ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው

- ✓ **የክረምት ተግባራት እቅድ፡-** በ2014 በጀት ዓመት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሁነን ብዙ ልምዶች ከወሰድንባቸዉ ዉስጥ አንዱ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ነው፡፡ በመሆኑም ከሐምሌ ጀምሮ ጥራት ያለው የክረምት እቅድ እና ቼክሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ በእቅዱ እና በቼክሊስቱ ላይ ከፈፃሚ አካላት ጋር በዙም ኮንፈረንስ የጋራ መግባባት ተፈጥሮ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- ✓ **የወቅታዊ ስራዎች እቅድ፡-** በዝግጅት ምዕራፉ የህልውና ዘመቻ ጦርነት የነበረበት ወቅት ስለነበር ሁለት ግንባሮች (የልማትና የጦርነት ግንባር) ስለነበሩን ለዚህ ተግባር የሚመጥን አጭር እቅድ ተዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን ከህልውና ዘመቻ ማግስት በጦርነት የተጎዱ ከተሞችን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡
- ✓ **የለውጥ /የሪፎርም/ ስራዎች እቅድ፡-** ተግባሮቻችን በወቅቱና በጥራት ለመፈጸም እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የለውጥ ስራዎች እቅድ ለማቀድ ጥረት ተደርጓል፡፡ በክልሉ መንግስት ተሻሽሎ የወጣውን የለውጥና የአደረጃጀት ማሻሻያ መመሪያ ታሳቢ በማድረግ እቅዱ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡
- ✓ **የመልካም አስተዳደር ችግር መፍቻ ዕቅድ፡-** ከቢሮው ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ባህሪያቸው አንፃር ራሱን የቻለ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍቻ እቅድ አቅደው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡
- ✓ **የ2015 በጀት አመት እቅድ፡-** ከተቋሙ የ10 ዓመት መሪ እቅድ የተቀዳ፤ የተቋሙን ራዕይ እና ተልዕኮ መሰረት ያደረገ፣ የተለጠጠ (ሰፊ) ግን ሊደረስበት የሚችል፤ ከፌደራል፣ ከክልል፣ ከዞኖችና ከድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ጋር የተናበበ፤ ጥራት ያለው፣ በጊዜ የተገደበና የተተነተነ፣ በውጤት ላይ ያተኮረ፣ የህዝብ ተሳትፎን ዋነኛ አቅም ያደረገ፣ በጦርነት የተጎዱ ከተሞች መልሶ ግንባታን ትኩረት የሰጠ፤ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራርን መሰረት ያደረገ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡
- ✓ **የፕሮጀክት እቅድ፡-** የፕሮጀክት ባህሪ ያላቸውን UIIDP እና የከተማ ምግብ ዋስትና በራሳቸው ባህሪ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በጥቅሉ በዘፈቀደ ሳይሆን እቅድን በእቅድ ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.2. የእቅድ ኦረንቴሽን

ጥራት ያለው ዕቅድ ማቀድ አንዱ ተግባር ሲሆን በዕቅዱ ላይ ከፈጻሚ አካላት ጋር በቂ መግባባት መፈጠር ደግሞ ሌላኛው ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡

### የአመራርና ፈፃሚ የእቅድ ኦረንቴሽን መድረኮች፡-

- ከዚህም አንፃር በየደረጃው የ2014 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ኦረንቴሽን መድረክ በማዘጋጀት 15,262 (9,920 ወንድና 5,342 ሴት) አመራሮችንና ፈፃሚዎችን በማሳተፍ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ታቅዶ
- በክልል ደረጃ ደብረማርቆስ ከተማ "ከተሞቻችንን የብልጽግና ማዕከል እናደርጋለን " በሚል መሪ ቃል በሞቀ እና በደመቀ መልኩ የእቅድ ኦረንቴሽንና የንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ ከመስከረም 9 - 10 /2015 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን በዚህም መድረክ መሳተፍ ከነበረባቸው 846 አመራሮችና ባለሙያዎች ውስጥ ወንድ 720 ሴት 112 በድምሩ 832 (የእቅዱን 98.3%) አመራሮችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡- የአመራርና ባለሙያ እቅድ ኦረንቴሽን የዞን መምሪያዎች አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | ዞን | እቅድ ኦረንቴሽን መሳተፍ ያለበት አመራርና ባለሙያ | | | እቅድ ኦረንቴሽን የተሳተፈ አመራርና ባለሙያ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |

| ተ.ቁ | ዞን | እቅድ ኦረንቴሽን መሳተፍ ያለበት አመራርና ባለሙያ | | | እቅድ ኦረንቴሽን የተሳተፈ አመራርና ባለሙያ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | ደሴ | 269 | 191 | 460 | 269 | 191 | 460 | 100 | 1ኛ |
| 2 | ደ/ጎንደር | 1,108 | 465 | 1,573 | 1,108 | 465 | 1,573 | 100 | 1ኛ |
| 3 | ምዕ/ጐንደር | 78 | 12 | 90 | 78 | 12 | 90 | 100 | 1ኛ |
| 4 | ባህር ዳር | 395 | 251 | 646 | 395 | 251 | 646 | 100 | 1ኛ |
| 5 | ደ/ወሎ | 790 | 344 | 1,134 | 790 | 344 | 1,134 | 100 | 1ኛ |
| 6 | ማዕ/ጐንደር | 343 | 189 | 532 | 343 | 189 | 532 | 100 | 1ኛ |
| 7 | ደ/ታቦር | 125 | 74 | 199 | 125 | 74 | 199 | 100 | 1ኛ |
| 8 | ሰ/ጎንደር | 150 | 84 | 234 | 150 | 84 | 234 | 100 | 1ኛ |
| 9 | ደ/ማርቆስ | 325 | 300 | 625 | 318 | 296 | 614 | 98.24 | 9ኛ |
| 10 | ኦሮሞ | 212 | 105 | 317 | 208 | 102 | 310 | 97.79 | 10ኛ |
| 11 | ሰ/ወሎ | 575 | 251 | 826 | 560 | 245 | 805 | 97.46 | 11ኛ |
| 12 | ምዕ/ጐጃም | 972 | 401 | 1,373 | 945 | 382 | 1,327 | 96.65 | 12ኛ |
| 13 | ደ/ብርሃን | 156 | 115 | 271 | 149 | 112 | 261 | 96 | 13ኛ |
| 14 | ጐንደር | 220 | 250 | 470 | 219 | 231 | 450 | 95.74 | 14ኛ |
| 15 | ምስ/ጐጃም | 319 | 59 | 378 | 310 | 50 | 360 | 95.24 | 15ኛ |
| 16 | ኮምቦልቻ | 125 | 100 | 225 | 149 | 56 | 205 | 91.11 | 16ኛ |
| 17 | ወልደያ | 200 | 62 | 262 | 178 | 57 | 235 | 89.69 | 17ኛ |
| 18 | አዊ | 190 | 20 | 210 | 153 | 35 | 188 | 89.52 | 18ኛ |
| 19 | ዋግ ኽምራ | 241 | 159 | 400 | 237 | 105 | 342 | 85.5 | 19ኛ |
| 20 | ሰ/ሸዋ | 273 | 60 | 333 | 219 | 52 | 271 | 81.38 | 20ኛ |
| | **የዞን ድምር** | **7,066** | **3,492** | **10,558** | **6,903** | **3,333** | **10,236** | **96.95** | |
| 21 | በክልል ደረጃ | 732 | 114 | 846 | 720 | 112 | 832 | 98.35 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **7,798** | **3,606** | **11,404** | **7,623** | **3,445** | **11,068** | **97.05** | |

- በዚህ ተዋረድ በዞኖች እና ከተሞች በተካሄዱ የእቅድ ኦረንቴሽን እና የአፈፃፀም ግምገማ መድረኮች መሳተፍ ከነበረባቸው 10,558 (7,066 ወንድና 3,492 ሴት) አመራሮች እና ፈፃሚዎች ውስጥ 10,236 (96.95%) (ወንድ 6,903 ሴት 3,333) አመራሮችና ፈፃሚዎች ተሳትፈዋል፡፡

## የህዝብ ክንፍ/አጋር አካላት የእቅድ ኦረንቴሽን መድረኮች፡-

- በተቋሙ የልማትና መልካም አስተዳደር አጀንዳዎች ዙሪያ ተሳትፎ የሚኖራቸው 889 (624 ወንድና 265 ሴት) የሴክተሩ የህዝብ ክንፎችና አጋር አካላት (ባለሀብቶች፣ ኢንቨስተሮች፣ ተደማጭ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶችና ሴቶች) በ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ በዞን ደረጃ በዞኖችና ከተሞች በተፈጠሩ የእቅድ ኦረንቴሽን መድረኮች መሳተፍ ከነበረባቸው 14,984 (9,459 ወንድና 5,525 ሴት) የህዝብ ክንፍ /አጋር አካላት ውስጥ 12,932 (ወንድ 8,084 ሴት 4,848) በማሳተፍ የእቅዱን 86.31% ማሳካት ተችሏል፡፡

### ሰንጠረዥ 2፡- የህዝብ ክንፍ /አጋር አካላት እቅድ ኦረንቴሽን የዞን መምሪያዎች አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዞን | መሳተፍ ያለበት | | | የተሳተፈ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | ደሴ | 350 | 168 | 518 | 350 | 168 | 518 | 100 | 1ኛ |
| 2 | አዊ | 160 | 15 | 175 | 175 | | 175 | 100 | 1ኛ |
| 3 | ማዕ/ጎንደር | 96 | 27 | 123 | 96 | 27 | 123 | 100 | 1ኛ |
| 4 | ባህርዳር | 303 | 191 | 494 | 303 | 191 | 494 | 100 | 1ኛ |
| 5 | ደ/ብርሃን | 568 | 177 | 745 | 568 | 177 | 745 | 100 | 1ኛ |

| ተ.ቁ | ዞን | መሳተፍ ያለበት | | | የተሳተፈ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 6 | ደ/ወሎ | 1,251 | 642 | 1,893 | 1,251 | 642 | 1,893 | 100 | 1ኛ |
| 7 | ዋግህምራ | 49 | 39 | 88 | 49 | 39 | 88 | 100 | 1ኛ |
| 8 | ምዕ/ጐጃም | 541 | 162 | 703 | 539 | 160 | 699 | 99.43 | 5ኛ |
| 9 | ደ/ማርቆስ | 250 | 200 | 450 | 245 | 192 | 437 | 97.11 | 6ኛ |
| 10 | ኮምቦልቻ | 250 | 200 | 450 | 245 | 192 | 437 | 97.11 | 6ኛ |
| 11 | ምዕ/ጐንደር | 68 | 42 | 110 | 65 | 39 | 104 | 94.55 | 11ኛ |
| 12 | ደ/ጎንደር | 1,100 | 900 | 2,000 | 964 | 874 | 1,838 | 91.9 | 12ኛ |
| 13 | ጐንደር | 310 | 300 | 610 | 289 | 267 | 556 | 91.15 | 13ኛ |
| 14 | ሰ/ጎንደር | 900 | 900 | 1,800 | 701 | 921 | 1,622 | 90.11 | 14ኛ |
| 15 | ወልደያ | 75 | 19 | 94 | 67 | 13 | 80 | 85.11 | 14ኛ |
| 16 | ሰ/ወሎ | 414 | 125 | 539 | 325 | 88 | 413 | 76.62 | 16ኛ |
| 17 | ምስ/ጎጃም | 860 | 480 | 1,340 | 651 | 294 | 945 | 70.52 | 17ኛ |
| 18 | ደ/ታቦር | 330 | 215 | 545 | 250 | 128 | 378 | 69.36 | 18ኛ |
| 19 | ኦሮሞ | 100 | 100 | 200 | 94 | 32 | 126 | 63 | 19ኛ |
| 20 | ሰ/ሸዋ | 1,484 | 623 | 2,107 | 857 | 404 | 1,261 | 59.85 | 20ኛ |
| | **የዞን ድምር** | **9,459** | **5,525** | **14,984** | **8,084** | **4,848** | **12,932** | **86.31** | |
| 21 | በክልል ደረጃ | 152 | 63 | 215 | 152 | 63 | 215 | 100 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **9,611** | **5,588** | **15,199** | **8,236** | **4,911** | **13,147** | **86.50** | |

## የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች፡-

- ሌላው በየደረጃው የህብረተሰብ ንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀትና ቢያንስ 162,500 የከተማ ነዋሪወችን በማሳተፍ በ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር አጀንዳዎቻችን ላይ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ታቅዶ በዞኖችና ከተሞች በተፈጠሩ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች መሳተፍ ከነበረባቸው 431,006 (259,683 ወንድና 171,323 ሴት) የከተማ ነዋሪዎች ውስጥ 399,692 (92.73%) (239,947 ወንድና 159,745 ሴት) የከተማ ነዋሪዎችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

### ሰንጠረዥ 3፡- በዞኖችና ከተሞች ደረጃ የተካሄዱ የእቅድ ኦረንቴሽን (የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች)

| ተ.ቁ | ዞን | መሳተፍ ያለበት የከተማ ነዋሪ ህዝብ | | | የተሳተፈ የከተማ ነዋሪ ህዝብ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | አዊ | 10,400 | 6,470 | 16,870 | 10,400 | 6,470 | 16,870 | 100 | 1ኛ |
| 2 | ሰ/ጎንደር | 11,220 | 12,177 | 23,397 | 11,220 | 12,177 | 23,397 | 100 | 1ኛ |
| 3 | ደ/ጎንደር | 11,686 | 7,825 | 19,511 | 11,686 | 7,825 | 19,511 | 100 | 1ኛ |
| 4 | ማዕ/ጎንደር | 22,627 | 7,169 | 29,796 | 22,627 | 7,169 | 29,796 | 100 | 1ኛ |
| 5 | ደ/ብርሃን | 7,632 | 4,108 | 11,740 | 7,632 | 4,108 | 11,740 | 100 | 1ኛ |
| 6 | ባህር ዳር | 20,000 | 13,000 | 33,000 | 20,000 | 13,000 | 33,000 | 100 | 1ኛ |
| 7 | ደ/ታቦር | 7,825 | 4,135 | 11,960 | 7,825 | 4,135 | 11,960 | 100 | 1ኛ |
| 8 | ደሴ | 580 | 289 | 869 | 580 | 289 | 869 | 100 | 1ኛ |
| 9 | ደ/ወሎ | 32,569 | 26,964 | 59,533 | 32,493 | 26,932 | 59,425 | 99.82 | 9ኛ |
| 10 | ሰ/ወሎ | 29,800 | 21,200 | 51,000 | 27,676 | 21,927 | 49,603 | 97.26 | 10ኛ |
| 11 | ደ/ማርቆስ | 4,000 | 3,000 | 7,000 | 3,800 | 2,791 | 6,591 | 94.16 | 11ኛ |
| 12 | ኮምቦልቻ | 4,000 | 3,000 | 7,000 | 3,800 | 2,791 | 6,591 | 94.16 | 11ኛ |
| 13 | ዋግህምራ | 7,500 | 7,500 | 15,000 | 7,339 | 6,640 | 13,979 | 93.19 | 13ኛ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ምዕ/ጐጃም | 26,007 | 12,060 | 38,067 | 24,743 | 10,646 | 35,389 | 92.97 | 14ኛ |
| 15 | ምዕ/ጐንደር | 2,860 | 640 | 3,500 | 2,515 | 738 | 3,253 | 92.94 | 15ኛ |
| 16 | ጎንደር | 9,829 | 6,312 | 16,141 | 8,981 | 5,538 | 14,519 | 89.95 | 16ኛ |
| 17 | ወልደያ | 2,500 | 206 | 2,706 | 2,011 | 225 | 2,236 | 82.63 | 17ኛ |
| 18 | ሰ/ሸዋ | 23,063 | 14,770 | 37,833 | 18,088 | 12,066 | 30,154 | 79.70 | 18ኛ |
| 19 | ኦሮሞ | 5,815 | 5,460 | 11,275 | 4,328 | 4,165 | 8,493 | 75.33 | 19ኛ |
| 20 | ምስ/ጎጃም | 19,770 | 15,038 | 34,808 | 12,203 | 10,113 | 22,316 | 64.11 | 20ኛ |
| | **ድምር** | **259,683** | **171,323** | **431,006** | **239,947** | **159,745** | **399,692** | **92.73** | |

- ከክልል እስከ ከተማ በተካሄዱ መድረኮች የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ፣ በተቋሙ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አፈታት ሂደት፣ በከተሞች ልማት የህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት ወሳኝ ስለመሆኑ፣ ስለከተማ ፕላን አተገባበር፣ የመሬት አስተዳደርና ልማት አፈፃፀምን ከህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች የፀዳ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በሰፊው ተመክሮባቸዋል፡፡

## የተካሄዱ የእቅድ ኦረንቴሽን መድረኮች አፈጻጸም የነበረው ጉልህ ጥንካሬ፡-

- በክልል ደረጃ ደብረ ማርቆስ ከተማ ላይ የተካሄደው መድረክ ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶችንም ከማካተቱም በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ የላቀ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ዞኖች፣ ሪጅኦፖልታን ከተሞች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሪ እና ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች በየፈርጃቸዉ ሰፊ የዕውቅና ስነ-ስርዓት የተካሄደበት መድረክ ስለነበር ትልቅ የመነሳሳት ስሜት ፈጥሯል፡፡
- በ2015 በጀት ዓመት የታቀዱ የልማትና መልካም አስተዳር ተግባራትን በተሻለ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ለመፈፀም የሚያስችል የዓቅም መገንቢያ መድረክም ሁኖ አገልግሏል፡፡
- 8 ዞንና ሪጅኦፖሊታን ከተሞች ከ2014 በጀት ዓመት ከተግባሮቻቸው ውስጥ በተለየ ሁኔታ የፈፀሙትን ተግባር ተለይቶ በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅተው ተሞክሯቸውን እንዲያስተላልፉ ተደርጓል፡፡
- የተቋሙን 21 ዋና ዋና ግቦችን ያካተተ የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ከሁሉም ዞኖችና ከተሞች ጋር የፊርማ ስነ ስርዓት ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ በእቅዱ ላይ የጋራ መግባባት የተደረሰበት፣ እቅዱን የመፈጸም እና የማስፈፀም ዝግጁነት የታየበትና ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት የተፈጠረበት መድረክ ነበር፡፡

በዚህ መድረክ ሁሉም ዞኖችና ሪጅኦፖሊታን ከተሞች እስከ መስከረም 25/2015 ዓ.ም በዞን ደረጃ ለአመራርና ፈፃሚ እቅድ ኦሪንቴሽን በመስጠት ወደ ተግባር እንዲገቡ መግባባት ላይ ተደርሶ የነበረ ሲሆን የክልሉ ኮር አመራር ዞኖችን ተከፋፍሎ የዞኖች የእቅድ ኦሬንቴሽን መድረክ ስኬታማ እንዲሆን የደገፈበት መንገድ በጣም አበረታች ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በፍጥነት ወደ ተግባር በመግባት ሰ/ሸዋ፣ ሰ/ጐንደር እና ጐንደር ከተማ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ሌሎች ዞኖችና ከተሞችም በተባለው ጊዜ አለመጨረስ ወይም ጊዜ የመውሰድ ችግሮች ቢስተዋልም እንኳን በተሟላ መንገድ ከማስኬዳቸው ባለፈም፡-

- መድረኮቻቸውን ያካሄዱ ዞኖችና ሪጅኦፖሊታን ከተሞች የሚቀርቡ ሰነዶችን በጥራት በማዘጋጀትና ተሞክሮዎችን ቀምረው በመድረኩ በማቅረብ በቂ ትምህርት እንዲወሰድባቸውና ለቀጣይ አቅም አድርጐ ለመጠቀም የተሰራው ሥራ የሚበረታታ ነበር፡፡
- ከታዳጊ ከተሞች ጀምሮ እስከ ዞን አመራሮች ድረስ የሚመለከታቸውን ፈፃሚ አካላት፣ አጋር አካላትን በማካተት እንዲሁም የዞን ኮር አመራሮች በመድረኩ ተገኝተው ለተግባሩ ትኩረት በመስጠት ጥብቅ የሥራ አቅጣጫዎችን እንዲሰጡ ማድረግ ከመቻሉም በላይ የሥራ መነሳሳት ለመፍጠር የተደረገው ጥረት መልካም ጅምር ሆኖ ታይቷል፡፡
- ከባለሀብቶች ሀብት በማሰባሰብ መድረኮችን ሳቢና ማራኪ ማድረግ ከመቻሉም በተጨማሪ በሁሉም በተፈጠሩ መድረኮች ፈፃሚውን ሊያነሳሳ በሚችል መንገድ የእውቅና ሥነስርዓት ተካሄዷል፡፡
- ሁሉም ዞኖችና ሪጅዮፖሊታን ከተሞች ከዞን መድረክ በተጨማሪ ወደ ወረዳዎች፣ ከተሞች፣ ክፍለ ከተሞች እና ቀበሌዎች በመውረድና የሕዝብ ንቅናቄ መድረኮችን ማካሄድ ችለዋል፡፡
- በአጠቃላይ እቅድ ኦሪንቴሽኑን ወደ ከተሞች፣ ክ/ከተሞች መሪና፣ ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች እንዲሁም ታዳጊ ከተሞችና ሕዝቡ ድረስ በማውረድ በ2015 በጀት ዓመት ተግባሮቻችን ላይ በቂ መተማመን በመፍጠር ወደ ተግባር ምዕራፍ መሸጋገር ተችሏል፡፡ ይህም ለተግባር ምዕራፉ ጅምር አፈጻጸም ጥሩ አቅም መፍጠር ችሏል፡፡

### 1.3. የክረምት ተግባራት እቅድ አፈፃፀም

የክረመት ጊዜውን በተለመደ ልምድ በዘፈቀደ ላለማሳለፍ ከሐምሌ 1/2014 ጀምሮ ጥራት ያለው የክረምት ተግባራትን (በተለይም የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የውሃ ማፈሰሻ ቦዮች ከፈታና በክረምት በጎፈቃድ የአቅመ ደካሞች ቤት ግንባታና ጥገና ስራዎችን) ለማሳካት የሚያስችል እቅድ እና ቼክሊስት በማዘጋጀት በእቅዱ እና በቼክ ሊስቱ ላይ ከፈጻሚ አካላት ጋር በዙም ኮንፈረንስ የጋራ መግባባት ተፈጥሮ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

#### ከዚህም አኳያ በሁሉም ከተሞች ንቅናቄ በመፍጠር፡-

- የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ 743,728 ወንድ እና 602,496 ሴት በድምሩ 1,346,224 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታ ተሳትፈዋል፡፡ በዚህም 19,753,114 (88.78%) የውበት ችግኞችን በመትከል 2,414.36 ሄ/ር አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡
- እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና የውሃ ማፈሰሻ ቦዮች ጽዳት ዘመቻ ወንድ 275,380፣ ሴት 270,267 በድምሩ 545,648 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍል በቀጥታ ተሳትፏል፡፡

#### በክረምት በጎፈቃድ፡-

- 269 የአቅመ ደካሞች ቤቶች በአዲስ ተገንብተዋል፡፡ 208 የአቅመ ደካሞች ቤቶች ተጠግነዋል፡፡ በቤት ግንባታ እና ጥገና ስራው ላይ 151 ባለሀብቶች እና 3,728 በጎፈቃደኞች በጉልበታቸው ተሳትፈዋል፡፡

#### ሌላው በእቅድ እና በቼክ ሊስት ትኩረት ከተሰጣቸው የክረምት ተግባራት ጎን ለጎን፡-

- በ2014 በጀት ዓመት የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎችን የመመረቅ፣ የፈጻሚዉን እና የህብረተሰቡን ተነሳሽነት የማሳደግ እንዲሁም በእቅድ እና በቼክ ሊስት ያስቀመጥናቸውን የክረምት ተግባራቶች በደማቅ ፕሮግራም ለማስጀመር ትልቅ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 1.4. የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረኮች አፈፃፀም

- ✓ በየደረጃው በየሩብ ዓመቱ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረኮችን በማዘጋጀት 15,262 (9,920 ወንድና 5,342 ሴት) አመራሮችን እና ፈፃሚዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ

#### 1.4.1. የ1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ አፈፃፀም፡-

- በክልል ደረጃ የቢሮው፣ የፕላን ኢንስቲቲዮትና የአለም ባንክ /UIIDP/ ወንድ 183 ሴት 111 በድምሩ 294 አመራሮችና ሰራተኞች በተገኙበት በደ/ታቦር ከተማ 1ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም ግምገማ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የቢሮው፣ የፕላን ኢንስቲቲዮት የ5ቱ ቅርንጫፍ ኃላፊዎችን ጨምሮ፣ የዞኖችና የ32ቱ UIIDP ከተሞች 280 ያህል የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ኢጋርና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የ2015 በጀት ዓመት 1ኛ ሩብ አመት አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በሁመራ ከተማ ተካሂዷል፡፡
- በዚሁ ተዋረድ በዞኖችና ከተሞች በ1ኛ ሩብ ዓመት በተካሄዱ የሰራተኛ ውይይት መድረኮች መሳተፍ ከነበረባቸው 9,634 (6,186 ወንድና 3,448 ሴት) አመራሮችና ፈፃሚዎች ውስጥ 8,525 (88.49%) (ወንድ 5,501 ሴት 3,024) አመራሮችንና ፈፃሚዎችን በማሳተፍ ለቀጣይ ተልእኮ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- በ1ኛ ሩብ ዓመት የተካሄዱ የሰራተኛ ውይይት መድረኮች የዞን መምሪያዎች አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | ዞን | መሳተፍ ያለበት | | | የተሳተፈ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | ማዕ/ጐንደር | 343 | 189 | 532 | 343 | 189 | 532 | 100 | 1ኛ |
| 2 | ባህር ዳር | 365 | 251 | 616 | 365 | 251 | 616 | 100 | 1ኛ |
| 3 | ደሴ | 234 | 94 | 328 | 234 | 94 | 328 | 100 | 1ኛ |
| 4 | አዊ | 351 | 211 | 562 | 351 | 211 | 562 | 100 | 1ኛ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ደ/ብርሃን | 156 | 115 | 271 | 156 | 115 | 271 | 100 | 1ኛ |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 266 | 208 | 474 | 266 | 208 | 474 | 100 | 1ኛ |
| 7 | ኮምቦልቻ | 132 | 55 | 187 | 132 | 55 | 187 | 100 | 1ኛ |
| 8 | ደ/ታቦር | 92 | 80 | 172 | 92 | 80 | 172 | 100 | 1ኛ |
| 9 | አርሞ | 182 | 104 | 286 | 178 | 101 | 279 | 97.55 | 9ኛ |
| 10 | ጐንደር | 302 | 201 | 503 | 294 | 196 | 490 | 97.42 | 10ኛ |
| 11 | ሰ/ጎንደር | 229 | 116 | 345 | 219 | 109 | 328 | 95.07 | 11ኛ |
| 12 | ሰ/ሸዋ | 597 | 265 | 862 | 562 | 257 | 819 | 95.01 | 12ኛ |
| 13 | ሰ/ወሎ | 575 | 251 | 826 | 550 | 230 | 780 | 94.43 | 13ኛ |
| 14 | ምዕ/ጐጃም | 637 | 391 | 1,028 | 582 | 382 | 964 | 93.77 | 14ኛ |
| 15 | ደ/ማርቆስ | 66 | 47 | 113 | 54 | 38 | 92 | 81.42 | 15ኛ |
| 16 | ወልደያ | 69 | 49 | 118 | 50 | 45 | 95 | 80.51 | 16ኛ |
| 17 | ደ/ወሎ | 790 | 344 | 1,134 | 616 | 295 | 911 | 80.34 | 17ኛ |
| 18 | ዋግህምራ | 208 | 150 | 358 | 177 | 94 | 271 | 75.7 | 18ኛ |
| 19 | ደ/ጎንደር | 546 | 318 | 864 | 264 | 70 | 334 | 38.66 | 19ኛ |
| 20 | ምዕ/ጐንደር | 46 | 9 | 55 | 16 | 4 | 20 | 36.36 | 20ኛ |
| | **የዞን ድምር** | **6,186** | **3,448** | **9,634** | **5,501** | **3,024** | **8,525** | **88.49** | |
| 21 | በክልል ደረጃ | 183 | 111 | 294 | 183 | 111 | 294 | 100 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **6,369** | **3,559** | **9,928** | **5,684** | **3,135** | **8,819** | **88.83** | |

### 1.4.2. የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ አፈፃፀም፡-

- በፍጥነት እያደገ የመጣውን የክልላችን ከተሞች በየፈርጃቸውና በየደረጃቸው ለመምራት የሚደረገው ጥረት የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅና ፈጣን ምላሽ የሚያስፈልገው በመሆኑ በክልል ደረጃ "ከተሞችን የለውጥና የብልፅግና ማዕከል እናደርጋለን" በሚል መሪ ቃል  የ2015 በጀት ዓመት የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም ግምገማና በተቋሙ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ እያጋጠሙ ባሉ ማነቆዎችና መፍትሄዎቻቸው ላይ ከዞኖች፣ ከከተማ አስተዳደሮች ከመሪ ማዘጋጃ ቤቶችና ወረዳ ፅ/ቤቶች እንዲሁም ለከተሞች ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና መሳካት ታላቅ ድርሻ ያላቸው ኢጋር አካላት ወንድ 1,236 ሴት 81 በድምሩ 1,317 የተሳተፉበት የምክክር እና የንቅናቄ መድረክ ከጥር 26 እስከ 28/2015 ዓ.ም በጐንደር ከተማ በበቂ ዝግጅት ላይ ተመስርቶ በሞቀና በደመቀ ሁኔታ ተካሂዷል፡፡
- ይህንንም መነሻ በማድረግ ከዞንና ከሪጅኦፖሊታን ከተሞች ጀምሮ እስከ ታችኛው የከተማ ፈርጅ ድረስ ለከተሞች እድገትና ብልጽግና መረጋገጥ የሚመለከታቸውን አካላት ማለትም ፈፃሚና አስፈፃሚ፣ ኢጋር አካላትና የሕብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ እንደ የከተሞች ነባራዊ ሁኔታ አሉ የሚባሉ ችግሮችን ለይቶ በዝርዝር በመወያየት፣ መፍትሄ ማስቀመጥና የተቀመጠውን መፍትሄ ተግባራዊ ማድረግ ለነገ የማይባል ተግባር መሆኑን በውል ተገንዝበን በልዩ ትኩረት ልንፈጽመው ይገባል በሚል የማደማደሚያ ሃሳብ ተደርሶ ተጠናቋል፡፡
- በመሆኑም በየደረጃው በሁሉም ዞኖች እና በ681 ከተሞች መካሄድ ከነበረባቸው 922 መድረኮች መካከል 637 (69.09%) የተካሄዱ ሲሆን በነዚህም መድረኮች መሳተፍ ከነበረበት 232,204 (ወንድ 168,704 እና ሴት 63,500) የሰው ኃይል ውስጥ 223,843 (ወንድ 165,140 እና ሴት 58,703) በማሳተፍ የእቅዱን 96.40% ማሳካት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡- በየደረጃው የተካሄዱ መድረኮች ብዛትና የሰው ኃይል ተሳትፎ አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | የዞን ስም | በየደረጃው መካሄድ ያለባቸው መድረኮች ብዛት | | | በመድረኮች መሳተፍ የነበረበት የሰው ሃይል ብዛት | | | በመድረኮች የተሳተፈ የሰው ሃይል ብዛት | | | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መካሄድ የነበረበት | የተካሄደ ብዛት | አፈፃፀም | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ምዕ/ጎንደር | 36 | 36 | 100 | 6,097 | 3,236 | 9,333 | 5,584 | 2,605 | 8,189 | 87.74 |
| 2 | ወልዲያ | 15 | 15 | 100 | 2,960 | 2,348 | 5,308 | 2,216 | 2,056 | 4,272 | 80.48 |
| 3 | ማዕ/ጎንደር | 78 | 77 | 98.72 | 13,440 | 6,019 | 19,459 | 12,327 | 5,198 | 17,525 | 90.06 |
| 4 | ምስ/ጎጃም | 77 | 75 | 97.40 | 23,376 | 7,433 | 30,809 | 21,685 | 6,790 | 28,475 | 92.42 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ሰ/ሸዋ | 67 | 63 | 94.03 | 13,264 | 6,360 | 19,624 | 13,232 | 6,748 | 19,980 | 101.81 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 78 | 70 | 89.74 | 9,199 | 4,410 | 13,609 | 12,362 | 5,582 | 17,944 | 131.85 |
| 7 | ደ/ወሎ | 99 | 86 | 86.87 | 52,508 | 7,820 | 60,328 | 51,416 | 7,370 | 58,786 | 97.44 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 56 | 48 | 85.71 | 18,937 | 10,302 | 29,239 | 17,472 | 9,167 | 26,639 | 91.11 |
| 9 | አዊ | 60 | 46 | 76.67 | 12,509 | 6,739 | 19,248 | 11,082 | 5,006 | 16,088 | 83.58 |
| 10 | ምዕ/ጎጃም | 83 | 62 | 74.70 | 7,410 | 2,599 | 10,009 | 8,497 | 2,077 | 10,574 | 105.64 |
| 11 | ዋግኽምራ | 34 | 19 | 55.88 | 1,752 | 1,657 | 3,409 | 1,227 | 974 | 2,201 | 64.56 |
| 12 | ሰ/ጎንደር | 24 | 8 | 33.33 | 3,004 | 2,188 | 5,192 | 2,314 | 1536 | 3,850 | 74.15 |
| 13 | ጎንደር | 32 | 7 | 21.88 | 945 | 539 | 1,484 | 911 | 480 | 1,391 | 93.73 |
| 14 | ባህር ዳር | 38 | 7 | 18.42 | 1,273 | 906 | 2,179 | 1,411 | 926 | 2,337 | 107.25 |
| 15 | ኮምቦልቻ | 19 | 3 | 15.79 | 871 | 492 | 1,363 | 793 | 419 | 1,212 | 88.92 |
| 16 | ደሴ | 24 | 2 | 8.33 | 335 | 130 | 465 | 315 | 106 | 421 | 90.54 |
| 17 | ደ/ታቦር | 13 | 1 | 7.69 | 285 | 36 | 321 | 264 | 25 | 289 | 90.03 |
| 18 | ኦሮሞ | 27 | 2 | 7.41 | 146 | 47 | 193 | 131 | 37 | 168 | 87.05 |
| 19 | ደ/ማርቆስ | 19 | 1 | 5.26 | 245 | 155 | 400 | 236 | 147 | 383 | 95.75 |
| 20 | ደ/ብርሃን | 34 | 1 | 2.94 | 148 | 84 | 232 | 141 | 78 | 219 | 94.40 |
| 21 | ወ/ጠ/ሴ/ሁ/ራ | 9 | 8 | 88.89 | | | | 1,524 | 1,376 | 2,900 | |
| | **ድምር** | **922** | **637** | **69.09** | **168,704** | **63,500** | **232,204** | **165,140** | **58,703** | **223,843** | **96.40** |
| 22 | በክልል ደረጃ | 1 | 1 | 100 | 1,236 | 81 | 1,317 | 1,236 | 81 | 1,317 | 100 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **923** | **638** | **69.12** | **169,940** | **63,581** | **233,521** | **166,376** | **58,784** | **225,160** | **96.42** |

### በየደረጃው በተካሄዱ መድረኮች የተሳተፉ አካላት፡-

- በዞን በማዕከል ደረጃ (በ13ቱ ዞኖችና በ8ቱ ሪጅዮ ፖሊታን ከተሞች) በተካሄዱ መድረኮች ሁሉም የከተሞችና መሰረተ ልማት መምሪያ አመራሮችና የማኔጅመንት ቡድን አባላት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንቶች፣ የፍትህ መምሪያ ኃላፊዎች፣ የፖሊስ መምሪያ ኃላፊዎች፣ የሁሉም ወረዳ አስተዳዳሪዎች እና ብልጽግና ጽ/ቤት ኃላፊወች፣ የሁሉም ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎችና ብልጽግና ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች የሰላምና ደህንነት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ በመምሪያው ስር የሚገኙ እስከ ታዳጊ ከተማ ድረስ ያሉ የወረዳ ጽ/ቤት ሃላፊዎች፣ ስራአስኪያጆች እና ምክትል ስራ አስኪያጆች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡
- እነዚህ በዞን ማዕከል ደረጃ የተካሄዱ መድረኮች በዞን ዋና አስተዳዳሪዎች፣ በዞን ብልጽግና ጽቤት ኃላፊዎች እና በዞን ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ኃላፊዎች እንዲመሩ ተደርጓል፡፡
- በከተማ ደረጃ (በክ/ከተሞች፣ በመሪና ንዑስ ማዘጋጃቤቶች፣ በታዳጊ ከተሞች ቀበሌዎችን ጨምሮ በተካሄዱ ሁሉም መድረኮች የሁሉም የወረዳና ከተማ አመራሮች፣ የወረዳ ሰብሳቢ ዳኞች፣ ፍትህ ፅ/ቤት ኃላፊዎች፣ ፖሊስ ፅ/ቤት ኃላፊዎች፣ የቀበሌ አመራሮች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ነጋዴዎች፣ ወጣቶች እና ሴቶች እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን መድረኮችም በወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ በከንቲባዎችና በስራ አስኪያጆች እንዲመሩ ተደርጓል፡፡

### በመድረኮች አጀንዳ እንዲሆኑ የተቀረፁ ሀሳቦች፡-

- የዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣ ብልሹ አሰራርንና ሌብነትን መታገል፣ የከተሞች ጽዳትና ውበትን ከማስጠበቅ አኳያ የህሰ/ቡ ድርሻ፣ ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል፣ በከተሞች የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ጥራትና ተደራሽነት፣ ህገ ወጥነትን ስርዓት ለማስያዝ እና ለመታገል ህ/ሰቡን ከመንግስት ጎን ማሰለፍ እንዲሁም በሁሉም መስኮች ህ/ሰቡን ዋነኛ ባለቤትና ተዋናይ እንዲሆን ማድረግ የሚሉት ጭብጦች እና አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

### በተፈጠሩ መድረኮች የተነሱና ውይይት የተደረገባቸው ዋና ዋና ሃሳቦች፡-

1. በብዙ መድረኮች በስፋት የተነሳው እና የመጀመሪያው ጉዳይ ስለከተማ እና መሰረተ ልማት ተቋም የነበረው የተሳሳተ አመለካከት/ግንዛቤ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ስለከተማ እና መሰረተ ልማት ተቋም ላይ የነበረው ግንዛቤ ሲገለጽ የተሳሳተ እንደነበር እና ‹‹የከተማ ልማት ስራ ለከተማ እና መሰረተ ልማት ተቋም ብቻ የተተወ ይመስለን እንደ ነበር እውነቱ ግን ከተማን ማልማት ለካ ቤታችንን ማልማት እንደሆነ ልብ ሳንለው የቆየ ነው›› በሚል በስፋት ተነስቶ ተመክሮበታል፡፡ በከተማ ስራ የማይመለከተው አካል የለም፤ ሁሉም በየደረጃው ያለው አመራርና አጋር አካል (የሀይማኖት አባት፤ የፍትህ አካላት፤ ወጣቶች እና ሴቶች ወዘተ) ይመለከተናል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የየድርሻችን መወጣት አለብን (የጋራ ቤታችንን በጋራ እናለማለን) በሚል በአብዛኛው መድረኮች ተነስቶ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በአጠቃላይ በአብዛኛው መድረኮች ላይ ስለ ከተማና መሰረተ ልማት ካሁን በፊት የነበረው ግንዛቤ የተሳሳተ እንደሆነ እና ከተማን ማልማት የሁሉም ሰው ተግባር እንደሆነ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡
2. በሁሉም ከተሞቻችን በስፋት የተነሳው ሁለተኛው ጉዳይ የአገልግሎት አሰጣጥ ጉድለት ነው፡፡ በአብዛኛው ዞኖች፣ ወረዳዎች፤ ከተሞች (ከተማ አስተዳደሮች፣ ማ/ቤቶች እና ታዳጊዎች) መድረክ ላይ የተቋማችን አመራሮች እና ባለሞያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ሲፈተሽ ባለጉዳይን የማንገላታት (መመሪያን በማያሰራው በኩል አጣሞ መተርጎም፣ በፅሑፍ ምላሽ ለመስጠት ተጠያቂነትን መፍራት፣ በሰዓት አለምግባትና አለመውጣት፣ እጅ መንሻ መጠየቅ፣ ለጉዳይ አስፈፃሚ ወይም ደላላ ቅድሚያ መስጠት፣ ምክንያት እየፈጠሩ ነገ ዛሬ ማለት /ስበባስበብ ማብዛት/… ወዘተ) ችግሮች አሉ በሚል በስፋት የተነሳ ሲሆን ከዚህ አኳያ የተቀመጠው አቅጣጫ ከዞን ጀምሮ የባለጉዳይን ጉዳይ ፈጣን ምላሽ በጹሁፍም ሆነ በቃል ቶሎ ምላሽ መስጠት ተገቢ መሆኑን እና ያለበቂ ምክንያት ባለጉዳይን ነገ ዛሬ የሚል አመራር ሌላ ዝንባሌ ያለው መሆኑ ትርጉም የሚሰጠው መሆኑን በመድረኮች የጋራ መግባባት የተደረሰ ሲሆን በቀጣይ በዚህ ዘርፍ አብዮት ማምጣት ያስፈልጋል በሚል ማደማደም ተችሏል፡፡

3. ሶስተኛው ጉዳይ ከሌብነት እና ብልሹ አሰራር አኳያ የተነሳው ነው፡፡ በተቋማችን የሚስተዋሉ የሌብነት እና ብልሹ አሰራር ችግሮች እና ዘርፋቸው ሲገልጹ አገልግሎትን ሆን ብሎ ማጓተት፤ በስመ-ንብረት ዝውውር ወቅት የቤት ግምትን ከፍ እና ዝቅ ማድረግ እና ወረፋን ማቀዳደም፤ መሬት ግብይት ሂደት ላይ በተለይ በጨረታ ማስተላለፍ እና ለፍርድ ቤት የተሳሳተ ማስረጃ መስጠት፤ ፕላን ስምምነት እስከ ማጸደቅ ነገ ዛሬ ማለት፤ የተቋማችን ሰራተኛ ሁነው መሬት መደለል፤ የመሰረተ ልማት ስራን ሲረከቡ የጥራት ቁጥጥር እና ርክክብ ወቅት ጥራቱን በአግባቡ አለማረጋገጥ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች ዝንባሌያቸው የከፋ መሆኑን በስፋት ተነስቷል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ብልሹ አሰራሮች በቀጣይ በፍጥነት መታረም እንዳለባቸው እና የማይታረሙ ከሆነ በቀጣይ ይህን በሚፈጥሩ አመራሮች እና ባለሞያዎች ላይ ምርመራ በማድረግ አጥፊነታቸው ሲረጋገጥ እርምጃ እንደሚወሰድ እና ህዝቡም ህግ ለማስከበር ተባባሪ መሆን እንዳለበት መግባባት ተችሏል፡፡ በተለይም የአገልግለት አሰጣጥ ችግሮችን፣ ሌብነትን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚቻለው ህብረተሰቡን ማሳተፍ ሲቻል በመሆኑ ህዝቡ ጥቆማ እንዲሰጥ ሌቦችን እንዲያጋልጥ እና የእጅ መንሻ ካልሰጠሁ አይፈፀምልኝም የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዲያስወግድ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

4. አራተኛው ጉዳይ የከተማን ስራ በትብብር እና በቅንጅት ከመስራት አኳያ ያለው ችግር ነው፡፡ ከገጠር መሬት አኳያ፣ ከፍ/ቤቶች አኳያ፣ ከፍትህ ጽ/ቤት አኳያ እና በራሱ በከተማና መሰረተ ልማት መዋቅር የሚፈጠሩ የመገፋፋት እና ያለመቀናጀት ችግሮች ናቸው፡፡ በአብዛኛው መድረኮች  ህገወጥ የመሬት ወረራ እና ግንባታን ከመከላከል አኳያ የኢጋር አካላት ሚና አናሳ መሆንና በተለይም ያለመቀናጀት ችግር በስፋት ተነስቷል፡፡ በመሆኑም ህገወጥ የመሬት ወረራ እና ግንባታን ከመከላከል አንፃር ለከተሞች እድገት እና ልማት ፀር መሆኑን ሁሉም የከተማ ነዋሪ ተረድቶ ይህን ተግባር የሚፈፅሙትን በንቃት ማጋለጥ እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በየደረጃው ያለ የከተማ ባለድርሻ አካላት (በተለይ የፍትህ እና የፀጥታ አካላት) በከተሞች እድገትና የልማት ስራዎች በያገባኛል ስሜት መስራት እና ቅንጅታዊ አሰራሩን ማጠናከር እንደሚገባ መግባባት ተደርሷል፡፡ ሌላው መገፋፋትን ሊያስወግድ በሚችል መልኩ ተቋማዊ አሰራሮችን በማጠናከር ሁሉም ኢጋር አካላት ተቀናጅተን መስራት አለብን የሚል መግባባት ተደርሷል፡፡ እየተስፋፋ ያለዉ ህገ ወጥ ግንባታም ችግሩ በአንድ የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ብቻ ሊፈታ እንደማይችል እና የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን በመግባባት ሁሉም የየድርሻዉን እንደሚወጣ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህ ሲሆን ብቻ ነው የገጠርና የከተማ መሬት ከሌብነት መከላከልና ለታለመለት ጥቅም ማዋል የሚቻለው የሚል መደምደሚያ ተደርሷል፡፡

5. በአምስተኛ ደረጃ የሚታየው በከተሞች የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች በወቅቱ አለመጠናቀቅ፣ የተሰሩትም ቢሆን የጥራት ችግር መኖር (መፍረስ) እና በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ያለመሆን ችግር ነው፡፡ በመሆኑም በከተሞች የሚገነቡ የመሰረተ ልማት ስራዎች እየተከታተሉና እየገመገሙ እንዲሰሩ ህብረተሰቡን ማሳተፍ፣ በሌላ መልኩ ህብረተሰቡን የልማቱ ባለቤት በማደረግና ልማቱም የህዝቡ እንደሆነ በማስገንዘብ ኮሚቴ አቋቁሞ ጥራቱን እንዲቆጣጠር መደረግ እንዳለበት እና በሁሉም ቦታ የመሰረተ ልማቱ ተደራሽ እንዲሆን ለሁሉም ልማት የመንግስት በጀት ከመጠብቅ ይልቅ ህብረተሰቡን በጉልበት፤ በቁሳቁስና በጥሬ ገንዘብ አስተዋጽዖ ላይ ሁሉም የሕ/ሰብ ክፍል ተሳታፊ ማድረግና አመራሩም በዚህ ተግባር ላይ በቁርጠኝነት መስራትና ውጤት ማስመዝገብ እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

## በየደረጃው በተካሄዱ መድረኮች የመጣ ለውጥና የተገኘ ውጤት፡-

- የመጀመሪያው የግንዛቤና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት መቻሉ ሲሆን ይህም በየደረጃው ያሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በከተማው ህዝብ፣ በኢጋር አካላት፣ በአመራሩና እና በባለሞያው ቁጭት፣ መነሳሳት እና አንድነት መፍጠር መቻሉ፤ የከተማው ህዝብም አንቁን፣ አወያዩን፣ ከጎናችሁ ነን የሚል ወኔ በመሰነቅ በመድረኮች ላይ የልማት ኮሜቴዎችን በመምረጥ ወደ ተግባር መገባቱ፤ በተለይም ፍ/ቤቶችና የፍትህ ተቋማት ከመድረክ መልስ ለከተማ ልማት ስራ ትኩረት በመስጠት ችግሮችን ለመፍታት ወደ ተጨባጭ ተግባር መግባት መቻሉ፤
- ደ/ወሎ የቀበሌ ቤቶችን በፍ/ቤት ለግለሰብ መወሰንን በተመለከተ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ትክክል አለመሆኑ ስለተወሰነ ከዚህ በኋላ የትኛውም ፍ/ቤት የቀበሌ ቤቶችን መከራከር የማይችል መሆኑንና ይህንንም ለፍ/ቤቶች ተደራሽ የሚደረግ መሆኑ መግባባት መቻሉ፡፡

- በምስ/ጎጃምና አዊ ዞን በሚገኙ ሁሉም ከተሞች በዘመቻ መልክ እስከ ግንቦት 30 የተገነቡ ህገ ወጥ ግንባታዎችን ስርዓት ማስያዝ እንደሚገባ እና እስከ ሚያዝያ 30 በሁሉም ከተሞች ለቤቶች ህብረት ስራ ማህበራት የተዘጋጀ ቦታ ለመስጠት መግባባት ላይ መደረሱ፤
- ደ/ብርሃን ሁሉም መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች እሰከ ግንቦት 30 መጠናቀቅ እንዳለባቸው ከባለድረሻና ከአጋር አካላት ጋር በተግባቦትና በቅንጅት መስራት ላይ የጋራ መግባባት መደረሱ፤
- በምዕ/ጎንደር ዞን አብርሃጅራ መሪ ማ/ቤት በተፈጠረው የምክክር መድረክ በአረንጓዴ ልማት የውሃ ቦቲ ነዳጅ እንሰጣለን በሚል 4 በርሚል ነዳጅ የከተማዋ ነዋሪ ከመድረኩ በስጦታ ማበርከት መቻሉ፣ በጥሬ ገንዘብ መድረኩ ላይ 35,000.00 ብር ማዋጣት መቻሉ፤ እንዲሁም ከመድረክ በኋላ 2.2 ኪ.ሜ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ከፈታ የተደረገ ሲሆን በሂደቱ 6 መኖሪያ ቤት፣ 12 በረንዳ፣ 3 መፀዳጃ ቤት፣ 132 ሜትር አጥር እንዲፈርስ መደረጉ፤ መተማ ዮሀንስ፣ ምድረገነት፣ ገንዳውሃ እና አብርሃጅራ መሪ ማ/ቤት የቤቶች ህብረት ስራ ማህበር የቦታ ሽንሻኖ ማድረግ መጀመሩ፤ ከመድረኩ በኋላ በሁለም ከተሞች በሚባል ደረጃ ህገወጥ ግንባታን ለመከላከል ኮሚቴ ተደራጅቶ ወደ ተግባር መገባቱ እና ህብረተሰቡ በወሰነው ቀን መሰረት የፅዳት ዘመቻ መጀመሩ፤
- ማዕ/ጎንደር የአገልግሎት አሰጣጥ የመሻሻል ጅምር ማሳየቱ፤ ስታንዳርድ የመለጠፍ በስዓት የመገኘት ባለጉዳዩ ቢሮ ሲመጣ በክብር ማስተናገድ መጀመሩ፤ 3 ከተሞች ደግሞ በመድረኩ ወቅት ከማህበር ጋር የተነሳ ጥያቄ ስለነበር በባለሙያ የቦታ ሽንሽና መካሄዱ፤ ትችት የተነሳባቸው እና ማስረጃ የተገኘባቸው ባለሙያዎች በህግ ቁጥጥር ስር እንዲዉሉ መደረጉ፤
- ደ/ጎንደር መ/የሱስ ከተማ አስተዳደር ከመድረክ ሲወጡ የተጀመሩ መሰረተ ልማቶችን በመጎብኘት የሚሰራባቸው ብሎኮች በእያንዳንዱ ቤት 1,500 ብር የህብረተሰብ ተሳትፎ መሰብሰብ መጀመሩ፤ ሀሙሲት በአገልግሎት አሰጣጥ የተነሱ ችግሮችን ለመፍታት ተገልጋይ በኩፐን በተራ ቅደም ተከተል እንዲስተናገድ መደረጉ፤ ትችት የተነሳበትን ባለሙያ በዲሲፒሊን ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ተቋሙን እንዲለቅ መወሰኑ፤ የማህበር ቦታ ጥያቄ ለማስተናገድ እንቅስቃሴ መጀመሩ፤ የህብረተሰብ ተሳትፎና ገቢ አሰባሰብ በአብዛኛዎቹ ከተሞች እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- ሰ/ወሎ ቢጋሸና ከተማ በህዝብ መድረክ ላይ ህብረተሰቡ ድርሻውን ለመወጣት ብር 55,000 በደረሰኝ መሰብሰቡ፤ ዋድላ ወረዳ በሀሙሲት ንዑስ ማዘጋጃ ቤት በህብረተሰብ ተሳትፎ ዝቅተኛው ብር 300፣ መካከለኛው ብር 500 እና ከፍተኛው ብር 1,000 ለማዋጣት መግባባት መቻሉ እና የማዘጋጃ ቤቱ ቢሮ በህብረተሰብ ተሳትፎ እየተገነባ መሆኑ፤ ዋድላ ቤተ ዮሃንስ ታዳጊ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የጠጠር መንገድ ለማሰራት በመድረኩ ከተሳተፈው ማህበረሰብ 65,000 ብር መሰብሰብ መቻሉ፤ እንዲሁም ራያ ቆቦ - ባይባዋ ታዳጊ ከተማ የልማት ኮሜቴ በማዋቀር በእለቱ 37,700 ብር መሰብሰቡ፣
- ሰ/ሸዋ በአንድ አነስተኛ ከተማ/አስ ከመድረክ በኋላ ለመሰረተ ልማት ግንባታ የሚውል 226,000 ብር መሰብሰቡ፤ በሌላ አንድ አነስተኛ ከተማ/አስ ከ3 ባለሀብቶች 950,000 ብር ተሰብስቦ ለሸማች ህብረት ማህበር በመስጠት ለኑሮ ውድነት መደጎሚያ እንዲውል መደረጉ፤ ከአንድ መሪ ማዘጋጃ ቤት 5,000,000 ብር በመሰብሰብ ለመሰረተ ልማት ስራ እንዲውል መደረጉ፤ ከማህበራት ቦታ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ በተወሰኑ ከተሞች ለቀረበው ቅሬታ ምላሽ መሰጠቱ፤
- ጎንደር ከመድረኩ ማግስት 600,000 ብር ህ/ሰቡ በማዋጣት ላይ መሆኑ፣ ህገወጥ መሬት ወረራና ግንባታን የሚከላከል አፍራሽ ግብረ ሃይል በማቋቋም ወደ ስራ መገባቱ፣ የመሰረተ ልማ ስራዎችን በጊዜ ለማጠናቀቅ የሚያስችል ንቅናቄ መፈጠሩ፣ ለ282 የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ቦታ መስረከብ መቻሉ፣
- ደሴ 36 የከተማና የክፍለ ከተማ የመሬትና ህንፃ ሹም መሀንዲሶች (ባለሙያዎች) በሙስና የተጠረጠሩ ሲሆኑ ታግደው በህግ የሚጠየቁበት የምርመራ ሥራ መጀመሩ፤ አዘውትረው ሥራ የማይገቡና ባለጉዳይ የሚያጉላሉ 2 ባለሙያዎች ታግደው ጉዳያቸው በዲሲፒሊን እየታየ መሆኑ፤

## 1.5. የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አፈጻጸም

**ግብ 2፡- የከተማ ልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎቻችን በላቀ ደረጃ ለማስፈፀም ከኢፌዴሪ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በተቋሙ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ 8,652 አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ኢጋር አካላት (35% ሴቶች) የክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ**

- ✓ በፌደራል ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለ326 (ወንድ 267 ሴት 59)፣ በቢሮው ለ2,493 (ወንድ 1,825 ሴት 668)፣ በዞን መምሪያዎችና በከተሞች ለ8,534 (ወንድ 5,088 ሴት 3,446) በጠቅላላው 11,353 (ከ100% በላይ) (ወንድ 7,180 ሴት 4,173) አመራሮችና ባለሙያዎች በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡
  - ○ በየደረጃው የሚገኙ 914 (35% ሴቶች) አመራሮችና ፈፃሚዎች በተዘጋጁ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችና በማስፈፀሚያ ሰነዶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ለ1,452 (ከ100% በላይ) (ወንድ 923 ሴት 529) አመራሮችና ፈፃሚዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ○ በፌደራል ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኩል በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ሙያዎች ላይ እና የከተሞች የሰው ኃይል ልማት ስራን በተመለከተ ለ16 አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና የባለ ድርሻ አካላት (50% ሴቶች) የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ70 (ከ100% በላይ) የሚመለከታቸዉ አመራሮችና ቡድን መሪዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ○ በቄራ አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ200 ባለሙያዎች፣ በእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ75 ባለሙያዎች፣ እንዲሁም በዘመናዊ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ60 ባለሙያዎች በድምሩ ለ335 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በቄራ አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ283 (ወንድ 186 ሴት 97) ባለሙያዎች፣ በእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ291 (ወንድ 171 ሴት 120) ባለሙያዎች፣ እንዲሁም በዘመናዊ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ ለ224 (ወንድ 148 ሴት 96) ባለሙያዎች በድምሩ ለ818 (ወንድ 505 ሴት 313) (ከ100% በላይ) ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
  - ○ በየደረጃው ለሚገኙ 600 (35% ሴቶች) አመራሮችና ፈጻሚዎች በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ874 (ከ100% በላይ) (ወንድ 593 እና ሴት 281) ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ○ በየደረጃው ለሚገኙ 40 አመራሮች፣ የምክርቤት አባላትና ፈጻሚዎች በከተማ አመራርና አሰራር የህግ ማዕቀፎች ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 83 ሴት 59 ድምር 142 (ከ100% በላይ) ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

  - ○ በክልሉ ለሚገኙ 992 (35% ሴቶች) የማዘጋጃ ቤት ፋይናንስ ባለሙያዎች በከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለ66 (ወንድ 40 ሴት 26) እንዲሁም በዞን ደረጃ ለ558 (ወንድ 366 ሴት 192) በድምሩ ለ624 (ወንድ 406 ሴት 218) (62.9%) የማዘጋጃ ቤት ፋይናንስ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ○ በጥናት በተለዩ ክፍተቶች ላይ ተመስርቶ በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ለተሰማሩ 100 ባለሙያዎች (35% ሴቶች) የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በክልል ደረጃ ለ36 (ወንድ 32 ሴት 4) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ ለተመደቡ የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ባለሙያዎች፣ በፌደራል ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለ56 (ወንድ 46 እና ሴት 10) በድምሩ ለ92 (92%) (ወንድ 78 እና ሴት 14) የፕላን ዝግጅትና ትግበራ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ○ በመሬት አዋጅ፣ ደንብና አሰራር መመሪያዎች ዙሪያ ከሁሉም ዞኖችና ከተሞች ለተውጣጡ 1,570 (35% ሴቶች) የመሬት ልማትና አስተዳደር አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በፌደራል ደረጃ ለ160 (ወንድ 129 እና ሴት 31)፣

በክልል ደረጃ ለ57 (ወንድ 49 እና ሴት 8) እንዲሁም በዞን ደረጃ ለ1,282 (ወንድ 1,079 እና ሴት 203) በድምሩ ለ1,499 (95.47%) (ወንድ 1,257 እና ሴት 242) የሚመለከታቸው አመራሮችና ባለሙያዎች ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ ቁጥር 4/2015፣ የሊዝ መነሻ ዋጋና የነባር ይዞታ ዓመታዊ ክፍያ ማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ፣ በህገወጥ መሬት ወራራ፣ በመልሶ ማልማት፣ የመሬት ባንክና ፋይል አደረጃጀት በተዘጋጀ ማኑዋል ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በቤት ልማትና አስተዳደር ስራዎች ከዞኖችና ከከተሞች ለተውጣጡ 302 (ለ197 ወንዶች እና ለ105 ሴቶች) አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በክልል ደረጃ በመጀመሪያ ዙር ለ33 (14 ወንድ እና 19 ሴት) ባለሙያዎች እና በሁለተኛው ዙር ለ28 ሰልጣኞች በቤት መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር አጠቃቀም ላይ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በዞን ደረጃ ለ632 (451 ወንድ እና 181 ሴት) በድምሩ ለ665 (ከ100% በላይ) (465 ወንድ እና 200 ሴት) አመራሮችና ባለሙያዎች በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡
- በምግብ ዋስትና ፕሮግራም በታቀፉ 17 ከተሞች ለሚገኙ 724 (180 አመራሮችና 544 ባለሙያዎች) እንዲሁም 122 ባለድርሻ አካለት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ879 (ወንድ 563 ሴት 291) አመራሮች እና ባለሙያዎች እንዲሁም ለ112 (ወንድ 64 ሴት 48) ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡
- ለ1,000 (35% ሴቶች) አመራሮች እና ፈፃሚዎች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት ዙሪያ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በሚ/ር መ/ቤቱ ለ80 (ወንድ 70 እና ሴት 10)፣ በቢሮው ለ50 (ወንድ 43 እና ሴት 7) እና በዞን ደረጃ ለ2,434 (ወንድ 1,321 እና ሴት 1,113) በድምሩ ለ2,564 (ከ100% በላይ) (ወንድ 1,434 እና ሴት 1,130) አመራሮች እና ፈጻሚዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡
- ለ400 (35%) የሕንፃ ሹሞች ባለሙያዎች በሕንፃ አዋጅና ማስፈፀሚያ ህጎች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ112 (ወንድ 78 ሴት 34) ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 28% ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- በፌደራል፣ በክልል፣ በዞኖችና ከተሞች ደረጃ የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች**

| ተ.ቁ | ስልጠናውን ያዘጋጀው አካል | የስልጠናው ርዕስ ጉዳይ | የስልጠናው ተሳታፊ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1ኛ | በፌደራል ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር | በህገወጥ መሬት ወራራ፣ በመልሶ ማልማት፣ የመሬት ባንክና ፋይል አደረጃጀት | 35 | 10 | 45 |
| | | በመሬት ዘርፍ አገልግሎት ስታንዳርዶች ስልጠናና ምዘና | 94 | 21 | 115 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 70 | 10 | 80 |
| | | በፕላን ዝግጅትና ትግበራ | 46 | 10 | 56 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 22 | 8 | 30 |
| | | ድምር | 267 | 59 | 326 |
| 2ኛ | ቢሮው | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ)፣ የሊዝ መነሻ ዋጋና የነባር ይዞታ አመታዊ ክፍያ በተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ | 49 | 8 | 57 |
| | | በቤት መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር | 14 | 19 | 33 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 66 | 7 | 73 |
| | | በከተማ አመራርና አሰራር የህግ ማዕቀፎች ላይ | 83 | 59 | 142 |
| | | በከተማ ተቋማዊና መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮግራም (UIIDP) | 911 | 225 | 1136 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 43 | 7 | 50 |
| | | በምግብ ዋስትና ፕሮግራም | 627 | 339 | 966 |
| | ፕላን ኢንስቲቲዩት | በፕላን ዝግጅትና ትግበራ | 32 | 4 | 36 |
| | | ድምር | 1,825 | 668 | 2,493 |
| 3ኛ | ሰ/ሸዋ | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 12 | | 12 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 20 | 6 | 26 |
| | | በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች | 20 | 12 | 32 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 78 | 42 | 120 |

| ተ.ቁ | ስልጠናውን ያዘጋጀው አካል | የስልጠናው ርዕስ ጉዳይ | የስልጠናው ተሳታፊ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| | ማዕ/ጎንደር | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 78 | 16 | 94 |
| | | በአገልግሎት አሰጣጥ | 116 | 22 | 138 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 48 | 5 | 53 |
| | ምዕ/ጎንደር | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 13 | 4 | 17 |
| | ሰ/ጎንደር | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 8 | 2 | 10 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 8 | 4 | 12 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 18 | 1 | 19 |
| | ሰ/ወሎ | በመ/ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) እና በመ/ቁጥር 3/2013 | 124 | 55 | 179 |
| | | በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በገቢ አሰባሰብና በኦዲት ዙሪያ | 59 | 36 | 95 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 124 | 26 | 150 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 100 | 35 | 135 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 28 | 7 | 35 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 65 | 30 | 95 |
| | ደ/ወሎ | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 132 | 40 | 172 |
| | | በፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች | 186 | 38 | 224 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 24 | 4 | 28 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 137 | 22 | 159 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 460 | 209 | 669 |
| | | በሕንፃ አዋጅና ማስፈፀሚያ ህጎች | 18 | 7 | 25 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 47 | 15 | 62 |
| | ምዕ/ጎጃም | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 140 | 34 | 174 |
| | | በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች | 27 | 15 | 42 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 48 | 32 | 80 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 75 | 102 | 177 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 86 | 43 | 129 |
| | ምስ/ጎጃም | በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች | 223 | 68 | 291 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 70 | 39 | 109 |
| | | በሕንፃ አዋጅና ማስፈፀሚያ ህጎች | 18 | 3 | 21 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 172 | 33 | 205 |
| | ደ/ጎንደር | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 13 | 11 | 24 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | | 2 | 2 |
| | ኦሮሞ | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 35 | 13 | 48 |
| | | የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 42 | 33 | 75 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 36 | 23 | 59 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 37 | 17 | 54 |
| | | በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ በቁራ አገልግሎት እና በዘላቂ ማረፊያ | 5 | 3 | 8 |
| | ዋግኽምራ | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 93 | 261 | 354 |
| | አዊ | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 54 | 11 | 65 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 111 | 33 | 144 |
| | | ከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ | 50 | 29 | 79 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 43 | 2 | 45 |
| | ባ/ዳር | በመመሪያ ቁጥር 4/2015 (ከፊል ሰነድ አልባ መመሪያ) | 109 | 17 | 126 |
| | | በገቢያ ቦታ መመሪያ ዙሪያ | 104 | 15 | 119 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 455 | 1,120 | 1,575 |
| | | በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር | | 10 | 10 |
| | ጎንደር | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 33 | 32 | 65 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 36 | 12 | 48 |

| ተ.ቁ | ስልጠናውን ያዘጋጀው አካል | የስልጠናው ርዕስ ጉዳይ | የስልጠናው ተሳታፊ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| | | በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች | 43 | 19 | 62 |
| | | በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር | 80 | 34 | 114 |
| | | በቁራ አገልግሎት | 70 | 8 | 78 |
| | | በዘላቂ ማረፊያ | 58 | 20 | 78 |
| | ደሴ | በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ በቁራ አገልግሎት እና በዘላቂ ማረፊያ | 89 | 76 | 165 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 115 | 170 | 285 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 49 | 41 | 90 |
| | ኮምቦልቻ | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 49 | 17 | 66 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 66 | 23 | 89 |
| | | በቁራ አገልግሎት | 25 | 10 | 35 |
| | ደ/ማርቆስ | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 10 | 1 | 11 |
| | ወልደያ | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 42 | 65 | 107 |
| | ደ/ታቦር | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 100 | 100 | 200 |
| | | በቤት ልማት ስትራቴጅ ዙሪያ | 24 | 5 | 29 |
| | ደ/ብርሃን | በፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች | 25 | 19 | 44 |
| | | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና አረንጓዴ ልማት | 21 | 58 | 79 |
| | | በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአሰራር ማዕቀፎች | 95 | 100 | 195 |
| | | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች | 89 | 29 | 118 |
| | | **ድምር** | **5,088** | **3,446** | **8,534** |
| | | **ጠቅላላ ድምር** | **7,180** | **4,173** | **11,353** |

## 1.6. የለውጥ አመራርና አደረጃጀት ማሻሻያ ስራዎች አጸጻም

**ግብ 3፡- ከሲቪል ሰርቪስ ጋር በመቀናጀት የተቋማችን መዋቅር የዳሰሳ ጥናት በማደረግ ሊያሰራ የሚችል መፍትሄ መስጠት እና ተዘጋጅተው የወረዱ የሲቪል ሰረቪስ የለውጥ ስራ አመራር ስርአትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ፣**

- ✓ ከለውጥ ስራዎች አኳያ በተሻሻለው የመንግስት ተቋማት የለውጥ አመራር አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ መሰረት በየደረጃው ራሱን የቻለ የለውጥ ማስፈጸሚያ ዕቅድ በማዘጋጀት እና ለፈፃሚ አካላት በማውረድ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡
- ✓ ከዚህ ጋር ተያይዞ የቢሮው የ2015 በጀት ዓመት የለውጥ አመራር፣ አሰራርና አደረጃጀት እቅድን በተመለከተና በተሻሻለው የስራ አፈጻጸም ምዘና ስርአት ዙሪያ ለ126 ወንድ እና ለ58 ሴት በድምሩ ለ184 የቢሮውና የተጠሪ ተቋማት ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ✓ በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና መመሪያ መሰረት በቢሮው እና በተዋረድ ተቋማት የሚገኙ 9,453 (ወንድ 5,983 ሴት 3,470) የመንግስት ሰራተኞች የ6 ወር የስራ አፈፃፀም ውል እንዲይዙ ለማድረግ ታቅዶ 9,052 (95.76%) (ወንድ 5,692 ሴት 3,360) ፈፃሚዎች ውል እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 7፡- በዞኖችና በከተሞች የሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | ዞን | ውል መያዝ ያለበት | | | ውል የያዘ | | | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | ደሴ | 234 | 94 | 328 | 234 | 94 | 328 | 100 | 1ኛ |
| 2 | ደ/ብርሃን | 156 | 115 | 271 | 156 | 115 | 271 | 100 | 1ኛ |
| 3 | ሰ/ጎንደር | 154 | 79 | 233 | 154 | 79 | 233 | 100 | 1ኛ |
| 4 | ዋግኽምራ | 208 | 150 | 358 | 208 | 150 | 358 | 100 | 1ኛ |
| 5 | ማዕ/ጐንደር | 343 | 189 | 532 | 343 | 189 | 532 | 100 | 1ኛ |
| 6 | ምዕ/ጐንደር | 178 | 125 | 303 | 178 | 125 | 303 | 100 | 1ኛ |
| 7 | አሮሞ | 182 | 104 | 286 | 182 | 104 | 286 | 100 | 1ኛ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ደ/ጎንደር | 546 | 318 | 864 | 546 | 318 | 864 | 100 | 1ኛ |
| 9 | አዊ | 351 | 211 | 562 | 351 | 211 | 562 | 100 | 1ኛ |
| 10 | ደ/ማርቆስ | 39 | 34 | 73 | 39 | 34 | 73 | 100 | 1ኛ |
| 11 | ደ/ታቦር | 71 | 71 | 142 | 71 | 71 | 142 | 100 | 1ኛ |
| 12 | ባህር ዳር | 376 | 235 | 611 | 375 | 235 | 610 | 99.84 | 1ኛ |
| 13 | ሰ/ወሎ | 575 | 251 | 826 | 573 | 248 | 821 | 99.39 | 1ኛ |
| 14 | ምዕ/ጐጃም | 591 | 387 | 978 | 575 | 376 | 951 | 97.24 | 14ኛ |
| 15 | ኮምቦልቻ | 83 | 45 | 128 | 79 | 44 | 123 | 96.09 | 15ኛ |
| 16 | ሰ/ሸዋ | 597 | 265 | 862 | 562 | 265 | 827 | 95.94 | 16ኛ |
| 17 | ጐንደር | 57 | 75 | 132 | 53 | 72 | 125 | 94.70 | 17ኛ |
| 18 | ወልደያ | 116 | 76 | 192 | 106 | 69 | 175 | 91.15 | 18ኛ |
| 19 | ምስ/ጐጃም | 196 | 198 | 394 | 182 | 177 | 359 | 91.12 | 19ኛ |
| 20 | ደ/ወሎ | 790 | 344 | 1134 | 599 | 286 | 885 | 78.04 | 20ኛ |
| | **የዞን ድምር** | **5,843** | **3,366** | **9,209** | **5,566** | **3,262** | **8,828** | **95.86** | |
| 21 | በክልል ደረጃ | 140 | 104 | 244 | 126 | 98 | 224 | 91.80 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **5,983** | **3,470** | **9,453** | **5,692** | **3,360** | **9,052** | **95.76** | |

ከተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት ጋር በተያያዘ

- የተፈቀደው መዋቅር ህብረተሰቡ የሚጠይቀውን አግልግሎት ለማስተናገድ የማይችል መሆኑ፣
- አሁንም እስከታችኛው መዋቅራችን ድረስ ባሉ አንዳንድ የሰራ ክፍሎች ከJEG የስራ መደብ ፍረጃ ጋር ተያይዞ ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በተፈጠሩ አዳዲስ አደረጃጀቶች በበጀት ችግር ምክንያት የሰዉ ኃይል በወቅቱ አሟልቶ ወደ ስራ ለመግባት አለመቻሉ እና
- የሰራተኛ ጥቅማጥቅም አለመሟላት /ለምህንድስና የስራ መደቦች/ ወዘተ ችግሮች በስፋት የሚስተዋሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የተቋሙን መዋቅራዊ አደረጃጀት በመፈተሸ ችግሮችን ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ

- ✓ ከቢሮው እና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አጥኝ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ተግባር በመግባት የተደራጀው ኮሚቴ ተግባሩን በአጭር ጊዜ አጥንቶ ያቀረበ ሲሆን በችግሮቹና መፍትሄው ዙሪያ ከቢሮውና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አመራሮች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡
- ✓ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱ የጥቅማጥቅም (የደረጃና የኬሪየር) ጥያቄዎችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 1.7. የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎች

### ግብ 4፡- በተቋሙ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለይቶ በመፍታት እንዲሁም በዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የተገልጋዮች እርካታ አሁን ካለበት 48% ቢያንስ በአማካይ 55% እንዲደርስ ማድረግ፣

በየደረጃው ባለው መዋቅራችን በህብረተሰቡ የሚነሱት የልማት ፍላጎት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ በመምጣታቸው በተቋሙ የሚታዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ወይም የሌብነት ተግባራት በስፋት የሚታዩባቸውን ዘርፎችና ችግሮች በመለየት ከቢሮው ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ባህሪያቸው አንፃር ራሱን የቻለ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍቻ እቅድ አቅደው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

የተለዩ ዋና ዋና ችግሮች፡-

- የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር (በስመ-ንብረት ዝውውር፣ በመሬት ማስተላለፍ፣ በግንባታ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የግንባታ አገልግሎት ግዥ፣ የመደበኛ ግዥ...ወዘተ) ተገልጋይን ማንገላታትና መደለያ መጠየቅ /የቅን መስተንግዶ ችግር)፣
- የከተማ ፕላን ዝግጅትና ክለሳ የተደራሽነትና የጥራት ችግር፣
- ለተደራጁ ማህበራት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አቅርቦት ችግር፣
- ህገወጥ መሬት ወረራና ግንባታ መበራከት፣

- ለከፊል ሰነድ አልባ ይዞታዎች ካርታ ሰጥቶ ያለማጠናቀቅ፣
- የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ችግር፣
- የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አስታደደር ችግር /ቋሚ የማስወገጃ ቦታና የማጓጓዣ ተሽከርካሪ ችግር/፣
- የመሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ችግር /የመብራትና ውሃ አቅርቦት ችግር/ ወዘተ ናቸው፡፡
- የሌብነት ችግር (አሰራርን ጠብቆ ገቢን አለመሰብሰብ፣ የኦዲት ጉድለት፣ ደረሰኝ እና መረጃን ማጥፋት…ወዘተ)

የተለዩ ዘርፎች፡-

- መሬትና መሬት ነክ አስተዳደር ተግባራት፤
- የህንጻ ሹም ተግባራት/ፕላን ስምምነት፣ ግንባታ ፈቃድ፣ ስመንብረት ዝውውር/
- ፕላን ዝግጅትና ፕላን አፈጻጸም፣
- የፋይናንስ ነክ ተግባራት፣
- የኮንስትራክሽን ግዥዎች፣
- የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ወዘተ….ሲሆኑ

✓ በዚህም በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ጥናት የተጠና ሲሆን እንደ ችግሮች ክብደትና ቅለት በቅደም ተከተል ለመፍታት እቅድ ተይዞ በዞኖችና ከተሞች በእቅድ ከተለዩት 570 የመልካም አስተዳደር ችግሮች ውስጥ 433 (75.96%) የተፈቱ ሲሆን ቀሪዎቹ በሂደት ላይ ያሉና እንደ ችግሮች ክብደትና ቅለት በቅደም ተከተል ለመፍታት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡- በዞኖችና ከተሞች በእቅድ ከተለዩና የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች**

| ተ.ቁ | ዞን/ከተማ | በእቅድ የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች | የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች | አፈፃፀም | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰ/ጎንደር | 8 | 8 | 100 | 1ኛ |
| 2 | ሰ/ሸዋ | 47 | 46 | 97.87 | 2ኛ |
| 3 | ደ/ማርቆስ | 40 | 38 | 95 | 3ኛ |
| 4 | ምዕ/ጐንደር | 18 | 17 | 94.44 | 4ኛ |
| 5 | ምስ/ጐጃም | 31 | 29 | 93.55 | 5ኛ |
| 6 | ጐንደር | 21 | 19 | 90.48 | 6ኛ |
| 7 | አዊ | 10 | 9 | 90 | 7ኛ |
| 8 | ማዕ/ጐንደር | 30 | 25 | 83.33 | 8ኛ |
| 9 | ደ/ወሎ | 24 | 20 | 83.33 | 8ኛ |
| 10 | ደ/ጎንደር | 40 | 33 | 82.50 | 10ኛ |
| 11 | ደሴ | 15 | 12 | 80 | 11ኛ |
| 12 | ምዕ/ጐጃም | 51 | 36 | 70.59 | 12ኛ |
| 13 | ደ/ብርሃን | 51 | 36 | 70.59 | 12ኛ |
| 14 | ኦሮሞ | 15 | 10 | 66.67 | 14ኛ |
| 15 | ወልደያ | 6 | 4 | 66.67 | 14ኛ |
| 16 | ባህር ዳር | 55 | 36 | 65.45 | 16ኛ |
| 17 | ሰ/ወሎ | 34 | 21 | 61.76 | 17ኛ |
| 18 | ዋግኽምራ | 28 | 15 | 53.57 | 18ኛ |
| 19 | ደ/ታቦር | 20 | 10 | 50 | 19ኛ |
| 20 | ኮምቦልቻ | 26 | 9 | 34.62 | 20ኛ |
| | **ድምር** | **570** | **433** | **75.96** | |

በበጀት ዓመቱ ትኩረት ከተሰጣቸው የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ተግባራት መካከል አንዱ የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል ነው፡፡

- ✓ ከዚህ አንፃር በሁሉም የከተማ መዋቅር ባሉ የስራ ክፍሎች የሚሰጠው አገልግሎት 100% በዜጎች ቻርተር መሰረት እንዲሆን በማድረግ የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ታቅዶ በ13 ዞኖች ውስጥ ከሚገኙ 250 ከተሞች/ክ/ከተሞች/የስራ ክፍሎች ውስጥ 181 (72.40%) የሚሆኑት የዜጎች ቻርተር አዘጋጅተው እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡
- ✓ ለተቋሙ 298 ሰራተኞች (የቢሮው 204፣ የፕላን ኢንስቲቲዩት 65 እና የUIIDP 29) የደረት ባጅና መታወቂያ፣ የበር ባጅ እና የጠረጴዛ ባጅ ተሰርቶ እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡
- ✓ በ83 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች እና 6 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) በስታንዳረድ መሰረት የሚለካ አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል፡፡
- ✓ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለተመረጡ ከተሞች (ኮምቦልቻ፣ ደ/ማርቆስና ደ/ብርሃንና ባህርዳር) በተሟላና በተደራጀ መንገድ ጉድለት ሊሞላ የሚችል ልዩ ድጋፍ በአካል ወርዶ መደገፍ ተችሏል፡፡
- ✓ የተገልጋይ መስተንግዶን በተመለከተ በዞን መምሪያ ደረጃ ከመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተያይዞ 38,273 ባለጉዳዮችን ምላሽ መስጠት የተቻለ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በቃል ምላሽ የተሰጣቸው 23,848፣ በፅሁፍ ምላሽ የተሰጣቸው 7,749፣ ለፍትህና ለፀረ ሙስና ተቋማት ሙያዊ ማብራሪያ የተፃፈላቸው 6,676 ጉዳዮች ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡- በዞን መምሪያ ደረጃ ከመሬት ጋር ተያይዞ ምላሽ የተሰጣቸው ጉዳዮች**

| የተሰጠ ምላሽ | አገልግሎት የተሰጠባቸው ዞኖችና ከተሞች | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ምስ/ጎጃም | ምዕ/ጎንደር | ሰ/ጎንደር | ሰ/ወሎ | ደ/ወሎ | ማዕ/ጎንደር | ኦሮሚያ | ደ/ብርሃን | ደ/ጎንደር | ሰ/ሸዋ | አዊ | ምዕ/ጎጃም | ጎንደር | ደሴ | ድምር |
| በቃል ምላሽ የተሰጣቸው ተገልጋዮች ብዛት | 5,579 | 428 | 426 | 3,715 | 5,001 | 651 | 188 | | 316 | 310 | 1,269 | 5,965 | 0 | 0 | 23,848 |
| በፅሁፍ ምላሽ የተሰጣቸው ተገልጋዮች ብዛት | 960 | 407 | 201 | 1,739 | 1,511 | 342 | 48 | 85 | 148 | 27 | 1,289 | 136 | 760 | 96 | 7,749 |
| ለፍትህ ተቋማት የተሰጠ ምላሽ | 1,164 | 340 | 89 | 2,077 | 1,002 | 373 | 19 | 55 | 139 | 23 | 711 | 634 | 0 | 50 | 6,676 |
| ጠቅላላ ድምር | | | | | | | | | | | | | | | **38,273** |

- ✓ ከፍርድ ቤት፣ ከፖሊስ እና ከፀረ-ሙስና ተቋማት ለመጡ ከግንባታ ኘሮጀክቶች አስተዳደር ጋር የተያያዙ 1,475 ጉዳዮች ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ✓ ከዞኑ አቅም በላይ ሁነው ለቢሮው የተላኩ (ወደ ቢሮው የመጡ) ከመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተያይዞ 492፣ ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር ጋር ተያይዞ 10 እና ከግንባታ ኘሮጀክቶች አስተዳደር ጋር የተያያዙ 301 እና ሌሎች 244 ጉዳች በድምሩ 1,047 ጉዳዮች ለቢሮው በፅሁፍ ቀርበው 806 ጉዳዮች (ከመሬት አስተዳደር 455፣ ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር 10 እና ከግንባታ ኘሮጀክቶች አስተዳደር 161 እና ሌሎች 180) በፅሁፍ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡
- ✓ ከነዚህም ውስጥ 285 ጉዳዮች (ከመሬት አስተዳደር 118፣ ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር 6 እና ከግንባታ ኘሮጀክቶች አስተዳደር 161) ለፍትህና ለፀረ ሙስና ተቋማት በፅሁፍ ሙያዊ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ለአብነትም በባህር ዳር ከተማ ከ8 እስከ 22 ዓመት በላይ ሳይፈቱ የቆዩ 4 የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችን በዚህ በጀት ዓመት በውሳኔ መፍታት ተችሏል፡፡
- ለቢሮው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ከተለያዩ ዞንና ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች 279 የምደባ ጥያቄዎች ቀርበው 139 ፐሮጀክቶች (133 በቦርድ እና 6 በቢሮው) ውሳኔ የተሰጣቸው ሲሆን ቀሪዎቹ 140 ፐሮጀክቶች በቀጣይ የሚታዩ ናቸው፡፡
- የአምልኮ ቦታ ጥያቄን በተመለከተ በቁጥር 21 የሚሆኑና የቦታ መጠናቸው 117.4 ሄ/ር የሆነ አዲስ እና የማስፋፊያ የአምልኮ ቦታዎች ጥያቄ የቀረቡ ሲሆን ሁሉም እንዲያገኙ ውሳኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ከዞኖችና ከተሞች የማስፋፊያ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በቢሮውና በመስተዳደር ምክር ቤቱ በኩል ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ከቀረቡት 80 የአገልግሎት ዘርፍ የማስፋፊያ ጥያቄዎች መካከል 54 ይዞታዎች የቦታ መጠናቸው 45,849 ካ.ሜ የሆነ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ቀሪ 26 የሚሆኑት በቀጣይ የሚታዩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- ➢ ችግሩን ለማቃለል ከዚህ በላይ የተገለፁት ሰፋፊ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም አሁንም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች መኖራቸው ግንዛቤ መውሰድ ይጠይቃል፡፡
- ➢ በየደረጃው እየተሰጠ የሚገኘው አገልግሎት በባለሙያው ሙሉ ሰዓቱን ተጠቅሞ አለመስራት እና ከደላላ ነፃ የሆነ አገልገሎት አለመስጠት የሚጠቀሱ ጉልህ ችግሮች ናቸው፡፡

በበጀት ዓመቱ ትኩረት ከተሰጣቸው የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ተግባራት መካከል ሌላው በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የሚስተዋለውን የሌብነት ተግባር መከላከል ነው፡፡

- ✓ ከዚህም አኳያ በየደረጃው በሀብት ምዝገባ፣ በስነ-ምግባር እና በሙስና ወንጀሎች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር የሚመለከታቸው 11 አመራሮችና ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ታቅዶ የፀረ- ሙስና ቀን በዓል አከባበርን ምክንያት በማድረግ ለ289 (ወንድ 176 እና ሴት 113) የአብክመ ከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ እና የአብክመ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ አመራሮችና ሰራተኞች በሀብት ምዝገባ፣ በስነ-ምግባር እና በሙስና ወንጀሎች ዙሪያ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡
- ✓ ኮምቦልቻና እንጅባራ ከተማ ላይ ለ194 (ወንድ 141 ሴት 53) ለ32ቱ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር መኮንኖች፣ ለህዝብ ቅሬታ ሰሚዎች፣ ለአገልግሎት ቅሬታ ሰሚዎች፣ ለግዥ ቅሬታ ሰሚዎችና ለከተማ ፕላንና መሬት ልማት ማኔጅመንት ባለሙያዎች በስነ-ምግባር ምንነት፣ በሙስና ምንነትና በግዥና ፋይናንስ ላይ የሚፈፀሙ ብልሹ አሰራሮችን በተመለከተ እንዲሁም መራዊ ከተማ ላይ ለ177 (ወንድ 96 እና ሴት 81) የቢሮ አመራሮችና ሰራተኞች በስነ-ምግባርና በአመለካከት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ✓ በቢሮ ደረጃ ወንድ 8 ሴት 3 ድምር 11 ሀብት አስመዘጋቢዎች ሃብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 7 እና ሴት 3 በድምሩ 10 (የመጀመሪያ ምዝገባ 4 እድሳት 6) የቢሮው አመራሮችና ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው ለ413 ወንድ ለ247 ሴት በድምሩ ለ660 አመራሮችና ባለሙያዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሌብነትን ሊቀንሱ የሚችሉ ተግባራት እየተከናወኑ ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው በተቋሙ የልማትና መልካም አስተዳደር አጀንዳዎች ላይ ህብረተሰቡን በቀጥታ የማሳተፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

- ✓ በዚህም በየደረጃው በተከናወኑ የ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ ትውውቅ መድረኮች 399,692 (92.73%) (239,947 ወንድና 159,745 ሴት) የከተማ ነዋሪዎችን በቀጥታ ማሳተፍ ተችሏል፡፡
- ✓ የ2015 በጀት ዓመት የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም ግምገማና በተቋሙ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ እያጋጠሙ ባሉ ማነቆዎችና መፍትሄዎቻቸው ላይ በከተሞች በተፈጠሩ 637 መድረኮች 223,843 (ወንድ 165,140 ሴት 58,703) የከተማ ነዋሪዎች በቀጥታ ተሳትፈዋል፡፡
- ✓ በተፈጠሩ መድረኮችም የሌብነትና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ያለባቸው አመራሮች እና ባለሙያዎች ላይ ጥቆማዎች በየጊዜው የተነሳባቸው ሲሆን በየደረጃው ባለ መዋቅር በተቋሙ ከሙስና እና ብልሹ አሰራ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በማጣራት የስነ ምግባር ጉድለት የታየባቸው 201 አመራሮች እና ባለሙያዎች (15 አመራሮች እና በ186 ባለሙያዎች) ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ተወስዷል፡፡

ለአብነትም፡-

- ✓ ምዕ/ጎጃም አንጉት መዘጋጃ ቤት 1 አመራር በገንዘብ ሙስና ምክንያት ከኃላፊነት መነሳትና ሂደቱ በፍ/ቤት እየታየ ያለ፤ ዱርቤቴ ከተማ ያላግባብ የመንግስት መሬት ለግለሰብ አሳልፎ በመስጠት 2 ቀያሽ ባለሙያዎች ከስራ የተሰናበቱ፣ 1 ቀያሽ ባለሙያ ከደረጃ ዝቅ ብሎ መመደብ እና 1 የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቡድን መሪ ከኃላፊነት በማንሳት በድምሩ 5 አመራርና ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ማዕ/ጎንደር (ቆላድባ ከተማ) የመልካም አስተዳደር እጦት እና ብልሹ አሠራርን ከመታገል አኳያ በ6 ባለሙያዎች ላይ (3ቱ በህግ ጥላ ስር ውለው ጉዳያቸው እየታየ ያለ እና 3 ደግሞ ከሥራ በማሰናበትና ቦታ በመቀየር) በጥናት የተመሠረተ እርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ሰ/ወሎ መርሳ ከተማ 2600 ካ.ሜ ቦታ ያለ ከንቲባ ውሳኔ ያስተላለፉና በስመ ንብረት ዝውውር ዙሪያ የድርጅቱን መኖሪያ በማድረግ 4 የመሬት ባለሙያዎች አንድ ደረጃ ዝቅ ብለው የተመደቡ እና 1 የመሬት ባለሙያ ደግሞ ከስራ የተሰናበተ ሲሆን 1 የመሬት ልማት

ማኔጅመንት ቡድን መሪ ከኃላፊነት በማንሳት በፀረ-ሙስና ፍ/ቤት ጉዳዩ እየታየ ያለ በድምሩ 6 አመራርና ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡

- ✓ ደ/ጎንደር በዘርፉ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በማጣራት የስነ ምግባር ጉድለት በማጋጠሙ 1 ስራ አስኪያጁ እና 4 የመሬት ቡድን መሪዎች ከኃላፊነት እንዲነሱ እና 5 የስመ ንብረት ባለሙያዎች መደብ እንዲቀይሩ በማድረግ በድምሩ በ10 አመራርና ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ደ/ወሎ ብልሹ አሰራርና የስነ ምግባር ችግር ያለባቸውን 10 ፈፃሚዎችን በመለየት አስተማሪ ዕርምጃ የተወሰደ ሲሆን አልብኮ (ሳልመኔ ማዘጋጃ 2 ባለሙያዎች ከስራ የማሰናበት)፣ ወረኢሉ ወረዳ (ሰኞና ካቤ 2 ባለሙያ ማስጠንቀቂያና የ1 ወር ደመወዝ ዕገዳ)፣ ጃማ (ፋጅ 1 ባለሙያ ከደረጃ ዝቅድ ማድረግ)፣ ቦረና (ቢሊ ታዳጊ ከተማ 2 ባለሙያ ከስራ ማሰናበት)፣ ሊጋምቦ (ገነቴ 1 ባለሙያ ማስጠንቀቂያ መስጠት)፣ ከለላ ከተማ 2 ባለሙያ ከመሬት ልማት ቡድን በማንሳት ወደ ሌላ ቡድን የማዛወር ስራ ተሰርቷል፡፡
- ✓ ምዕ/ጎንደር የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው 9 ባለሙያዎች (5 ባለሙያዎች መደብ በመቀየር እና 4 ባለሙያዎች የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት) እርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ አዊ በመሬት፣ በኮንስትራክሽን፣ በገቢና በሌሎች ዘርፎች የሚስተዋለው ሌብነት በአሉታና በአወንታ ያለው ሁኔታ በመገምገም ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ ያለባቸውን ዘርፎች የመለየትና ራሱን አስችሎ በፕሮግራም ተከታታይነት ያለው ግምገማ የማድረግ ክፍተቶች ቢኖርም መምሪያው እስከ ታች ወርዶ በተለይም መሰረታዊ ችግር ያለባቸው 5 ከተሞችን ክትትል በማድረግ ወንድ 43 ሴት 2 በድምሩ 45 (5 አመራሮችና 40 ባለሙያዎች) ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል፡፡
    - ➢ ለአብነትም እንጅባራ ከተማ ወንድ 12 ሴት 2 ድምር 14 የጨረታ ኮሚቴ (5)፣ የስመ-ንብረት እና የምህንድስና ባለሙያዎች ከሊዝ ጨረታ ጋር ተያይዞ ከመመሪያው ውጭ ስመ-ንብረት ዝውውር በመፈፀማቸው ምክንያት 7 ባለሙያዎች በእስራት፣ 5 ባለሙያዎች የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት፣ 2 ባለሙያዎች አንድ ደረጃ ዝቅ ማድረግ እርምጃ ተወስዷል፡፡
    - ➢ ቻግኒ ከተማ 3 አመራሮች (ስ/አስኪያጅና ከንቲባ) እና 12 የቦታ አሰጣጥና ትክ ባለሙያ የስመ-ንብረት ዝውውር የምህድስና ባለሙያዎች ለግለሰቦች የድርጅት ቦታ አስፋፍቶ በመስጠታቸው ምክንያት 5ቱ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ 4ቱ የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት፣ 2ቱ የጠፉ እና 4ቱ አመራሮችን ጨምሮ የእስራት እርምጃ ተወስዷል፡፡
    - ➢ ዳንግላ ከተማ 5 ወንድ የመሬት ልማት ቡድን መሪ ባለሙያዎች ስራን በአግባቡ ባለመወጣት 4ቱ የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ሲሆን 1 መደብ እንዲቀይር ተደርጓል፡፡
    - ➢ አ/ቅዳም ከተማ 2 አመራር (ስ/አስኪያጅና ህንፃ ሹም) እና 6 ወንድ 1 ሴት በድምሩ 7 የሰነድ አልባ ኮሚቴዎች፣ የመሬት ቡድንና የምህድስና ባለሙያዎች ከመመሪያው ውጭ ያላግባብ ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጥናታቸው ምክንያት 2ቱ በዲሲፕሊን ተጠይቀው ምርመራ ላይ ያሉ እና 7ቱ አመራሮችን ጨምሮ የእስራት እርምጃ ተወስዷል፡፡
    - ➢ አገው ግምጃ ቤት ከተማ 2 ወንድ የመሬት ልማት ቡድን መሪ እና የግብይት ባለሙያዎች የድርጅት ቦታን ከመመሪያ ውጭ በመስጠታቸው ምክንያት በ2ቱም የእስራት እርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ዋግኽምራ ሰቆጣ ከተማ 2 አመራር (የመዘጋጃ ቤት የቀድሞው ስ/አስኪያጅና ም/ስራ አስኪያጅ) እና 1 ባለሙያ በመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች የጥራት መጓደል እና ስራ አፈፃፀም ከአመራርነት ተነስተው ጉዳያቸው በፍ/ቤት በመታየት ላይ ይገኛል፡፡
- ✓ ወልዲያ ከተማ 1 ህንፃ ሹም ስራውን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡

- ✓ ባህርዳር ጣና ክ/ከተማ 1 ፕላነር ያለመደቡ ካርታ ፕሪንት ሲያደርግ በመገኘቱ፣ 1 ቀያሽ ባለሙያ ስራን በአግባቡ ባለመወጣትና ቸለልተኝነት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን 1 ሰስመ-ንብረት ዝውውር ባለሙያ ቶሎ ምላሽ ባለመስጠት የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ ፋሲሎ ክ/ከተማ 1 የዳታ ቤዝ ባለሙያ ስራን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን 1 የህ/ሰብ ተሳትፎ ባለሙያ በስራ ላይ ቸለልተኝነት የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ ዳግማዊ ምኒሊክ ክ/ከተማ 1 ፕላነር የተመደበበትን ስራ በአግባቡ ባለመወጣት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን 2 ቡድን መሪዎች ከኃላፊነት እንዲነሱ የተደረገ ሲሆን በጠቅላላው 8 አመራሮችና ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ጎንደር አራዳ ክ/ከተማ 1 የግዥ ባለሙያ በግዥ ምክንያት በፍ/ቤት በሂደት ላይ ያለ፣ 5 የሲቪል መሃንዲስ ባለሙያዎች በሙስና ተጠርጥረው የስራ መደብ እንዲቀይሩ ማድረግ፣ 3 ሲቪል መሃንዲስ (መሬት ዘርፍ) እና 1 ደንብ ማስከበር ስራን በአግባቡ ባለመወጣት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ 1 መሬት ባለሙያ ስራን በአግባቡ ባለመወጣት ከስራ መሰናበት፣ 1 ሲቪል መሃንዲስ ስራን በአግባቡ ባለመወጣት የ1 ወር ደመወዝ በመቅጣት እርምጃ ተወስዷል፡፡ እንዲሁም ጃንተከል ክ/ከተማ 1 ዕቅድ/ዝ/ ባለሙያ በጨረታ ኮሚቴ ምክንያት በፍ/ቤት በሂደት ላይ ያለ ሲሆን በጠቅላላው 13 ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡
- ✓ ደሴ ከተማ ወደ ከተመው ከመምጣታቸው በፊት ሲሰሩ በነበሩባቸው የክልሉ ከተሞች የቤት መስሪያ ቦታ ወስደው እያለ ድጋሜ በደሴ ከተማ ባሉ 5 ክ/ከተሞች በቤት ማህበር ተደራጅተው ያለአግባብ ቦታ ሊወስዱ የነበሩ 111 ግለሰቦችን መረጃ በማጣራት ያለአግባብ ሊወሰድ የነበረን 11,100 ካ.ሜ ቦታ ማዳን ተችሏል፡፡
- ✓ ኮምቦልቻ ከተማ በመኖሪያ ቤት ህብርት ስራ ማህበር ተደራጅተው ያለአግባብ ድጋሜ 150 ካ.ሜ ቦታ ሊወስዱ የነበሩ 18 ግለሰቦችን መረጃ በማጣራት ያለአግባብ ሊወሰድ የነበረን 2700 ካ.ሜ ቦታ መከላከል ተችሏል፡፡
- ✓ ወረታ ከተማ ላይ በአለም ባንክ የኮብል እስቶን ንጣፍ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በወጣው ጨረታ በሀሰተኛ የምዝገባ ፈቃድ ተወዳድሮ በማሸነፍ ወደ ስራ ገብቶ የነበረ ሲሆን ይህንንም በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ጉዳዩ ተጣርቶ በሃሰተኛ ማስረጃ የተወዳደረ መሆኑ ተደርሶበት ተቋራጩ ታግዶ ለሁለተኛው አሸናፊ ስራው ተሰጥቷል፡፡
- ✓ በ118 ከተሞች የልማት ክትትል በማድረግ በጨረታ እና በምደባ ለተለያየ አገልግሎቶች ተወስደው በውላቸው መሰረት ወደ ልማት ያልገቡ 250 ቦታዎችን በመለየትና በመንጠቅ 26.09 ሄ/ር (67.94%) ያለማ መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- ➢ በከተሞች የሚታየውን ሌብነት ለማረም ሰፊ ጥረት ቢደረግም አሁን ካለው ተጨባጭ እውነት አንፃር ችግሩን ተሻግረናል ማለት አይቻልም፡፡
- ➢ አገልግሎት ፈላጊውም ያለምልጃ ጉዳዩ እንደማይፈፀምለት አምኖ ጉቦ በመክፈል የሌባው ተባባሪ የሆነበት እና ይህን ችግር ባለመፍታቱ መንግስትን የሚወቅስበት እና የሚያማርርበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡
- ➢ በሌላ በኩል የከተማ ነዋሪውም ሁሉንም ነገር መንግስት ሊሰራለት እንደሚገባ አድርጎ የመመልከትና መንግስትን በማስጨነቅ ያላግባብ የመጠቀም ዝንባሌ ይስተዋላል፡፡

## 1.8. የህግ እና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች

**ግብ 5፡- በተቋሙ ተዘጋጅተው በወረዱ የአሰራር መመሪያዎች ላይ የክፍተት ትንተና እና የፋይዳ ግምገማ ጥናቶችን በማድረግ እንዲሁም የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ነባር የህግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ እና አስፈላጊ የሆኑ አዲስ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣**

ከአሰራር ጋር ተያይዞ የሚታየው ዋናው ጉዳይ ተቋሙ የሚመራባቸው የህግ ማዕቀፎች አግባብነትና ችግር ፈችነት ነው፡፡

ከዚህም አኳያ ብዙ ሊያሰሩ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች ያሉ ቢሆንም

- ተቋሙ የሚመራባቸው አብዛኛው አሰራሮችና መመሪያዎች የህግ ክፍተት ያለባቸው፣
- አግባብነትና ችግር ፈችነት የጎደላቸው፣
- ቢሮክራሲ ማራዘም የተጠናወታቸው፣
- እንዲሁም ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ በመሆናቸው እያደገ የመጣውን የህዝብ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄ የማይመልሱ ናቸው፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በተቋሙ ተዘጋጅተው በወረዱ የማስፈፀሚያ ስትራቴጅዎች፣ ደንቦች እና የአሰራር መመሪያዎች ላይ የክፍተት ትንተና እና የፋይዳ ግምገማ ጥናቶችን በማድረግ 10 ነባር የህግ ማዕቀፎችን ለማሻሻልና 2 አዲስ የህግ ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት እቅድ የተያዘ ሲሆን በተቋሙ ተዘጋጅተው ወርደው በትግበራ ላይ ያሉና መሻሻል ያለባቸው የህግ ማዕቀፎች ማለትም፡-

- ✓ ፀድቀው የወጡ ህጎች
  - በከተሞች ውስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸውና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ /ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2015 ተጠናቆ ወደታች ወርዷል፡፡
  - የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመፍቀድ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2005 የአንቀፅ ማሻሻያ ጸድቆ ወደ ስራ ገብቷል፡፡
- ✓ መስተዳደር ምክር ቤት ለመጽደቅ ወረፋ ላይ ያሉ
  - የገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 135/2008 ማሻሻያ፣
  - የጣና ኃይቅ ደህንነትን ለመጠበቅ የደጀን ቀጠና ለመወሰን ረቂቅ ደንብ፣
  - ለህዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳ እና የልማት ተነሺዎችን መልሶ ለማቋቋም የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 44/2013 ላይ የአንቀጽ ማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ፣
  - የሊዝ መነሻ እና የቦታ ኪራይ ዋጋ ማሻሻያ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 7/2006፣
  - የማካካሻና የትክ ቤት የባለቤትነት መብት ለመፍጠር የተዘጋጀ አዲስ መመሪያ፣
- ✓ ለኢንቨስተመንት ቦርድ የቀረበ
  - የሪል ስቴት ልማት አስተዳደር መመሪያ፣
- ✓ በዝግጅት ላይ ያሉ
  - የአገልግሎት ዘርፍ የማስፋፊያ ቦታ አሰጣጥ መመሪያ፣
  - የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ተሻሽሎ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ፣
  - የቤት ልማት ስትራቴጅ ሰነድ፣
  - የጥቃቅንና አነስተኛ የኮንስትራክሽን ኩብንያዎች የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ

በመሆኑም እነዚህን በዝግጅት ሂደት ላይ ያሉ የማሻሻያና አዲስ ሰነዶች በፍጥነት በማጠናቀቅ አስፀድቆ ወደ ተግባር ለመግባት እየተሰራ ይገኛል፡፡

## 1.9. ተቋማዊ አሰራርን ማዘመን (E- Service)

**ግብ 6፡- በቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት እንዲኖረው ማድረግ እና ድጅታላይዝድ ማድረግ**

- ✓ በተቋሙ የሚታየውን ብልሹ አሰራርና ሌብነት ለመታገል እንዲሁም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታን ለማሳደግ ተቋማዊ አሰራሮችን ማሻሻልና ማዘመን አስፈላጊ ነው፡፡
- ✓ በመሆኑ ቤት መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ለምቶ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በ6 ዞኖች እና በ6 ሪጅዮፖሊታን ከተሞች 3,497 የመንግስት ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የቤት መረጃ ስርዓት (system software) ማስገባት የተቻለ ሲሆን በሌሎች ዞኖችና ከተሞች ለመተግበር የቤቶች መረጃ ለሶፍትዌሩ ግብዓት በሚሆን አግባብ በሃርድ ኮፒ የማደራጀት ስራ በሁሉም ከተሞች እየተሰራ ይገኛል፡፡

- ✓ በ3 ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንዲዘምን ለማድረግ ታቅዶ በ2 ከተሞች (ኬሚሴ እና ባህርዳር) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን የሚያስችል ሶፍትዌር በማስለማት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡
- ✓ ሌላው እንደ ክልል ከባህር ዳር ዩንቨርስቲ ጋር በመተባበር በከተማ መሬት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ዘርፍ ያሉትን የመረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን እና በኮንስትራክሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጥና ምዝገባ የመረጃ አያያዝ ዘዴን ለማዘመን የሚያስችሉ 2 system software (የተቀናጀ የመሬት ባለቤትነት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌር እና የኮንስትራክሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጥና ምዝገባ የመረጃ ስርዓት ሶፍትዌር) አስለምቶ ቢሮውን ጨምሮ በ8 የሪጅኦፓሊታን ከተሞች ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ ከመሬት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌር ልማት አኳያ:-
  - በከተሞች ያለውን የከተማ መሬት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ነባራዊ ሁኔታ ማለትም ችግሮችንና መፍትሄ ሃሳቦችን የሚያሳይ የዳሰሳ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
  - በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የመሬት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌር ልማትና ትግበራ የተገኙ ልምዶችን ለሶፍትዌሩ ልማት ግብዓት በሚሆኑበት አግባብ አደራጅቶ የመያዝ ስራ ተሰርቷል፡፡
  - በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት ሶፍትዌሩን ለማልማት ፕሮጀክት ፕሮፖዛልና ውል ተዘጋጅቶ ለቢሮው ቀርቧል፡፡
  - በቀረበውም ፕሮፖዛል ከባለድርሻ አካላት ጋር 4 ጊዜ ውይይት ተደርጎበታል፡፡
  - ወደ ስራ ለማስገባት የበጀት መጠኑ ተለይቶ ውል ለመውሰድ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
- ✓ የኮንስትራክሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጥና ምዝገባ የመረጃ ስርዓት (ሶፍትዌር) ልማትን በተመለከተ የባህር ዳር ዩንቨርስቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ሥራውን እንዲሰራ በዘርፍ ፈቃድ ያወጡ ባለሙያዎች ባደረጉት እገዛ ባለሙያዎቹ ሶፍትዌሩን በማልማት ላይ ሲሆኑ ሥራው 80% ደርሷል፡፡
- ✓ ሌላው ቢሮክራሲውን የሚያሳጥሩ ኦንላይን አገልግሎት በቢሮ፣ የከንቲባ ችሎት ደሴና ከሚሴ ከተሞች እንዲሁም በጎንደር ከተማ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ባለጉዳዮችን በጋራ ማወያይት መፍትሄዎች መልካም ጅምሮች ናቸው፡፡

## 1.10. ቅንጅታዊ አሰራርን ከማጠናከር አንፃር

ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር ማለትም:-

- ከገቢዎች ቢሮ ጋር በከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ፣
- ከህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ ጋር በመኖሪያ ቤት ህ/ስ/ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ዙሪያ፣
- ከመሬት ቢሮ ጋር በከተሞች ማስፋፊያ አካባቢ የመሬት አቅርቦትና ዝግጅት፣ በልማት ተነሽዎች የካሳ አከፋፈል፣ በገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና አሰጣጥ ዙሪያ፣

- ከገንዘብ ቢሮ ጋር በበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች፣
- ከስራና ስልጠና ቢሮ ጋር በስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ፣ ከውጭ ኦዲተር ቢሮ ጋር በፋይናንሸያልና ክዋኔ ኦዲት ዙሪያ፣
- ከፕላን እና ልማት ቢሮ ጋር በከተሞች አስተዳደር ወሰን፣ በከተማ እውቅና እና ደረጃ ሽግግር፣
- ከፖሊስ፣ ከፍ/ቤት፣ ከፍትህና ከፀረ-ሙስና ጋር በተለያዩ መመሪያዎች /ሰነዶች ዝግጅት፣ በህግ ማማከርና በህገ-ወጥ መሬት ወረራና ግንባታን በመከላከል ረገድ፣ በተቋሙ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን ከማስተካከልና ሌብነትን ከመታገል አንፃር፣
- ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመዋቅራዊ አደረጃጀት ዙሪያ በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጅ ከሌሎች መሰረተ ልማት አቅራቢና ተዛማጅ ተቋማት ጋር በዕቅድ ዝግጅትም ሆነ በትግበራ ወቅት ተቀናጅቶ የመስራት ልምዱ ውስንነት ያለበት ነው፡፡

## 1.11. ከግብዓት አቅርቦት አኳያ

- ✓ ለቢሮውና ለ9ኙ ዞን መምሪያዎች የኮምቦልቻ አፈር ምርምርን ጨምሮ፣ ለፕላን ኢንስቲቲዩት፣ የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP)፣ የምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት እንዲሁም ለማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ምዘና የፌደራል በጀት በጠቅላላው 182,995,355.41 ብር መደበኛ በጀት (ለደመወዝ 80,243,664.16 ብር እና ለስራ ማስኬጃ 102,751,691.25 ብር) እና 6,146,084,258.98 ብር ካፒታል በጀት በድምሩ 6,329,079,614.39 ብር ጠቅላላ በጀት ተመድቦ ፈፃሚውን የማዘጋጀትና ቁሳቁሶችን የማቅረብ እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- ✓ ግዥን በተመለከተ በቢሮ ደረጃ በበጀት ዓመቱ ከየስራ ክፍሉ የሚቀርብ የግዥ ፍላጎት መረጃ የማደራጀት ስራ የተሰራ ሲሆን በግልፅ ጨረታ 6 ጊዜ ታቅዶ 3 ጊዜ (50%) የ20,312,917.00 ብር ግዥ የተፈፀመ ሲሆን በውስን ጨረታ 16 ጊዜ ታቅዶ 29 ጊዜ (ከ100% በላይ) የ4,200,571.00 ብር ግዥ ተፈፅሟል፡፡ በፕሮፎርማ 36 ታቅዶ 49 ጊዜ (ከ100% በላይ) የ2,017,532.87 ብር ግዥ ተፈፅሟል፡፡ እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ የ4,757,751.12 ብር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሟል፡፡ በጠቅላላው የ31,288,771.99 ብር ግዥ ተፈጽሟል፡፡
- ✓ ሌላው በቢሮው፣ በዞን መምሪያውና በተዋረድ ተቋማት ካሉ ክፍት የስራ መደቦች መካከል በጀት ያላቸውን 90% በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በውስጥና በውጪ ዝውውር እንዲሁም በምደባ የዘርፉን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል የሰው ሀይል ስምሪት በማከናወን የመፈፀም አቅምን ለማሳደግ ታቅዶ በጀት ባላቸው መደቦች ላይ ወንድ 34 ሴት 9 በድምሩ 43 ስምሪት ተፈፅሟል፡፡

## 1.12. በጦርነት የተጎዱ ከተሞችን መልሶ ግንባታ ስራዎች

- ✓ በ2015 በጀት ዓመት ለወልቃይት ጠገዴ ሴቲት ሁመራ ዞን 1 ሞተር ሳይክል በልዩ ሁኔታ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በወራሪው ኃይል ለ3ኛ ጊዜ ወረራ ተፈፅሞባቸው ነፃ በወጡ የሰሜን ወሎ ዞን ከተሞች ማለትም ለቆቦ፣ ለዕራያ፣ ለሙጃ፣ ለሮቢት፣ ለጎብየ እና ለአላማጣ ከተሞች በቢሮው በኩል 11 ኮምፒተር፣ 93 ወንበር፣ 6 ጠረጴዛ፣ 8 ፕሪንትር፣ 1 ሰርቨር፣ 1 ካሜራ፣ 8 ካልኩሌተር፣ 14 ዲሊንክ 18 ፓንቸር፣ 11 ዕርሳስ መቅረጫ እና 58 መጋረጃ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ✓ በአማራ ክልል በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽ/ቤት የመልሶ ግንባታ ስራዎች ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በተመለከተ፡-
    - ወረራ በተካሄደባቸው ከተሞች ጉዳት የደረሰባቸው 18,315 መኖሪያ ቤቶችን ጥገና እና 15,934 ቤቶችን የመልሶ ግንባታ ስራ ለመስራት ታቅዶ የ87 ቤቶችን ጥገና እና የ497 ቤቶችን ግንባታ ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም ሰ/ሸዋ 493 ቤቶች ግንባታ እና ለ56 ቤቶች ጥገና፣ ደ/ጎንደር 23 ቤቶች ጥገ እና ዋግኽምራ 8 ቤቶችን ጥገና የተደረገ ሲሆን ወልድያ ከተማ ላይ በጦርነቱ የወደሙ 4 ቤቶችን የመልሶ ግንባታ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

- ወረራ በተካሄደባቸው 30 ከተሞች የመኖሪያ ቤቶችን መረጃ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሶፍትዌር ለማደራጀት ኮምፒውተሮች ድጋፍ እንዲደረግ እና የበየነመረብ ዝርጋታ ስራዎች እንዲከናወኑ ታቅዶ 2 (6.25%) ከተሞች ላይ (ኮምቦልቻ እና ወልዲያ) ኢንተርኔት አቅርቦት እንዲሟላ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በክልሉ በጦርነት ለተጎዱ 45 ት/ቤቶች ግንባታ የአካበቢ እና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፡፡
- የ9 የጤና ተቋማት ጥገና፣ የ22 የትምህርት ተቋማት ግንባታ፣ የ10 የስራና ስልጠና ፕሮጀክቶች ግንባታን እንዲያከናውኑ በተመረጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በአሰሪው አካል ከግንባታ ጋር ተያይዞ በነጠላ ዋጋ አሞላል ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን በማደራደር ውለታ ተይዞላቸዋል፡፡
- ለ17 የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ፕሮጀችቶች፣ ለ54 የእንስሳት ሃብት ልማት ፕሮጀችቶች እና 1 የግብርና ቢሮ ፕሮጀት የስራ ዝርዝር ዝግጅት፣ የነጠላ ዋጋ መሙላት እና ከተቋራጭ ጋር የዋጋ ድርድር ለማድረግ ሙያዊ ትብብር ተጠይቆ የነበረ ሲሆን ለ10 የወጣቶችና ስፖርት ፕሮጀችቶች፣ ለ15 የእንስሳት ሃብት ልማት ፕሮጀችቶች ሙያዊ ድጋፍ ተደርጎ ለሁሉም ፕሮጀክቶች የግንባታ ውለታ ተፈፅሟል፡፡
- ከተቋራጮች ጋር ውለታ ፕሮጀችቶች የግንባታ ክትትል የሚያደርጉ የክልል የቴክኒክ ቡድን ተደራጅቶ ወደ ስራ እንዲገባ የማስተባበር ስራ እና የዞን ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የመመደብ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የእንስሳት ሃብት ልማት በካፒታል በጀት ሊያስገነባ ያሰባቸውን 2 ፕሮጀክቶች የምህንድስና ዋጋ ግምት እንዲሰራላቸው ሙያዊ ትብብር ጠይቀው ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡
- በአጠቃላይ አሁን ላይ እየተገነቡ ያሉ 71 የመልሶ ማቋቋም ግንባታዎች ከቢሮው እስከ ታችኛው መዋቅር የማማከር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## 1.13. የቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም ማጠቃለያ

በዝግጅት ምዕራፉ ወቅት

- ✓ በየደረጃው ሁሉንም የዝግጅት ምዕራፍ ተግባሮች ቆጥሮ በመያዝ መፈፀም ተችሏል፡፡
- ✓ ጥራት ያለው ዕቅድ ማቀድ ተችሏል፡፡
- ✓ የዕቅድ ኦሬንቴሽን መድረኮችንም ከተለመደው በተለየ አግባብ መፈፀም ተችሏል፡፡
- ✓ በየደረጃው የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የሚያቃልሉ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለአብነትም፡-
    - የማያሰሩና መሻሻል ያለባቸው በርካታ መመሪያዎች ተሻሽለዋል፡፡
    - በልማትና መልካም አስተዳደር ተግባሮች ላይ ህዝብን በቀጥታ ማሳተፍ ተችሏል፡፡
    - ከ8 እስከ 22 ዓመት በላይ ሳይፈቱ ለረጅም ጊዜ ተንጠልጥለው የቆዩ የመሬት ጉዳዮች ተፈተዋል፡፡
- ✓ ሌላው ቢሮክራሲን የሚያሳጥሩ አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ለአብነትም፡-
    - በቢሮ ደረጃ ኦላይን ሰርቪስ መስጠት ተጀምሯል፡፡
    - በአንዳንድ ከተሞችም የከንቲባ ችሎት ተጀምሯል፡፡
    - ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር አሰራርን ለማዘመን የሚያስችሉ ሶፍትዌሮች ልማት ተጀምሯል፡፡
- ✓ እንዲሁም በተቋሙ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ሌብነትን ለመከላከል የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- ✓ የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራችን በተገቢው መንገድ በመፈፀማችን በተግባር ምዕራፍ አፈፃፀማችን መሻሻል አምጥቷል፡፡

በአጠቃላይ የእቅድ ዝግጅትና ኦረንቴሽን፣ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስራዎች፣ የድጋፍና ክትትል ስራዎች፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ የአሰራር መመሪያዎችን የማሻሻልና የማዘጋጀት እንዲሁም በተቋሙ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ በየመድረኮቻችን የከተማውን ነዋሪ ህዝብ

በማሳተፍ በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን እና የሌብነት ተግባራትን ለይቶ የመፍታትና ርምጃ የመውሰድ ተግባሮቻችን ሳይንጠባጠቡ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉበት አግባብ የተፈፀሙ መሆኑ ለአበይት ተግባሮቻችን የላቀ አፈፃፀም ጉልህ ድርሻ ነበራቸው፡፡

ይሁን እንጅ የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም ከዳይሬክቶሬት ዳይሬክቶሬት፣ ከዞን ዞን እና ከከተማ ከተማ በየፈርጁ ወጥነትና ተመሳሳይነት ባለው አግባብ በመፈፀም ረገድ ክፍተቶች የተስተዋሉበት ነበር፡፡ ይህም ለቀጣይ ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

## 2. የአበይት ተግባራት እቅድ አፈፃፀም

### 2.1. የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራዎች

#### ግብ 1፡- በ84 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮችና 7 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) ስታንዳርዱን የጠበቀ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት በቀጣይነት እንዲሻሻል በማድረግ የተገልጋዩ የዕርካታ መጠን አሁን ካለበት 48% ወደ 55% እንዲደርስ ማድረግ

በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በመጀመሪያ ሁሉም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ደረጃ ወጥቶላቸው ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና የተገልጋዩን ዕርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

- ከዚህም አኳያ በከተሞች የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል 7 የተለያዩ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው የወረዱ ሲሆን በክልሉ በሚገኙ 77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ7 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ84 (100%) ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች እና 7 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡
- ከመሪ ማዘጋጃ ቤቶች ምዕ/ጎጃም ግሽአባይ፣ ምስ/ጎጃም የጁቤ፣ ደ/ወሎ ተንታ፣ ማዕ/ጎንደር ምክሰኝት፣ ደ/ጎንደር ክምር ድንጋይ፣ ሰ/ወሎ ዞን ኮን ከተማ እና ሰ/ሸዋ ባልጭ መሪ ማዘጋጃ ቤቶች ተግባራዊ ያደረጉ ናቸው፡፡
- የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚተገበርባቸው 77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ7 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የተገልጋዩ ዕርካታ 55 በመቶ መድረሱን በጥናት ለማረጋገጥ በእቅድ ተይዞ በዞን ደረጃ በ56 ከተሞች እና በቢሮ ደረጃ ናሙና በተመረጡ 8 ከተሞች በድምሩ 64 ከተሞች ላይ በ3 ዘርፎች (መሬት ልማትና ማኔጅመንት፣ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አሰባሰብ) አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋይ ርካታ ጥናት የተጠና ሲሆን አማካይ የእርካታ ደረጃው 58.37% መድረሱን ጥናቱ ያመለክታል፡፡
- የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዱ በሚተገበርባቸው 84 ከተሞችም የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ እና እንዲተገበር ለማድረግ ታቅዶ በ81 (96.42%) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡
- የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ምዘና ለማካሄድ የሚያስችሉ ቁልፍ የምዘና መለኪያዎችን (Key Performance Indicators) በማዘጋጀት በ52 ከተማ አስተዳደሮች ምዘና በማካሄድ ለከተሞቹ ግብረ ለመስጠት ታቅዶ በዞን ደረጃ በ58 ከ/አስተዳደሮች እና በ6 መሪ ማዘጋጃቤቶች በድምሩ 64 (ከ100% በላይ) ከተሞች ላይ ምዘና ተካሄዷል፡፡
- በ3 ከተሞች (ባህርዳር፣ ጎንደር እና ደሴ) የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንዲዘምን ለማድረግ በእቅድ ተይዞ በ3 ከተሞች (ባህዳ ዳር፣ ከሚሴ፣ መካነ እየሱስ) የመሬት ይዞታ ፋይሎችን ወደ ሶፍት ኮፒ ስካን በማድረግ የመረጃ አያያዝን የማሻሻልና የማዘመን ስራ የተጀመረ ሲሆን ይህም በቀጣይ አገልግሎትን ዲጅታላይዝ ለማድረግ መሰረት የሚሆን ነው፡፡

- በዓመቱ በ84 ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች አተገባበር፣ የአሰራር ግልጽነት፣ የመረጃ ግልጽናትና ተደራሽነት፣ በአጠቃላይ የአገልግሎት አቅርቦት መሻሻል ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለከተሞቹ ግበረ መልስ ለመስጠት ታቅዶ በስልክ ድጋፍና ክትትል ለሁሉም ዞኖች የተደረገ ሲሆን በባህር ዳር ከተማ ከ/መ/ል መምሪያና 6 ክፍለ ከተሞች ላይ የአካል ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቢሮው አመራሮች የሚመራ ቡድን ሁሉንም ዞኖች የዳሰሰ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙ ላይ ግብረ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- ተዘጋጅተው የወረዱ የማ/ቤታዊ አገልገሎት ስታንዳርዶችን በሁሉም ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ በከተሞች የግብዓት እጥረት መኖር፣
- በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችም የሙያዊ ብቃት ማነስ፣
- በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት የዝግጁነትና የቅንነት እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት አለመኖር በተግባሩ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡
- በመሆኑም የወረዱ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶችን ለመተግበር የአመራሩንና የባለሙያውን አቅም ማሳደግ፣
- ለዚህም በተግባራት አፈጻጸም ላይ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግና የአፈጻጸም ግምገማ በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡

**ግብ 2፡- በ77ቱ ከተማ አስተዳደሮች ደረጃውን የጠበቀ የቄራ፣ የእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ የዘላቂ ማረፊያ፣ የገበያ ቦታና የንግድ ቤቶች እንዲሁም የመንገድ መብራት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣**

- የአገልግሎት አቅርቦት ስራዎችን በተመለከተ በቄራ አገልግሎት 14,441 (የቀንድ ከብት 11,256 እና የበግና ፍየል 3,185) የእርድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- የእሳት አደጋን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ ከተሞች 73 የእሳት አደጋዎች ተከስተው ለመከላከልና ሊደርስ ይችል የነበረውን አደጋ ለመቀነስ ተችሏል፡፡
- ለባይተዋር ዜጎች ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት በመስጠት በኩል ለ1,770 ባይተዋር ዜጎችን የቀብር አገልግሎት ተፈፅሟል፡፡
- የንግድ ማዕከላት ከማዘጋጀት አንጻር ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን በሁመራ ከተማ 90 የኮንቲነር ሱቆች እና በዳንሻ ከተማ 53 የገበያ ሼድ ተዘጋጅተው ለተጠቃሚ ተሰጥቷል፡፡
- በ3 ሪጂዮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች (ባህርዳር፣ ጎንደርና ደሴ) በገበያ ቦታና በንግድ ቤቶች እንዲሁም በመንገድ መብራት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በደብረ ማርቆስ ከተማ አንድ ጥናት ተከናውኗል፡፡
- በቄራ፣ በእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ በዘመናዊ ዘላቂ ማረፊያ፣ በገበያ ቦታና በንግድ ቤቶች እንዲሁም በመንገድ መብራት አገልግሎት ስራዎች ዙሪያ በተሞክሮነት የሚወሰድ አሰራር ተለይቶ ተቀምሮ በ77 ከተማ አስተዳደሮች እንዲስፋፋ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ የባህር ዳር ከተማ እና የደብረብርሃን ከተማ በገበያ ቦታ አቅርቦትና አስተዳደር ዙሪያ የተዘጋጀ መመሪያ ለተሞክሮነት ለሁሉም ዞንና ከተማ አስተዳደሮች ተላልፏል፡፡

**ግብ 3፡- የሙያ ስታንዳርድ፣ ሥርዓተ ትምህርትና የምዘና መሳሪያ በተዘጋጀላቸው 6 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችና ሌሎች ሙያዎች በመዋቅሩ ውስጥ ለሚገኙ 4,311 ፈፃሚዎች /ሰልጣኞች በተለያዩ የሙያ ደረጃዎች በማሰልጠን ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲሰማሩ ማድረግ፣**

- የሙያ ስታንዳርድ፣ ሥርዓተ-ትምህርትና የምዘና መሳሪያ በተዘጋጀላቸው 6 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች በ10 ከተማ አስተዳደሮች 12 አዳዲስ የምዘና ጣቢያዎች እንዲደራጁና ስራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ታቅዶ 6 የምዘና ጣቢያዎች የተቋቋሙ ሲሆን አፈፃፀሙም 50% ነው፡፡
- የሙያ ስታንዳርድ፣ ሥርዓተ-ትምህርትና የምዘና መሳሪያ በተዘጋጀላቸው 6 የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሙያዎች ላይ 25 መዛኞችንና 50 (35% ሴቶች) የኢንዱስትሪ አሰልጣኞች እንዲዘጋጁ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 36 ሴት 7 በድምሩ 43 የሰለጠኑ ሲሆን አፈጻጸሙም 57.33% ነው፡፡
- በ12 ከተማ አስተዳደሮች በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት መስኮች አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ 4,311 (70% ሴቶች) አመራሮችንና ባለሙያዎችን በአሴት ማኔጅመንት፣ ቤቶች ማስተላለፍ፣ ቄራ፣ እሳት አደጋ፣ ህብረተሰብ ተሳትፎ፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አሰባሰብ፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በማሰልጠን ብቃታቸው ተመዝኖ እውቅና እየተሰጠ ወደ ስራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ የ3,635 ሰልጣኞችና

ተመዛኞች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አሰባሰብ 60፣ በአረንጓዴ ልማት 30 በድምሩ 90 ባለሙያዎች ስልጠና ወስደው ተመዝነዋል፡፡

**ግብ 4፡- በከተሞች ህብረተሰቡ ሊሳተፍባቸው በሚገቡ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ስራዎች ላይ ህዝቡ በገንዘብ፣ በጉለበትና በአይነት 2.2 ቢሊዮን ብር እንዲያዋጣ በማድረግ የህዝቡ ተሳትፎ ምጣኔ በአማካይ 50% እንዲሆን ማድረግ፣**

- የከተማ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎችን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያግዝ 1 የአሰራር ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ በከተሞች እንዲተገበር የአሰራር ማኑዋሉ ለማዘጋጀት በተያዘዉ እቅድ መሰረት ተዘጋጅቶ ለከተሞቹ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡
- በ681 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የሙብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ) ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 50% አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 651,692,591 ብር፣ በጉልበት 658,106,100 ብር፣ በቁሳቁስ 415,859,830 ብር በድምሩ 1,725,658,521 ብር የሚገመት ገንዘብ ለልማት ስራዎች አስተዋጾ ተደርጓል፡፡ በነዚህ የልማት ስራዎች ላይ ወንድ 2,863,212 ሴት 2,312,561 በድምሩ 5,175,773 የህብረተሰብ ክፍል የተሳተፈ ሲሆን በዚህም የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ በአማካይ 44.68% ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 10፡- በአካባቢ ልማት ስራዎች የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ የዞኖች አፈፃፀም በደረጃ**

| ተ.ቁ | ዞን | በልማት የተሳተፈ ህዝብ ብዛት | | | የሴቶች ተሳትፎ በመቶኛ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | ዋግ ኽምራ | 32,869 | 46,027 | 78,896 | 58.34 | 1ኛ |
| 2 | ደሴ | 108,497 | 118,479 | 226,976 | 52.20 | 2ኛ |
| 3 | ደ/ማርቆስ | 74,880 | 81,120 | 156,000 | 52.00 | 3ኛ |
| 4 | ማዕ/ጐንደር | 92,075 | 96,093 | 188,168 | 51.07 | 4ኛ |
| 5 | ጐንደር | 169,840 | 171,917 | 341,757 | 50.30 | 5ኛ |
| 6 | ወልዲያ | 28,150 | 28,200 | 56,350 | 50.04 | 6ኛ |
| 7 | ባ/ዳር | 85,229 | 82,384 | 167,613 | 49.15 | 7ኛ |
| 8 | ምዕ/ጐንደር | 22,711 | 21,319 | 44,030 | 48.42 | 8ኛ |
| 9 | ደ/ታቦር | 29,498 | 27,081 | 56,579 | 47.86 | 9ኛ |
| 10 | ምዕ/ጐጃም | 90,588 | 77,844 | 168,432 | 46.22 | 10ኛ |
| 11 | ኦሮሞ | 10,305 | 8,567 | 18,872 | 45.40 | 11ኛ |
| 12 | ሰ/ሸዋ | 294,126 | 241,758 | 535,884 | 45.11 | 12ኛ |
| 13 | አዊ | 199,470 | 156,762 | 356,232 | 44.01 | 13ኛ |
| 14 | ደ/ወሎ | 885,960 | 667,105 | 1,553,065 | 42.95 | 14ኛ |
| 15 | ደ/ብርሃን | 87,580 | 64,575 | 152,155 | 42.44 | 15ኛ |
| 16 | ኮምቦልቻ | 81,696 | 59,760 | 141,456 | 42.25 | 16ኛ |
| 17 | ደ/ጎንደር | 309,607 | 215,147 | 524,754 | 41.00 | 17ኛ |
| 18 | ሰ/ወሎ | 61,053 | 39,389 | 100,442 | 39.22 | 18ኛ |
| 19 | ምስ/ጐጃም | 179,597 | 101,131 | 280,728 | 36.02 | 19ኛ |
| 20 | ሰ/ጎንደር | 19,481 | 7,903 | 27,384 | 28.86 | 20ኛ |
| | **ጠ/ድምር** | **2,863,212** | **2,312,561** | **5,175,773** | **44.68** | |

**ሠንጠረዥ 11፡- በህብረተሰብ ተሳትፎ የዞኖች አፈፃፀም በደረጃ**

| ተ.ቁ | ዞን | የህብረተሰብ ተሣትፎ መጠን | | | | የመንግስት ወጪ በብር | ጠቅላላ የአካባቢ ስራዎች በብር | የህ/ሰብ ተሳትፎ በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በገንዘብ | በጉልበት | በቁሣቁስ | ጠ/ድምር | | | |
| 1 | ደ/ብርሃን | 16,823,202 | 16,240,942 | 9,824,948 | 42,889,092 | 1,728,824 | 44,617,916 | 96.13 |
| 2 | ኮምቦልቻ | 9,012,291 | 42,802,230 | 13,482,162 | 65,296,683 | 3,348,997 | 68,645,680 | 95.12 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ደሴ | 46,418,699 | 21,844,952 | 7,380,524 | 75,644,175 | 7,655,635 | 83,299,810 | 90.81 |
| 4 | ደ/ወሎ | 87,155,313 | 96,666,275 | 73,427,832 | 257,249,420 | 39,492,700 | 296,742,120 | 86.69 |
| 5 | ሰ/ሸዋ | 69,960,125 | 69,800,140 | 54,000,000 | 193,760,265 | 102,160,300 | 295,920,565 | 65.48 |
| 6 | ሰ/ወሎ | 23,966,840 | 28,813,080 | 16,214,657 | 68,994,577 | 48,589,522 | 117,584,099 | 58.68 |
| 7 | ወልዴያ | 3,542,000 | 20,270,000 | 6,542,000 | 30,354,000 | 22,876,596 | 53,230,596 | 57.02 |
| 8 | ባ/ዳር | 62,016,713 | 22,898,392 | 16,712,156 | 101,627,261 | 78,471,624 | 180,098,885 | 56.43 |
| 9 | ምስ/ ጐጃም | 64,773,863 | 30,894,624 | 23,383,863 | 119,052,350 | 106,636,994 | 225,689,344 | 52.75 |
| 10 | ምዕ/ጐጃም | 120,660,544 | 95,024,308 | 82,262,360 | 297,947,212 | 290,551,299 | 588,498,511 | 50.63 |
| 11 | ዋግ ኽምራ | 42,825 | 6,018,409 | 117,957 | 6,179,191 | 6,179,191 | 12,358,382 | 50.00 |
| 12 | ደ/ጎንደር | 60,854,757 | 42,209,033 | 39,426,234 | 142,490,024 | 202,807,504 | 345,297,528 | 41.27 |
| 13 | ማዕ/ጐንደር | 15,595,928 | 16,636,091 | 8,492,367 | 40,724,386 | 94,758,032 | 135,482,418 | 30.06 |
| 14 | አዊ | 275,468 | 46,252,922 | 20,670,431 | 67,198,821 | 197,164,314 | 264,363,135 | 25.42 |
| 15 | ደ/ማርቆስ | 18,832,829 | 16,903,748 | 13,075,867 | 48,812,444 | 262,272,700 | 311,085,144 | 15.69 |
| 16 | ጐንደር | 26,410,005 | 35,045,192 | 24,261,489 | 85,716,686 | 485,124,687 | 570,841,373 | 15.02 |
| 17 | ደ/ታቦር | 10,632,150 | 3,334,763 | 2,846,119 | 16,813,032 | 120,313,889 | 137,126,921 | 12.26 |
| 18 | ሰ/ጎንደር | 2,150,000 | 5,280,782 | 1,104,368 | 8,535,150 | | 8,535,150 | |
| 19 | ምዕ/ጐንደር | 7,680,351 | 26,161,486 | 1,245,503 | 35,087,340 | | 35,087,340 | |
| 20 | ኦሮሞ | 4,888,688 | 15,008,731 | 1,388,993 | 21,286,412 | | 21,286,412 | |
| | **ጠ/ድምር** | **651,692,591** | **658,106,100** | **415,859,830** | **1,725,658,521** | **2,070,132,808** | **3,795,791,329** | **45.46** |

- ለነዚህ የልማት ስራዎች በመንግስት በኩልም 2,070,132,808 ብር ወጪ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው (የመንግስት + የህዝብ ተሳትፎ) 3,795,791,329 ብር ለልማት ስራ የዋለ ሲሆን በዚህም የህብረተሰብ ተሳትፎ ድርሻን በአማካይ 45.46% ማድረስ ተችሏል፡፡
- የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ከህበረተሰቡ በጉልበት፣ በገንዘብና በቁሳቁስ 20 ሚልዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡
- ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን በከተሞች በሚከናወኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ስራዎች ላይ 2,450 የከተማ ነዋሪዎችን ለማሳተፍ በእቅድ ተይዞ 2,880 (ከ100% በላይ) የከተማ ነዋሪዎችን ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች ዙሪያ 1 የተሻለ አፈፃፀም ተለይቶ በ12ቱ ዞኖችና እና በ8ቱ ሪጂዮፖሊታን ከተሞች እንዲቀመርና እንዲስፋፋ ለማድረግ ታቅዶ በምስራቅ ጎጃም ዞን የሉማሜ ምርጥ ተሞክሮ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ለዞኖቹ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- በሁሉም ከተሞች የተደራጀና ዘላቂ የህዝብ ተሳትፎን በማረጋገጥ እንዲሁም የህዝብ ተሳትፎና የመንግስት ተሳትፎ መረጃውን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ በመያዝ እና ሪፖርት በማድረግ በኩል ሰፊ ክፍተት ይስተዋላል፡፡
- ለአብነትም የወጣቶችን ተሳትፎ መረጃ እና የመንግስት ወጪ ከህብረተሰብ ተሳትፎ መረጃው ጋር አብሮ የማይሰበሰብበትና የማይያዝበት ሁኔታ በመኖሩ የህብረተሰብ ተሳትፎ ድርሻን እና የወጣቶችን ተሳትፎ ድርሻ ትክክለኛ ስሌት ማስላት አይቻልም፡፡
- በመሆኑም የህዝብ ተሣትፎ ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችሉ የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

**ግብ 5፡- የከተማነት እውቅና አሰጣጥ ሥርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ 25 የገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን የከተማነት እዉቅና እንዲያገኙ በማድረግ የከተሞች ቁጥር አሁን ካለበት 681 ወደ 706 (በ3.67%) እንዲያድግ ማድረግ፣**

- የከተማነት እውቅና አሰጣጥ ሥርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ 25 የገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እዉቅና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ለ2 (8%) የገጠር ማዕከላት ከተማነት እውቅና በመስጠት የከተሞች ቁጥር አሁን ካለበት 681 ወደ 683 እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

**ግብ 6፡- ከተሞችን በፈርጅ የማደራጀት ስርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ 38 ከተሞች የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ በማድረግ ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት እንዲጠናከር ማድረግ፣**

- የከተማ ፈርጅ ለውጥ ሥርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ 38 ከተሞች (ከፈርጅ አምስት ወደ ፈርጅ አራት 10 ከተሞች፣ ከፈርጅ አራት ወደ ፈርጅ ሶስት 8 ከተሞች፣ ከፈርጅ ሶስት ወደ ፈርጅ ሁለት 10 ከተሞች፣ ከፈርጅ ሁለት ወደ ፈርጅ አንድ 10 ከተሞች) የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 21 (55.26%) ከተሞች (ከፈርጅ አምስት ወደ ፈርጅ አራት 9 ከተሞች፣ ከፈርጅ አራት ወደ ፈርጅ ሶስት 12 ከተሞች) የደረጃ ሽግግር ተደርጓል፡፡
- የከተማነት ዕውቅና ላገኙ እና የደረጃ ሽግግር ለተደረገላቸው 63 ከተሞች የሰው ኃይል አደረጃጀት እንዲዘጋጅ በተያዘዉ እቅድ መሰረት 23 ከተሞች ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተልኳል፡፡

## ግብ 7፡- በ681 ከተሞች የመንግስት የፋይናንስ ኦዲት አስተዳደር ስርዓት ተከትለው ሀብታቸውን ውጤት በሚያመጣ መንገድ አሟጠው በመጠቀም የመሰረተ ልማት ወጭያቸውን 75% ከራሳቸው ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ገቢ እንደሸፍኑ ማድረግ፣

- የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ በ604 ከተሞች 1.639 ቢሊዮን ብር እንዲሁም ከገቢዎች ጋር በመቀናጀት በ77 ከተማ አስተዳደሮች 4.468 ቢሊዮን ብር በድምሩ 6.107 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ከመሪ መዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች 1.188 (72.51%) ቢሊዮን ብር እና ከከተማ አስተዳደሮች 4.696 (ከ100% በላይ) ቢሊዮን ብር በድምሩ 5.884 (96.34%) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡
- ከዚህም በተጨማሪ ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ከቢሮው ዕቅድ ያልወረደላቸው ቢሆንም በዞኑ በሚገኙ መሪ ማዘጋጃቤ፣ ንዑስ ማዘጋጃቤ እና ታዳጊ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው የአገልግሎት ገቢ አርዕስቶች ውስጥ ብር 44,060,500 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 38,029,893.82 (86.38%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡
- በክልሉ በሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 57 የገቢ አርዕስቶች ውስጥ በአማካይ በ40 የገቢ አርዕስቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በአብዛኛው ከተሞች በአማካይ 38 (95%) የገቢ አርዕስቶች ላይ የአገልግሎት ገቢ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡

### ሠንጠረዥ 12፡- የመሪ፣ የንዑስና የታዳጊ ከተሞች ገቢ አሰባሰብ የዞኖች አፈጻጸም በደረጃ

| ተ.ቁ | የዞኖች ስም | ፈርጅ ሶስት | | ፈርጅ አራት | | ፈርጅ አምስት | | ጠቅላላ | | ከዓመቱ አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንዉን | ዕቅድ | ክንዉን | ዕቅድ | ክንዉን | ዕቅድ | ክንዉን | |
| 1 | ምስ/ጎጃም | 84,000,000 | 164,304,017 | 35,000,000 | 22,648,375 | 46,000,000 | 17,333,147 | 165,000,000 | 204,285,539 | 123.81 |
| 2 | ደ/ወሎ | 105,000,000 | 128,797,827 | 66,500,000 | 51,753,147 | 54,000,000 | 28,832,870 | 225,500,000 | 209,383,845 | 92.85 |
| 3 | ሰ/ሸዋ | 133,000,000 | 116,413,366 | 38,500,000 | 38,417,859 | 31,000,000 | 14,448,775 | 202,500,000 | 169,280,000 | 83.60 |
| 4 | ሰ/ወሎ | 70,000,000 | 50,708,136 | 17,500,000 | 19,186,084 | 34,000,000 | 26,947,570 | 121,500,000 | 96,841,790 | 79.71 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 77,000,000 | 67,614,498 | 31,500,000 | 16,537,212 | 38,000,000 | 24,120,336 | 146,500,000 | 108,272,046 | 73.91 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | 98,000,000 | 85,864,837 | 35,000,000 | 16,130,224 | 49,000,000 | 17,664,045 | 182,000,000 | 119,659,106 | 65.75 |
| 7 | ማዕ/ጎንደር | 126,000,000 | 100,787,043 | 28,000,000 | 6,601,195 | 34,000,000 | 11,679,098 | 188,000,000 | 119,067,336 | 63.33 |
| 8 | አዊ | 21,000,000 | 12,244,363 | 35,000,000 | 25,992,536 | 39,000,000 | 15,725,098 | 95,000,000 | 53,961,997 | 56.80 |
| 9 | ምዕ/ጎንደር | 77,000,000 | 42,028,664 | 21,000,000 | 8,136,385 | 9,000,000 | 4,192,559 | 107,000,000 | 54,357,607 | 50.80 |
| 10 | ኦሮሞ | 14,000,000 | 4,893,840 | 21,000,000 | 18,049,279 | 15,000,000 | 2,156,356 | 50,000,000 | 25,099,475 | 50.20 |
| 11 | ሰ/ጎንደር | 35,000,000 | 14,361,003 | | | 16,000,000 | 2,070,218 | 51,000,000 | 16,431,221 | 32.22 |
| 12 | ዋግ ኽምራ | 77,000,000 | 5,305,140 | 14,000,000 | 3,337,061 | 14,000,000 | 3,168,593 | 105,000,000 | 11,810,794 | 11.25 |
| | **ድምር** | **917,000,000** | **793,322,734** | **343,000,000** | **226,789,357** | **379,000,000** | **168,338,665** | **1,639,000,000** | **1,188,450,756** | **72.51** |

### ሠንጠረዥ 13፡- የከተማ አስተዳደሮች ገቢ አሰባሰብ አፈጻጸም በዞን ደረጃ

| ተ.ቁ | የዞንና የከተማ ስም | የአመቱ እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወልቃ/ጠ/ሰ/ ሁመራ ዞን | 18,000,000 | 29,819,669 | 165.66 | 1ኛ |
| 2 | ምሥ/ጎጃም | 130,193,951 | 210,855,321 | 161.95 | 2ኛ |
| 3 | ደ/ማርቆስ | 200,855,470 | 249,339,304 | 124.14 | 3ኛ |
| 4 | ሰ/ ሸዋ | 130,762,414 | 159,143,004 | 121.70 | 4ኛ |
| 5 | ደ/ታቦር | 95,379,450 | 114,932,671 | 120.50 | 5ኛ |
| 6 | ሰ/ወሎ | 112,532,798 | 134,654,333 | 119.66 | 6ኛ |
| 7 | ዋግ ኽምራ | 28,498,254 | 33,488,913 | 117.51 | 7ኛ |
| 8 | ደ/ ጎንደር | 149,716,956 | 168,072,572 | 112.26 | 7ኛ |
| 9 | ደ/ወሎ | 111,941,303 | 119,323,590 | 106.59 | 9ኛ |
| 10 | ማዕ/ጐንደር | 35,847,140 | 38,159,085 | 106.45 | 10ኛ |
| 11 | ምዕ/ ጎጃም | 269,053,819 | 273,259,144 | 101.56 | 11ኛ |
| 12 | ወልዲያ | 95,687,965 | 94,097,330 | 98.34 | 12ኛ |
| 13 | አዊ | 239,787,662 | 234,422,725 | 97.76 | 13ኛ |
| 14 | ምዕ/ ጐንደር | 51,885,157 | 50,459,973 | 97.25 | 14ኛ |
| 15 | ጐንደር | 524,409,820 | 501,461,222 | 95.62 | 15ኛ |
| 16 | ባህርዳር | 1,102,977,484 | 1,028,150,725 | 93.22 | 16ኛ |
| 17 | ደሴ | 422,226,917 | 392,210,695 | 92.89 | 17ኛ |
| 18 | ሰ/ጎንደር | 55,957,651 | 51,799,781 | 92.57 | 18ኛ |
| 19 | ኦሮሚያ | 99,791,757 | 86,620,997 | 86.80 | 19ኛ |
| 20 | ደ/ብርሀን | 366,925,175 | 271,885,450 | 74.10 | 20ኛ |
| 21 | ኮምቦልቻ | 225,568,857 | 141,136,613 | 62.57 | 21ኛ |
| | ድምር | 4,468,000,000 | 4,696,115,486.90 | ከ100% በላይ | |

**ግብ 8፡- የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 155 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት ማድረግ፣**

- የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 155 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች (ንዑስ መዘጋጃ 52፣ መ/መዘጋጃ 103) የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን ኦዲት እንዲያስደርጉ ታቅዶ 183 ከተሞች ኦዲት ያደረጉ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡
- በተደረገው ኦዲትም ብር 3,778,428.00 በጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 1,915,839.00 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪ ብር 1,915,839.00 ነው፡፡
- ከባለፉት ዓመታት በኦዲት የተገኘና የተንከባለለ ብር 8,249,392.00 የገንዘብ ጉድለት 100% ተመላሽ ለማድረግ ታቅዶ ብር 3,508,864.00 የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 4,740,528.00 ያልተመለሰ ነው፡፡
- ከተሞች የፋይናንስ ብክነትን ለመከላከል ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የፋይናንስ አጠቃቀም ኦዲት በማድረግ በኩል ከጊዜ መሻሻል ያሳየ ሲሆን የኦዲት ተደራሽነት ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ4 እጥፍ አድጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 14፡- የማዘጋጃቤት ከተሞች ፋይናንስ አጠቃቀም ኦዲት የዞኖች አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | የዞኖች ስም | ኦዲት የተደረጉ ከተሞች | | | በበጀት አመቱ የታየ ጉድለት የገንዘብ መጠን | | | ባለፉት ዓመታት በጉድለት የታየ ዉዝፍ ብር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | የታየ ጉድለት | የተመለሰ | ያልተመለሰ | የተንከባለለ | የተመለሰ | ያልተመለሰ |
| 1 | ምዕ/ጎጃም | 17 | 26 | 152.94 | 109,395 | 109,395 | | | | |
| 2 | ደ/ወሎ | 19 | 29 | 152.63 | 1,185,657 | 496,572 | 689,085 | 1,795,841 | 1,228,599 | 567,242 |
| 3 | ኦሮሞ | 6 | 6 | 100.00 | 23,338 | 15,849 | 7,489 | | | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ማ/ጎንደር | 20 | 21 | 105.00 | 483,461 | 322,260 | 161,201 | 1,767,646 | 45,121 | 1,722,524 |
| 5 | ሰ/ሸዋ | 22 | 28 | 127.27 | 787,066 | 258,397 | 528,669 | 2,606,235 | 1,690,358 | 915,877 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 14 | 26 | 185.71 | 670,350 | 304,020 | 366,330 | 418,444 | 170,526 | 247,918 |
| 7 | ዋግ | 8 | 3 | 37.50 | 35,417 | 35,417 | | 80,843 | 42,024 | 38,819 |
| 8 | አዊ | 8 | 17 | 212.50 | 249,166 | 166,213 | 82,952 | | | |
| 9 | ምዕ/ጎንደ | 8 | 2 | 25.00 | 53,231 | 29,357 | 23,874 | 26,189 | 26,189 | |
| 10 | ሰ/ወሎ | 13 | 14 | 107.69 | 148,896 | 148,896 | | 71,266 | 71,266 | |
| 11 | ምስ/ጎጃም | 15 | 11 | 73.33 | 32,452 | 29,463 | 2,988 | 1,437,079 | 228,446 | 1,208,634 |
| 12 | ሰ/ጎንደር | 5 | | | | | | 45,850 | 6,336 | 39,514 |
| | **ድምር** | **155** | **183** | **118.06** | **3,778,428** | **1,915,839** | **1,862,589** | **8,249,392** | **3,508,864** | **4,740,528** |

ይሁን እንጅ፡-

- የከተሞችን የገቢ አቅም ከማሳደግ አንጻር ሁሉንም የገቢ አርስቶች በዝርዝር ለይቶ አሟጦ አለመሰብሰብ፣
- ብዙ ድካም በሚጠይቁት የአገልግሎት ገቢ አርስቶች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራትና
- የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል እንዲቻል በወቅቱ ኦዲት አለማድረግ፣
- በኦዲት ወቅት በተገኙ ጉድለቶች ላይም ፈጥኖ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰድ ወዘተ የሚታዩ ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የገቢ ብክነትን ለመከላከል የሚያስችሉ የአሰራር ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ አመታዊ የፋይናንስ አጠቃቀም ኦዲት አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፣ በኦዲት የተገኙ ጉድለቶች በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረጉ ጥብቅ አመራር መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 2.2. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሥራዎች

### ግብ 9፡- በበጀት ዓመቱ በኢፌዲሪ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለሚዘጋጀው ክልላዊ ልማት ፕላን (Regional Spatial Development Plan) እና የከተሞች ትስስር ፕላን (City Cluster Development Plan) ዝግጅት ዙሪያ በክልሉ በኩል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- የክልላዊ ልማት ፕላን (Regional Spatial Development Plan) እና የከተሞች ትስስር ፕላን (City Cluster Developmet Plan) ዝግጅት በዚህ በጀት ዓመት 100% እንዲጠናቀቅ በሚመለከተው አካል ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ያለ ሲሆን ስራውን የሚሰራው UN Habitate ባዘጋጀው ወርክ ሾፕ ላይ ሁለት ጊዜ መሳተፍ ተችሏል፡፡ በአማካሪ ድርጅቱ የተዘጋጀውን የኢንስፔክሽን ሪፖርት በመገምገም ግብዓት ተሰጥቷል፡፡

- የፕላን ዝግጅት ሂደቱ አሁን ያለበትን ሁኔታ በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሪፖርት 100% ተጠናቋል፡፡ የነባራዊ ሁኔታ ጥናት 90% ተጠናቋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ስራው 48% ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በውሉ መሰረት የፕሮጀክቱ እድሜ 18 ወር ሲሆን ለ6 ወር የተራዘመ በመሆኑ አጠቃላይ ስራው በቀጣዩ በጀት ዓመት እስከ ታህሳስ 30/2016 ዓ/ም የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

### ግብ 10፡- አሳታፊ፣ ጥራት ያለውና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የከተማ ፕላን ዝግጅት እንዲኖር በማድረግ 95 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ፣ መሰረታዊ የከተማ ፕላን 80፣ መዋቅራዊ ፕላን 15 እንዲሁም 20 የሰፈር ልማት ፕላን (NDP) ማዘጋጀት፣

- በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ዙሪያ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ባለቤትነት ለማሳደግ 42,000 (35% ሴቶች) የከተማው ነዋሪ ህዝብ በፕላን ዝግጅትና ክለሳ ወቅት ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ታቅዶ በከተሞች በመሠረታዊ ካርታና ፕላን ዝግጅት እንዲሁም በመዋቅራዊ ካርታና ፕላን ዝግጅት ወቅት ወንድ 25,325 ሴት 13,235 ድምር 38,560 (91.80%) ህዝብ ማወያየት ተችሏል፡፡

- ለ95 ከተሞች መሠረታዊ ካርታ (ቅየሳ) ለመስራት ታቅዶ የ95 (100%) ከተሞች (ቁይ፣ ሀገረ ሰላም፣ ማንኩሳ፣ ግምጃ ቤት፣ ሸንዲ፣ ከምር ድንጋይ (ሰ/ሸዋ)፣ ሙጃ ሮቢት፣ ገነት፣ ቆላ ድባ፣ ደጎማ፣ አይሲጋ፣ ድቤት፣ ፈንድቃ/ጃዊ/፣ አለምበር፣ ተንታአጅባር፣ አዳዳ፣ ፋግታ፣ ድማማ አንገረፈ፣ ዋዝ፣ ዝሀራ፣ ገደብዬ፣ ጨረቲ፣ ጨፋሮቢት፣ ባልጪ፣ ሞላሌ፣ አምቦሜዳ፣ ጋብላ፣ ጃንሱማ፣ አርብ

ገበያ/ታች ጋይንት/፣ ደብረ ሲና፣ አቅስታ፣ ማክሰኝት፣ ሀርቡ፣ ጉጉፍቱ፣ ጠባሲት፣ ሜላት፣ ፈንድቃ (ደ/ጎንደር)፣ ዜኖ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ደልጊ፣ ሽከላ፣ ወለዲ፣ ሙሉ ሀሙሲት፣ ገና፣ ሳና፣ አምባ ጊዮርጊስ፣ ጋሸና፣ ዱባባ፣ ነጋዴ ባህር፣ ጊላ፣ ካቤ፣ ሰኞ ገበያ /ደ/ወሎ/፣ ሶሮቃ፣ አልዩ አንባ፣ የትኑራ፣ ምከሬ፣ ይስማላ፣ ሊበን፣ ገነት አቦ፣ አዲስ አለም ዋድ፣ ፍላቂት ገረገራ፣ ጅጋ፣ ደጐሎ፣ አጉት፣ ማሰሮ ደንበ፣ አሸሬ፣ ቆማ፣ እሁዲት፣ ዋብር፣ ሊጫ፣ ጅብ አስራ፣ ዳማ ማርቆስ፣ ሰቀላ፣ ጫት ዋርካ፣ ሀሙስ ገበያ፣ አረፋ መድሃኒአለም፣ ልጓማ፣ ፋጂ፣ ደብረማዊ፣ ጊፍት፣ ቀይ አፈር፣ ሮቢት /ደ/ወሎ/፣ ቦከክሳ፣ ጅሁር፣ ጉዳለማ፣ አባይ አጥር፣ ግራር አንባ፣ ቦረን፣ ወገሬ፣ በኬጃ፣ ጨወድባ፣ ጥራሂና፣ ዲንካራና ማሂን) መሠረታዊ ካርታቸው ተዘጋጅቷል፡፡

- የ33 ከተሞች (አምባ ጊዮርጊስ፣ ፍላቂት ገረገራ፣ ቁይ፣ ማንኩሳ፣ ይስማላ፣ ደልጊ፣ ደጎሎ፣ አርባ ፀጓር፣ ሳሊ፣ ደብረ ማዊ፣ ደብረታቦር፣ ሊበን፣ ድኩል አርባ፣ ሱሉላ፣ ካቤ፣ እነዋሬ፣ የጁቤ፣ ደጋጋ፣ ቦረን፣ ቦከክሳ፣ ይስማላ፣ ሀገረገነት፣ እሁዲትና ጫትዋርካ፣ ቦረን፣ ጊፍት፣ ቀይ አፈር፣ ልጓማ፣ ፋጂ፣ ጨውድባ፣ሀሙስ ገበያና ጅሁር) ከተሞች ከኦርቶ ፎቶ ወደ Line Map የመቀየር ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ለ80 ከተሞች መሰረታዊ የከተማ ፕላን ለመስራት ታቅዶ ለ80 (100%) (አምቦ ሜዳ፣ አየሁ፣ ሮቢት፣ ፋግታ፣ አልዩ አምባ፣ ሜላት፣ ሀገረ ሰላም (ምስ/ጐጃም)፣ ድቤት፣ ማንኩሳ፣ ፈንድቃ (ደ/ጎንደር)፣ መሎ ሀሙሲት፣ ጋብላ፣ ጀንግር፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ደብረ ዘይት፣ ቱመት፣ ጃንሱማ፣ ገደብዬ፣ ደጐማ፣ ሶሮቃ፣ ገዘህራ፣ ጨረቲ፣ ግራር አምባ፣ ወኸርድ፣ ከምር ድንጋይ ሰ/ሸዋ፣ ልጓማ፣ ጠባሲት፣ ሰኞገበያ፣/ደ/ወሎ/ ጉጉፍቱ፣ ካቤ፣ ሃሮ፣ ፋጂ፣ ቦረን፣ ተኩለሸ፣ ሸርያገነት፣ ነጋዴባህር፣ ባጃ፣ አይሰጋ፣ አፀደማርያም፣ ዱባባ፣ ጨዉድባ፣ የትኑራ፣ ዋብር፣ አባይአጥር፣ ግፋት፣ ቀይ አፈር፣ ቦከክሳ፣ ጥራሂና፣ ጊሳ፣ ወገሬ፣ ጅሁር፣ ሽከላ፣ በኬጃ፣ ገና፣ ዜኖ፣ ደቅ፣ ዳሂ መላ፣ ሀሙሲት፣ ገነት፣ አጉት፣ አዲስ አለም /ዋድ/፣ ገነት አቦ፣ አለም በር፣ ዋዝ፣ ድማማ አንገረፈ፣ ዲንካራ፣ ሙጃ ሮቢት፣ አዳዳ፣ ሊበን፣ ይስማላ፣ ተንታ አጅባር፣ ሰቀላ፣ እሁዲት፣ ደማ ማርቆስ፣ አረፈ መድሃኒዓለም፣ ማክሰኚት፣ ሀሙስ ገበያ፣ ጫት ዋርካ፣ ፅፅቃና ድል ይብዛ) መሠረታዊ ፕላናቸው ተዘጋጅቷል፡፡
- ለ15 ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ15 ከተሞች (አርብ ገበያ፣ ግምጃ ቤት፣ ትክል ድንጋይ፣ ጅጋ፣ ደ/ሲና፣ ኮምቦልቻ፣ የጁቤ፣ ቁይ፣ ሸንዲ፣ ደልጊ፣ አለም ከተማ፣ ቆላድባ፣ ኢቃስታ፣ ሀርቡና ሞላሌ) አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡
- 20 የሠፈር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ወልዲያ 2 እና መርጡለ ማርያም 2፣ አማኑኤል 2፣ ደ/ኤልያስ 1፣ ግምጃቤት 3፣ ደብረ ማርቆስ 1፣ ሉማሜ 1 ኮምቦልቻ 1 አርበ ገበያ /ታች ጋይንት/ 1፣ የጁቤ 1፣ ፍኖተ ሰላም 1፣ ከሚሴ 2፣ ላሊበላ 1 እና ሞላሌ 1) በድምሩ 20 (100%) የሠፈር ልማት ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡
- ለ80 ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎችን (Urban Profile) በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ ለ79 ከተሞች (አምቦ ሜዳ፣ አየሁ፣ ሮቢት፣ ፋግታ፣ አልዩ አምባ፣ ሜላት፣ ሀገረ ሰላም /ምስ/ጐጃም፣ ድቤት፣ የጁቤ፣ማንኩሳ፣ ፈንድቃ /ደ/ጎንደር፣ መሎ ሀሙሲት፣ ጋብላ፣ ጀንግር፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ደብረ ዘይት፣ ቱመት፣ ጃንሱማ፣ ገደብዬ፣ ደጐማ፣ ሶሮቃ፣ ገዘህራ፣ ጨረቲ፣ ግራር አምባ፣ ወኸርድ፣ ከምር ድንጋይ (ሰ/ሸዋ)፣ ልጓማ፣ ጠባሲት፣ ሰኞገበያ፣ ጉጉፍቱ፣ ካቤ፣ ሃሮ፣ ፋጂ፣ ቦረን፣ ተኩለሸ፣ ሸርያገነት፣ ነጋዴባህር፣ ባጃ፣ አይሰጋ፣ አፀደማርያም፣ ዱባባ፣ ጨዉድባ፣ የትኑራ፣ ዋብር፣ አባይአጥር፣ ግፋት፣ ቀይ አፈር፣ ቦከክሳ፣ ጥራሂና፣ ጊሳ፣ ወገሬ፣ ጅሁር፣ ሽከላ፣ በኬጃ፣ ገና፣ ዜኖ፣ ደቅ፣ ዳሂ መላ፣ ሀሙሲት፣ ገነት፣ አጉት፣ አዲስ አለም /ዋድ/፣ ገነት አቦ፣ አለም በር፣ ዋዝ፣ ድማማ አንገረፈ፣ ዲንካራ፣ ሙጃ ሮቢት፣ አዳዳ፣ ሊበን፣ ይስማላ፣ ተንታ አጅባር፣ ሰቀላ፣ እሁዲት፣ ደማ ማርቆስ፣ አረፈ መድሃኒዓለም፣ ማክሰኚት፣ ሀሙስ ገበያ፣ ጫት ዋርካና ፅፅቃ) ማሰባሰብና ማደራጀት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም (98.9%) ነው፡፡

**ግብ 11፡- በክልሉ የሚገኙ 665 ከተሞች በተዘጋጀላቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማትና አገልግሎቶች ቅንጅትና ትግበራ ፕላን እንዲመሩ ማድረግ፣**

- አዲስ 24 ከተሞች ወደ ፕላን ትግበራ እንዲገቡ በማድረግ በፕላን የሚመሩ ከተሞች ቁጥር አሁን ካለበት 641 ወደ 665 እንዲያግ ለማድረግ ታቅዶ 35 ከተሞች ወደ ፕላን ትግበራ እንዲገቡ በማድረግ 676 ከተሞች በተዘጋጀላቸው ፕላን እንዲመሩ ተደርጓል፡፡
- ከዞኖችና ከከተሞች ለሚቀርቡ የፕላን ማስተካከያ ጥያቄዎችና የፕላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ከ38 ከተሞች (ደብረ ኤልያስ፣ ሀሙሲት፣ ክምር ድንጋይ፣ ኩል መስክ፣ ማንኩሳ፣ አዴት፣ ሸዋ ሮቢት፣ ቱሉ አውሊያ፣ የቦቅላ፣ ይፋግ፣ አዘና፣ ደ/ማርቆስ፣ እንጅባራ 2 NDP፣ እንጅባራ SP፣ ጅጋ፣ ኩታበር፣ መተማ ዮሐንስ፣ ወገዳ፣ ዴንሳ፣ ኮቱ፣ ቻግኒ፣ ጎንደር፣ ወጀል፣ ግሼ አባይ፣ ቀራንዮ፣ ኤላ፣ ወይን አምባ፣ ደጋን፣ ጎንደር፣ ጭልጋ፣ ጎርጎራ፣ ቀራኒዮ፣ ዳንግላ፣ መሸሃ፣ አርባያና ቡሬ) ከተሞች ለቀረቡ የፕላን ማስተካከያ ጥያቄዎች ፕላን ምደባ ለውጥን ጨምሮ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡
- የፕላን ምደባ ለውጥና ጥሰት በሚታይባቸው 10 ከተሞች የፕላን አፈጻጸም ኦዲት በማድረግ ለከተሞቹ ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ ለ14 (ከ100% በላይ) ከተሞች (ሞጣ፣ ደብረ ብርሃን፣ ኬሚሴ፣ ሸዋሮቢት፣ ፈረስቤት፣ እና በዞን ደ/ወሎ 1 ከተማ እና ማዕ/ጎንደር 1 ከተማ፣ ደ/ጎንደር አንዳቤትና ጃራገዶ፣ ሰ/ሸዋ አርመንያ፣ ምዕ/ጎጃም ግሽ አባይ፣ መሀል ገነትና ደንበጫ፣ አዊ እንጅባራ) የፕላን አፈጻጸም ኦዲት ተደርጓል፡፡
- የከተሞችን ፕላን አፈፃፀም አቅም ለማሳደግ ለ60 ከተሞች የመስክ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ71 (ከ100% በላይ) ከተሞች የመስክ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- በፕላን ዝግጅት ወቅት የፕላን ጥራት ችግር በመኖሩ ወደ መሬት ለማውረድ አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ከጊዜ ወደ ጊዜ የፕላን ጥሰት እና የዞኒንግ ለውጥ ጥያቄዎች መበራከት፣
- የፕላን ዕድሜያቸው የተጠናቀቀ የከተማ ዕድገት ፕላኖችን በወቅቱ ክለሳ አለማድረግና ለዚህም የተሟላ አቅም አለመኖር፣
- የተዘጋጁ ፕላኖችን በወቅቱ አጸድቆ ወደ ተግባር አለመግባት ወይም ሳይፀድቁ ወደ ተግባር መግባት ወዘተ ከፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ክፍተቶች ናቸው፡፡
- ለዚህም ዋናው ምክንያት በፕላን ዝግጅት ወቅት የሚከናወኑ የቅየሳና የሶሽዎ-ኢኮኖሚ መረጃዎችን በተገቢው የጥራት ደረጃ በማከናወን ረገድ ጉድለት መኖር እና የከተማ አመራሩም ባለቤት ሆኖ በፕላን ዝግጅት ወቅት ህዝቡን በተሟላ መንገድ በማሳተፍ ችግር ፈቺ ፕላን እንዲዘጋጅ አለማድረጉ ነው፡፡
- ሌላው በፕላን ዝግጅት ወቅት ከሚፈጠረው ክፍተት በተጨማሪ አብዛኛው የከተሞች መሬት በህገ-ወጥ ይዞታዎችና ግንባታዎች ስለሚያዝና በፕላን ምድቡ መሰረት መሬቱን ለማልማት ከባድ ወጪ የሚጠይቅ ሲሆን የተሻለ ቦታ ለማግኘት ሲባል የዞኒንግ ለውጥና የፕላን ጥሰት የሚፈፀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡

በመሆኑም በከተሞች የሚታየውን የፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ውጤታማ ማድረግ በሚያስችል አግባብ የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ወጥና ተናባቢ መዋቅር በቅርቡ የተዘረጋ ሲሆን በቀጣይ ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት ለፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ስራው ተገቢውን የአመራር ትኩረት መስጠት፣ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት እንዲሁም ተያያዥ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብና በተገቢው መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## 2.3. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች

### ግብ 12፡- በክልሉ የሚገኙ ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ የፕላን ወሰን እንዲኖራቸዉ ሆኖ የመሬት ሀብታቸዉን በሚገባ ማስተዳደርና መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ፣

የከተማ መሬት ሃብትን ከንጥቂያና ከወረራ በመከላከል በቁጠባ ለላቀ ልማት ማዋል እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ዘመን ላይ ስለምንገኝ የጠራ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ማስተዳደር ይገባል፡፡

- ከዚህም አኳያ ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ የፕላን ወሰን እንዲኖራቸው በማድረግ የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ቆጥረውና መዝግበው ማስተዳደር እንዲችሉ የ203 ከተሞችን (77 ከተማ አስተዳደሮችና 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) የፕላን ወሰን እንደገና

እንዲካለል በማድረግ የተሟላ መረጃ ተደራጅቶ ለመያዝ ታቅዶ 378 (ከ100% በላይ) ከተሞች መረጃቸውን አደራጅተው የያዙ ናቸው፡፡

- በ302 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) የተተከሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ታቅዶ 354 (ከ100% በላይ) ከተሞች በመሬት ላይ የሚገኙ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመለየት መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲያዝና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ያደረጉ ናቸው፡፡ እንዲሁም በ302 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) የጠፉትንና የተነቀሉትን 600 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በአዲስ እንዲተኩ ለማድረግ ታቅዶ ቀደም ሲል የጠፉ 2,117 (ከ100% በላይ) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መተካት ተችሏል፡፡
- በ32 የUIIDP ፕሮግራም ተጠቃሚ ከተሞች የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት በከተሞች የፕላን ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ 250,000 ሄ/ር ቦታዎችን በአገልግሎት አይነት በመቁጠርና በመመዝገብ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ208 ከተሞች 115,755.59 ሄ/ር (46.3%) ቁራሽ መሬት መቁጠርና መመዝገብ ተችሏል፡፡
- በ379 ታዳጊ ከተሞች 72,800 ይዞታዎች በመመሪያ ቁጥር 3/13 መሰረት ተጣርተው የከተማ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ በ225 ከተሞች ለ41,965 (57.64%) ሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰጥቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 15፡- የሰነድ አልባ ይዞታዎች መረጃ አሰባሰብና መስተንግዶ የዞን መምሪያዎች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | የመምሪያው ስም | የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰነድ የሰጡ ከተሞች በቁጥር | | | የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰነድ የተሰጣቸው ብዛት | | | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | |
| 1 | ደ/ወሎ | 54 | 63 | 116.67 | 1,135 | 7,888 | 694.98 | 1ኛ |
| 2 | አዊ | 39 | 9 | 23.08 | 8,353 | 12,595 | 150.78 | 2ኛ |
| 3 | ሰ/ሸዋ | 31 | 33 | 106.45 | 6,909 | 5,846 | 84.61 | 3ኛ |
| 4 | ኦሮሞ | 15 | 7 | 46.67 | 3,582 | 1,599 | 44.64 | 4ኛ |
| 5 | ሰ/ወሎ | 34 | 7 | 21 | 7,577 | 3,300 | 43.55 | 5ኛ |
| 6 | ምዕ/ጎንደር | 9 | 15 | 166.67 | 2,579 | 1,033 | 40.05 | 6ኛ |
| 7 | ደ/ጎንደር | 38 | 31 | 81.58 | 8,296 | 3,214 | 38.74 | 7ኛ |
| 8 | ሰ/ጎንደር | 16 | 9 | 56.25 | 4,075 | 1,255 | 30.80 | 8ኛ |
| 9 | ዋግ | 14 | 1 | 7.14 | 3,476 | 1,003 | 28.86 | 9ኛ |
| 10 | ማዕ/ጎንደር | 34 | 20 | 58.82 | 7,361 | 1,709 | 23.22 | 10ኛ |
| 11 | ምዕ/ጎጃም | 49 | 9 | 18.37 | 10,252 | 1,357 | 13.24 | 11ኛ |
| 12 | ምስ/ጎጃም | 46 | 21 | 45.65 | 9,205 | 1,166 | 12.67 | 12ኛ |
| | **ድምር** | **379** | **225** | **59.37** | **72,800** | **41,965** | **57.64** | |

- በ302 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) አስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚገኙ 97,345 ህገ-ወጥ ይዞታና ግንባታዎችን በተላከው ፎርማት መሰረት በመለዩት መረጃው ተደራጅቶ እንዲያዝ እና እንዲያፈርሱ (ሥርዓት እንዲይዙ) ለማድረግ ታቅዶ በ319 ከተሞች 101,193 ህገወጥ ይዞታዎች ተደራጅተው የተያዙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 23,018 (18.01%) ህገ-ወጥ ግንባታዎች እንዲወገዱ በማድረግ 141.961 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 16፡- ህገ-ወጥ ይዞታዎችንና ግንባታዎችን ስርዓት ማስያዝ የዞን መምሪያዎች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | የዞኑ/ የከተማው ስም | ህገወጥ ግንባታን የለዩ ከተሞች በቁጥር | | | የተደራጀ ህገወጥ መረጃ በቁጥር | | | የፈረሰ ህገ-ወጥ ግንባታ | ወደ መሬት ባንክ የገባ መሬት በሄ/ር | አፈጻጸም በመቶኛ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | | | | |
| 1 | ባ/ዳር | 4 | 1 | 25 | 4,583 | 2,100 | 45.82 | 2,364 | 7 | 112.57 | 1ኛ |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ደ/ታቦር | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 2,481 | 54.13 | 2,481 | | 100 | 2ኛ |
| 3 | ሰ/ሸዋ | 39 | 38 | 97.44 | 7,791 | 4,549 | 58.39 | 3,921 | 9.9072 | 86.19 | 3ኛ |
| 4 | ደ/ብርሃን | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 2,105 | 45.93 | 1,648 | 6.28 | 78.29 | 4ኛ |
| 5 | ዋግ | 11 | 2 | 18.18 | 1,835 | 1254 | 68.34 | 851 | 5 | 67.86 | 5ኛ |
| 6 | ደሴ | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 482 | 10.52 | 277 | | 57.47 | 6ኛ |
| 7 | ጎንደር | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 990 | 21.60 | 546 | 0.65 | 55.15 | 7ኛ |
| 8 | ሰ/ጎንደር | 7 | 7 | 100 | 1,375 | 960 | 69.82 | 400 | 5.45 | 41.67 | 8ኛ |
| 9 | ደ/ወሎ | 44 | 46 | 104.55 | 11,366 | 13,083 | 115.11 | 5,082 | 30.7 | 38.84 | 9ኛ |
| 10 | ኦሮሞ | 12 | 7 | 58.33 | 2,566 | 731 | 28.49 | 269 | 2.82 | 36.80 | 10ኛ |
| 11 | ኮምቦልቻ | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 644 | 14.05 | 205 | 1 | 31.83 | 11ኛ |
| 12 | ማዕ/ጎንደር | 32 | 31 | 96.88 | 4,400 | 4,464 | 101.45 | 874 | 6.48 | 19.58 | 12ኛ |
| 13 | ወልድያ | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 107 | 2.33 | 19 | 0.3 | 17.76 | 13ኛ |
| 14 | አዊ | 20 | 16 | 80 | 4,308 | 4,580 | 106.31 | 522 | 9.9139 | 11.40 | 14ኛ |
| 15 | ምዕ/ጎንደር | 14 | 8 | 57.14 | 2,291 | 476 | 20.78 | 50 | 8.44 | 10.50 | 15ኛ |
| 16 | ደ/ማርቆስ | 1 | 1 | 100 | 4,583 | 2,220 | 48.44 | 205 | 10 | 9.23 | 16ኛ |
| 17 | ደ/ጎንደር | 28 | 33 | 117.86 | 6,416 | 10,283 | 160.27 | 862 | 8.22 | 8.38 | 17ኛ |
| 18 | ምዕ/ጎጃም | 33 | 48 | 145.45 | 5,775 | 13,641 | 236.21 | 1,133 | 5.15 | 8.31 | 18ኛ |
| 19 | ሰ/ወሎ | 21 | 17 | 80.95 | 6,875 | 11,115 | 161.67 | 672 | 8.81 | 6.05 | 19ኛ |
| 20 | ምስ/ጎጃም | 30 | 58 | 193.33 | 5,683 | 24,928 | 438.64 | 637 | 15.84 | 2.56 | 20ኛ |
- ✓ በ8 ከተሞች (ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ ደ/ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ደ/ብርሃን፣ ኮምቦልቻ እና ደ/ታቦር) የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አያያዝ ሽፋን 80% ስለመድረሱ በጥናት ለማረጋገጥ ታቅዶ ባህርዳር 80%፣ ጎንደር 80%፣ ወልደያ 74%፣ ደሴ 60%፣ ደ/ብርሃን 60%፣ ደ/ማርቆስ 50%፣ ምዕ/ጎንደር 85%፣ ደ/ጎንድር 65% ደ/ታቦር 48%፣ ኮምቦልቻ እና ምዕ/ጎጃም 56% በማስወገድ በአማካኝ 68% በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግብ 27፡- በ64 ነባር እና 30 አዲስ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ቀጣይነት ያለው እና የተመቻቸ የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት፣**

- ✓ የፋይናንስ ስርዓት ያላቸው 64 ነባር ከተሞች እንዲጠናከሩ እና 30 አዲስ ከተሞች (ከውሃ ቢልና ከሌሎች አማራጮች ጋር ማስተሳሰር) ቀጣይነት ያለው የተመቻቸ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 61 (95.31%) ነባር ከተሞችን የማጠናከር ስራ የተሰራ ሲሆን 40 (ከ100% በላይ) ከተሞች ደግሞ በአዲስ የደረቅ ቆሻሻ ፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጉ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 31፡- ቀጣይነት ያለው የተመቻቸ የደረቅ ቆሻሻ ፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች**

| ተ.ቁ | የዞኑ/ከተማው ስም | ነባሮችን ማጠናከር | | | በአዲስ የጀመሩ ከተሞች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | ደ/ወሎ | 1 | 8 | 800 | 1 | 9 | 900 |
| 2 | ደ/ጎንደር | 1 | 10 | 1000 | 1 | 3 | 300 |
| 3 | ማዕ/ጎንደር | 6 | 12 | 200 | 3 | 6 | 200 |
| 4 | ሰ/ሸዋ | 1 | | | 1 | 4 | 400 |
| 5 | ሰ/ወሎ | 2 | 5 | 250 | 2 | 2 | 100 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 12 | 6 | 50 | 3 | 6 | 200 |
| 7 | ምዕ/ጎጃም | 6 | 7 | 116.67 | 4 | 4 | 100 |
| 8 | ምዕ/ጎንደር | 3 | 1 | 33.33 | 1 | 1 | 100 |
| 9 | ደ/ማረቆስ | 1 | 1 | 100 | 3 | 1 | 33.33 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ዋግ ከምራ | | | | 1 | 1 | 100 |
| 11 | ጎንደር | 1 | 1 | 100 | | | |
| 12 | ደሴ | 1 | 1 | 100 | | | |
| 13 | ባ/ዳር | 1 | 1 | 100 | | | |
| 14 | ደ/ብርሃን | 1 | 1 | 100 | | 1 | |
| 15 | ኮምቦልቻ | 1 | 1 | 100 | 1 | | |
| 16 | አዊ | 12 | 3 | 25 | 2 | 1 | 50 |
| 17 | ሰ/ጎንደር | 7 | 3 | 42.86 | 4 | 1 | 25 |
| 18 | ኦሮሚያ | 6 | | | 3 | | |
| 19 | ደ/ታቦር | 1 | | | | | |
| 20 | ወልዲያ | 1 | | | | | |
| | **ድምር** | **64** | **61** | **95.31** | **30** | **40** | **133.33** |

**ግብ 28፡- በ8 ከተሞች እንደ የከተሞች የእድገት ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በመስፈርቱ ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ፣**

- ✓ ከ20,000 በላይ ህዝብ በሚኖርባቸው 8 ከተሞች በስታንዳርዱ መሰረት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ እንዲያደርጉ ታቅዶ 20 (ከ100% በላይ) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏዋል፡፡ ከ20,000 በታች ህዝብ በሚኖርባቸው አዲስ 8 ከተሞች በስታንዳርዱ መሰረት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ እንዲያደርጉ ታቅዶ ምዕ/ጎንደር በ14 (ከ100% በላይ) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በ6 ሪጅዮፖሊታን ከተሞች አቅማቸውን ታሳቢ ያደረጉ 10 ጊዜያዊ የቆሻሻ ማቆያ ቦታ (የቅብብሎሽ ጣብያ) ለማዘጋጀት ታቅዶ ባህርዳር 7፣ ደ/ማርቆስ 11፣ ደ/ታቦር 10 እና ወልድያ 12 በድምሩ 40 ጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎችን በማዘጋጀት የእቅዱ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡
- ✓ በ155 ከተሞች ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ታቅዶ ምዕ/ጎጃም 22፣ ምስ/ጎጃም 33፣ ማዕ/ጎንድር 9፣ ምዕ/ጎንደር 3፣ ሰ/ጎንደር 15፣ ሰ/ወሎ 19፣ ደ/ወሎ 24፣ ሰ/ሸዋ 30፣ ኦሮሞ 2፣ አዊ 12፣ ባህርዳር 12፣ ደ/ታቦር 1 እና ወልደያ 3 በድምሩ 185 ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- ✓ በክልላችን ሁሉም ከተሞች የተቀናጀ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት አልተፈጠረም፡፡
- ✓ በከተሞች የሚከናወኑ የፅዳት ተግባራትም የእለት ተለት ተግባር ከመሆን ይልቅ የዘመቻ ሥራዎች በመሆናቸው ቀጣይነት የላቸውም፡፡ ሁሉም የክልላችን ከተሞች በሚባል ደረጃ ዘመናዊ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (ዘመናዊ ሳኒተሪ ላንድፊል) የላቸውም፡፡
- ✓ አብዛኞቹ ከተሞች ቋሚ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የላቸውም፡፡
- ✓ ያላቸውም ቢሆን በአብዛኛው ከከተማው ክልል ውጭ የተዘጋጁ በመሆናቸው ደህንነታቸው የተጠበቀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጁ አይደሉም፡፡
- ✓ ህብረተሰቡም ቢሆን ቆሻሻን ከምንጩ በመለየት በመቀነስና መልሶ በመጠቀም በኩል ያለው ግንዛቤ በጣም አናሳ በመሆኑ እና ደረቅ ቆሻሻ በየአካባቢው ሲጣል እያየ የተለመደ አድረጎ የሚቆጥር (ቆሻሻን የመጠየፍ ባህሉ የዳበረ ባለመሆኑ) በመኖሪያና በሥራ ቦታዎች አካባቢውን ውብ፣ ጽዱና ሳቢ በማድረግ በኩል የድርሻውን እየተወጣ አይደለም፡፡
- ✓ ለዚህም ዋናው ምክንያት ህብረተሰቡን እና ባለድርሻ አካላትን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በማሣተፍ፣ የተደራጁ ማህበራትን በመደገፍና በማብቃት፣ እንዲሁም ቆሻሻን የሚጠየፍ ህብረተሰብ በመፍጠር በኩል አመራሩም ሆነ ባለሙያው በቂ ግንዛቤ ኑሮት እና ትኩረት ሰጥቶ የሚጠበቀውን ያህል አለመስራቱ ነው፡፡
- ✓ በመሆኑም ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት በከተማ ነዋሪው በኩል የአመለካከት ለውጥ ማምጣት መተኪያ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡
- ✓ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግም በተከታታይነት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መስራትና ለዚህም የተለያዩ ሚዲያዎችን ሽፋን በስፋት መጠቀም ተገቢ ነው፡፡
- ✓ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ የተዘጋጁ ህጎችንና ስታንዳርዶችን በተገቢው መንገድ መተግበር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

## ግብ 29፡- በ500 ከተሞች ህብረተሰቡንና ተቋማትን በማስተባበር በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 22.25 ሚሊየን ችግኝ በመትከልና በመንከባከብ የከተሞችን ገጽታ ማሻሻል፣

- ✓ በከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች በሁሉም ከተሞች ለ800,000 (50% ሴቶች) የከተማ ነዋሪዎች በአረንጓዴ ልማት፣ በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ በቀጥታ እንዲሳተፍ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 570,931 ሴት 499,739 በድምሩ ለ1,070,670 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር 743,728 ወንድ እና 602,496 ሴት በድምሩ 1,346,224 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን በአረንጓዴ ልማት ስራ (በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ) በቀጥታ ማሳተፍ ተችሏል፡፡
- ✓ በ500 ከተሞች በክረምት ወራት በህብረተሰብ ተሳትፎ ንቅናቄ በመፍጠር 22.25 ሚሊዮን የተለያዩ የውበት ችግኞችን በመትከል በ1,510 ሄ/ር አረንጓዴ ቦታዎችን በአዲስ ለማልማት ታቅዶ በ412 (82.4%) ከተሞች 20,031,494 (90.03%) የውበት ችግኞችን በመትከል 2,416 (ከ100% በላይ) ሄ/ር አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡

### ሰንጠረዥ 32፡- የዞኖች እና ከተሞች ችግኝ ተከላ እቅድ አፈጻጸም በደረጃ

| ተ.ቁ | የዞን/ከተማ ስም | በችግኝ ተከላው | | | የችግኝ ተከላ እቅድ አፈጻጸም | | | የለማ አረንጓዴ ቦታ በሄ/ር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መሳተፍ ያለባቸው | የተሳተፉ ከተሞች | አፈጻጸም | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | ምዕ/ጎጃም | 55 | 23 | 41.82 | 2,000,000 | 2,430,784 | 121.54 | 140 | 145 | 103.57 |
| 2 | ምስ/ጎጃም | 55 | 26 | 47.27 | 2,300,000 | 1,801,135 | 78.31 | 145 | 556 | 383.45 |
| 3 | አዊ/ብ/ዞን | 30 | 16 | 53.33 | 800,000 | 307,202 | 38.40 | 80 | 30 | 37.50 |
| 4 | ደ/ጎንደር | 55 | 55 | 100 | 2,350,000 | 1,212,720 | 51.61 | 150 | 101 | 67.33 |
| 5 | ሰ/ጐንደር | 20 | 20 | 100 | 700,000 | 325,598 | 46.51 | 60 | 32 | 53.33 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ማእ/ጎንደር | 45 | 6 | 13.33 | 2,500,000 | 843,446 | 33.74 | 140 | 140 | 100 |
| 7 | ምዕ/ጎንደር | 20 | 8 | 40 | 600,000 | 565,066 | 94.18 | 40 | 63 | 157.50 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 44 | 44 | 100 | 1,850,000 | 1,153,923 | 62.37 | 90 | 151 | 167.78 |
| 9 | ደ/ወሎ | 55 | 75 | 136.36 | 2,500,000 | 4,552,946 | 182.12 | 130 | 204 | 156.92 |
| 10 | ኦሮሞ | 20 | 27 | 135 | 900,000 | 750,655 | 83.41 | 60 | 55 | 91.67 |
| 11 | ዋግኽምራ | 15 | 18 | 120 | 500,000 | 324,556 | 64.91 | 40 | 46 | 115 |
| 12 | ሰ/ሸዋ | 55 | 58 | 105.45 | 2,500,000 | 2,002,977 | 80.12 | 160 | 236 | 147.50 |
| 13 | ጎንደር | 6 | 6 | 100 | 600,000 | 429,161 | 71.53 | 60 | 52 | 86.67 |
| 14 | ባ/ዳር | 6 | 6 | 100 | 600,000 | 1,055,684 | 175.95 | 70 | 234 | 334.29 |
| 15 | ደሴ | 5 | 5 | 100 | 500,000 | 1,026,915 | 205.38 | 60 | 171 | 285 |
| 16 | ደ/ብርሀን | 5 | 5 | 100 | 200,000 | 212,450 | 106.23 | 20 | 30 | 150 |
| 17 | ደ/ማርቆስ | 4 | 4 | 100 | 300,000 | 812,202 | 270.73 | 15 | 81 | 540 |
| 18 | ኮምቦልቻ | 4 | 4 | 100 | 250,000 | 166,824 | 66.73 | 30 | 45 | 150 |
| 19 | ወልዲያ | 3 | 3 | 100 | 150,000 | 20,250 | 13.50 | 10 | 44 | 440 |
| 20 | ደብረታቦር | 3 | 3 | 100 | 150,000 | 37,000 | 24.67 | 10 | | |
| | **ድምር** | **505** | **412** | **81.58** | **22,250,000** | **20,031,494** | **90.03** | **1,510** | **2,416** | **160** |

- ✓ በ77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ126 መሪ መዘጋጃ ቤቶች የሚገኙ 4,000 ተቋማት ግቢና አካባቢያቸውን በ50 ሜትር ራዲየስ እና በ210 ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች ደግሞ መኖሪያ ቤታቸውን በ20 ሜትር ራድየስ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ለማድረግ ታቅዶ 10,026 (ከ100% በላይ) ተቋማት እና በ265 ከተሞች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች አካባቢያቸውንና የመኖሪያ ቤታቸውን ዙሪያ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ተደርጓል፡፡
- ✓ 4,240 ሄ/ር ነባር አረንጓዴ ቦታዎች እንዳይጠፉና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለመንከባከብ ታቅዶ 4,155 ሄ/ር (98%) እንክብካቤ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ✓ የአለም ባንክ ፕሮጀክት ተግባራዊ በተደረገባቸው 32 ከተሞች 36 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ እና ለ175 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 40 (ከ100% በላይ) አዲስ የመዝናኛ ፓርኮች የለሙ ሲሆን ለ171 (97.71%) ነባር የመዝናኛ ፓርኮችን እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 33:- የዞኖችና ከተሞች አዲስ እና ነባር ፓርክ ልማት አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | የዞን/ከተማ ስም | እንክብካቤ አረንጓዴ ቦታ በሄክታር | | | ነባር ፓርክ በቁጥር | | | አዲስ ፓርክ ልማት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | ምዕ/ጎጃም | 299.69 | 299.69 | 100 | 13 | 13 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| 2 | ምስ/ጎጃም | 547.6 | 547.644 | 100 | 27 | 32 | 118.52 | 3 | 8 | 266.67 |
| 3 | አዊ/ብ/ዞን | 64 | 57.3 | 90 | 4 | 4 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| 4 | ደ/ጎንደር | 369 | 369 | 100 | 7 | 6 | 85.71 | 3 | 2 | 66.67 |
| 5 | ሰ/ጐንደር | 12 | 12 | 100 | 1 | 3 | 300 | 1 | 1 | 100 |
| 6 | ማዕ/ጎንደር | 258.7 | 258.7 | 100 | 7 | | | 1 | | |
| 7 | ምዕ/ጎንደር | 39 | 30 | 77 | 19 | 19 | 100.0 | 2 | 3 | 150 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 18.8 | 18.8 | 100 | 10 | 8 | 80 | 4 | 1 | 25 |
| 9 | ደ/ወሎ | 299.7 | 301.3 | 101 | 4 | 4 | 100 | 2 | 3 | 150 |
| 10 | ኦሮሞ/ብ/ዞን | 84 | 84 | 100 | 3 | 3 | 100 | 2 | 1 | 50 |
| 11 | ዋግኽምራ | 54 | 54 | 100 | 4 | 4 | 100 | 1 | 4 | 400 |
| 12 | ሰ/ሸዋ | 541 | 541 | 100 | 10 | 11 | 110 | 2 | 4 | 200 |
| 13 | ጎንደር | 120 | 120 | 100 | 8 | 8 | 100 | 1 | | |
| 14 | ባ/ዳር | 580 | 575 | 99 | 24 | 24 | 100 | 1 | 3 | 300 |
| 15 | ደሴ | 251 | 208 | 83 | 9 | 9 | 100 | 1 | | |
| 16 | ደ/ብርሃን | 620 | 620 | 100 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ደ/ማርቆስ | 31 | 25 | 81 | 3 | 2 | 66.67 | 1 | 1 | 100 |
| 18 | ኮምቦልቻ | 15.6 | 15.6 | 100 | 8 | 8 | 100 | 2 | | |
| 19 | ወልዲያ | 5 | 5 | 100 | 11 | 11 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| 20 | ደብረታቦር | 30 | 30 | 100 | 2 | 1 | 50 | | | |
| | **ድምር** | **4,240** | **4,172** | **98.39** | **175** | **171** | **97.71** | **36** | **40** | **111.11** |

- ✓ ለ163 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ለማድረግ እና 41 አዲስ ችግኝ ጣቢያ ለማልማት ታቅዶ 157 (96.91%) እንክብካቤ የተደረገ ሲሆን 41 (100%) አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች ለምተዋል፡፡

### ሰንጠረዥ 34:- የዞኖችና ከተሞች የነባር እና አዲስ ችግኝ ጣቢያ እንክብካቤና ልማት አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የዞን /ከተማ/ስም | ነባር ችግኝ ጣቢያ እንክብካቤ | | | የለሙ አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | ምዕ/ጎጃም | 20 | 20 | 100 | 4 | 13 | 325 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | 28 | 28 | 100 | 2 | 4 | 200 |
| 3 | ምዕ/ጎንደር | 5 | 5 | 100 | 2 | 3 | 150 |
| 4 | ጎንደር | 14 | 14 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| 5 | ደሴ | 6 | 6 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| 6 | ደ/ብርሀን | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| 7 | ደ/ወሎ | 37 | 37 | 83.78 | 2 | 2 | 100 |
| 8 | ምስ/ጎጃም | 10 | 10 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| 9 | ማእ/ጎንደር | 2 | 2 | 100 | 4 | 3 | 75 |
| 10 | ሰ/ወሎ | 6 | 6 | 60 | 4 | 6 | 150 |
| 11 | ደ/ጎንደር | 10 | 9 | 90 | 4 | 1 | 25 |
| 12 | አዊ/ብ/ዞን | 4 | 4 | 100 | 4 | 2 | |
| 13 | ሰ/ጎንደር | 3 | 3 | 100 | 2 | | |
| 14 | ኦሮሞ/ብ/ዞን | 1 | 1 | 100 | 2 | | |
| 15 | ደ/ማርቆስ | 1 | 1 | 100 | 1 | | |
| 16 | ኮምቦልቻ | 4 | 4 | 100 | 1 | | |
| 17 | ደብረታቦር | 1 | 1 | 100 | | | |
| 18 | ወልዲያ | 2 | 2 | 100 | | | |
| 19 | ባ/ዳር | 8 | 3 | 37.5 | 1 | | |
| 20 | ዋግኽምራ | | | | 1 | | |
| | **ድምር** | **163** | **157** | **96.32** | **41** | **41** | **100** |

### ግብ 30:- በፕላን የተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት 1,000 አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ እና በስታንዳርድና ዲዛይን እንዲለሙ ማድረግ፣

- ✓ በ229 ከተሞች በፕላን የተመላከቱ 1000 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ በ228 ከተሞች 2,026 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ለ1,349 (70.22%) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት ተችሏል፡፡

### ሰንጠረዥ 35:- በፕላን ለተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሰጡ ዞኖችና ከተሞች

| ተ.ቁ | ዞን/ከተማ | አረንጓዴ ቦታዎችን የለዩ ከተሞች | | | የተለዩ አረንጓዴ ቦታዎች ብዛት በቁጥር | | | ከተለዩት ውስጥ ካርታ የተሰራላቸው ቦታዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | ደ/ብርሀን | 5 | 5 | 100 | 10 | 25 | 250 | 25 | 33 | 132 |
| 2 | ደ/ወሎ | 25 | 25 | 100 | 80 | 81 | 101.25 | 80 | 81 | 101.25 |
| 3 | ባ/ዳር | 6 | 6 | 100 | 20 | 54 | 270 | 54 | 54 | 100 |
| 4 | ደብረታቦር | 3 | 3 | 100 | 15 | 15 | 100 | 15 | 15 | 100 |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | 23 | 27 | 117.39 | 100 | 107 | 107 | 101 | 101 | 100 |
| 6 | ዋግኽምራ | 7 | 18 | 257.14 | 50 | 63 | 126 | 63 | 54 | 85.71 |
| 7 | ደ/ጎንደር | 19 | 19 | 100 | 80 | 75 | 93.75 | 65 | 58 | 89.23 |

| ተ.ቁ | ዞን/ከተማ | አረንጓዴ ቦታዎችን የለዩ ከተሞች | | | የተለዩ አረንጓዴ ቦታዎች ብዛት በቁጥር | | | ከተለዩት ውስጥ ካርታ የተሰራላቸው ቦታዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 8 | ጎንደር | 6 | 6 | 100 | 20 | 25 | 125 | 25 | 21 | 84 |
| 9 | አዊ | 10 | 10 | 100 | 65 | 142 | 218.46 | 56 | 58 | 103.57 |
| 10 | ሰ/ጎንደር | 7 | 6 | 85.71 | 50 | 88 | 176 | 88 | 77 | 87.5 |
| 11 | ሰ/ሸዋ | 28 | 29 | 103.57 | 90 | 203 | 225.56 | 203 | 155 | 76.35 |
| 12 | ምስ/ጎጃም | 20 | 15 | 75 | 70 | 694 | 991.43 | 694 | 525 | 75.65 |
| 13 | ኦሮሞ | 6 | 3 | 50 | 50 | 19 | 38 | 19 | 19 | 100 |
| 14 | ወልዲያ | 3 | 3 | 100 | 20 | 46 | 230 | 46 | 19 | 41.30 |
| 15 | ምዕ/ጎንደር | 8 | 9 | 112.5 | 50 | 50 | 100 | 50 | 20 | 40 |
| 16 | ደሴ | 5 | 5 | 100 | 20 | 5 | 25 | 5 | 1 | 20 |
| 17 | ሰ/ወሎ | 16 | 35 | 218.75 | 50 | 213 | 426 | 211 | 43 | 20.38 |
| 18 | ማዕ/ጎንደር | 24 | 4 | 16.67 | 100 | 121 | 121 | 121 | 15 | 12.40 |
| 19 | ደ/ማርቆስ | 4 | | | 30 | | | | | |
| 20 | ኮምቦልቻ | 4 | | | 30 | | | | | |
| | **ድምር** | **229** | **228** | **99.56** | **1,000** | **2,026** | **202.6** | **1,921** | **1,349** | **70.22** |

- ✓ በ59 ከተሞችና ክ/ከተሞች የመንገድ ዳርቻ፣ አካፋይና አደባባዬች እንዲሁም የውሃ አካላትና ዳርቻ ቦታዎች ውበት በሚያጐናጽፍ መልኩ በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ ለማድረግ ታቅዶ በ94 ከተሞች (ምዕ/ጐጃም 9፣ ማዕ/ጎንደር 7፣ ደ/ወሎ 10፣ ሰ/ወሎ 8፣ ምስ/ጐጃም 2፣ ሰ/ጐንደር 4፣ ኦሮሞ 2፣ ደ/ጎንደር 4፣ ሰ/ሸዋ 15፣ ዋግኽምራ 2፣ ምዕ/ጐንደር 5፣ ደ/ታቦር 3፣ ጎንደር 6፣ ደ/ብርሀን 5፣ ደሴ 5፣ ኮምቦልቻ 1 እና ባህርዳር 6 ክ/ከተሞች) ለማልማት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ፡-

- ➢ የአረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ሳይትና ካርታ ተዘጋጅቶላቸው እንዲለሙ በማድረግ በኩል በአንጻራዊ ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳጊ የሆነ ለውጥ የታየ ቢሆንም አረንጓዴ ቦታዎችን (በተለይም የውሃ አካላትና ዳርቻ ቦታዎች እና ዘላቂ ማረፊያዎችን) በማልማትና ለመዝናኛና መናፈሻነት በመጠቀምና ውብና ማራኪ በማድረግ ረገድ የግንዛቤና የአፈፃፀም ችግሮች መኖራቸው፣
- ➢ በፕላን የተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች በአብዛኛው በሶስተኛ ወገን የተያዙ (በጊዜዊነት የተሰጡ፣ የግንባታ ቁሳቁስ የተቀመጠባቸው…ወዘተ) በመሆናቸው በታቀደው መሠረት ለማልማት አለመቻሉ፣
- ➢ እንዲሁም ካሳና ትክን በመፍራት ለሌላ አገልግሎት የፕላን ምደባ ለውጥ እየተደረገባቸው መሆኑ፣ ከሶስተኛ ወገን ነፃ የሆኑትም ቢሆን በተገቢው አለመልማታቸው እና በስትራቴጂው ላይ የተቀመጠውን የቦታ አጠቃቀም ምጣኔ (40/30/30) በመተግበር በኩል ችግሮች አሉ፡፡ ይህም የከተሞች መተንፈሻ ሳንባ የሆነውን አረንጓዴ ልማት ከመጉዳቱም በላይ ከተሞች ለተፈጥሮና ለሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭነታቸውን እያፋጠነው ይገኛል፡፡

በመሆኑም ከአረንጓዴ ልማት አኳያ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በከተማው ፕላን የተመላከቱ /የተቀመጡ አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማዘጋጀት፣ በሶስተኛ ወገን የተያዙትን አረንጓዴ ቦታዎች በመለየት ነፃ ማድረግ እና ማልማት፣ የፕላን ጥሰት እንዳይፈፀምባቸው ክትትል ማድረግ፣ የለሙትንም ቢሆን በዘላቂነት እንክብካቤ በማድረግ ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ ማድረግ፣ በአረንጓዴ ልማቱ ባለድርሻና አጋር አካላትን ማሳተፍ እንዲሁም በቂ የአመራር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

## 2.7. የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች

### ግብ 31፡- የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በሆኑ 17 ከተሞች ለምግብ ዋስትና ተጋላጭ የሆኑ 83,752 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ፣

በከተሞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙና ለምግብ እጥረት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዲቻል የኢፌዲሪ መንግስት የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት በክልላችን ባሉ 17 ከተሞች (16 አዲስና

በነባሩ በደሴ ከተማ) በኑሮ ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች የሆኑና የመስራት አቅም ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በህብረተሰብ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ማህበራዊ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች፣ በከተማ ግብርና እና በሌሎችም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች በማሳተፍና የስራ እድል በመፍጠር ገቢ እንዲያገኙና ከሚያገኙት ገቢም ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ ለማስቻል እየተሰራ ይገኛል፡፡

- ✓ በምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ምንነት፣ የተጠቃሚዎች ምልመላ፣ ቅሬታ አቀራረብ፣ የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ፣ ወዘተ ላይ ለ336,000 ተጠቃሚዎች፣ ሕ/ሰብ፣ ባለድርሻ አካላት፣ አመራር እና ባለሙያ ወዘተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለመስራት ታቅዶ ለ350,035 ለከተማና ለቀበሌ አመራር፣ ለባድርሻ አካላትና ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡

### ሰንጠረዥ 36:- በምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ ዙሪያ የተፈጠረ ግንዛቤ የከተሞች አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ከተማ | ለከተማ አስተዳደር አመራር | | | ለክፍለ ከተማና ቀበሌ አመራር | | | ለባለድርሻ አካላት | | | ለከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ጎንደር | 12 | 3 | 15 | 33 | 16 | 49 | 36 | 36 | 72 | 10,480 | 12,363 | 22,843 | 22,979 |
| 2 | ባህርዳር | 134 | 53 | 187 | 42 | 36 | 78 | 114 | 91 | 205 | 11,582 | 13,978 | 25,560 | 26,030 |
| 3 | ደ/ብርሃን | 22 | 11 | 33 | 21 | 10 | 31 | 21 | 23 | 44 | 7,854 | 3,411 | 11,265 | 11,373 |
| 4 | ደ/ማርቆስ | 79 | 34 | 113 | 21 | 21 | 42 | 104 | 132 | 236 | 67,298 | 106,727 | 174,025 | 174,416 |
| 5 | ደ/ታቦር | 28 | 8 | 36 | 33 | 9 | 42 | 20 | 15 | 35 | 3,300 | 5,271 | 8,571 | 8,684 |
| 6 | ኮምቦልቻ | 15 | 3 | 18 | 26 | 11 | 37 | 17 | 15 | 32 | 31,300 | 44,670 | 75,970 | 76,057 |
| 7 | ወልዲያ | 18 | 4 | 22 | 12 | 4 | 16 | 10 | 10 | 20 | 6,182 | 4,963 | 11,145 | 11,203 |
| 8 | ደሴ | 46 | 6 | 52 | 53 | 13 | 66 | 102 | 98 | 200 | 7,760 | 11,215 | 18,975 | 19,293 |
| ድምር | | **354** | **122** | **476** | **241** | **120** | **361** | **424** | **420** | **844** | **145,756** | **202,598** | **348,354** | **350,035** |

- ✓ በ17 ከተሞች በ1ኛው ዙር ምልመላ 34,870 ዜጎች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን በ2015 ዓ/ም 48,882 ተጠቃሚዎች በ2ኛ እና 3ኛ ዙር የምልመላ እና ልየታ ስራ ለመስራት ታቅዶ 40,727 (83.31%) ተጠቃሚዎች ተለይተዋል፡፡ በተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ የሚሳተፉ 8,163 የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች ልየታና ምልመላ ስራ ለመስራት ታቅዶ 6,378 (78.13%) ተጠቃሚዎች ተለይተዋል፡፡

### ሰንጠረዥ 37:- በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ ዙር እና በተጨማሪ ፋይናንስ የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች

| ተ.ቁ | የከተማ ስም | የመጀመሪያ ዙር የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች | | | የ2ኛና 3ኛ ዙር የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች | | | የተጨማሪ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች | | | ጠቅላላ ድምር | | | ስራ ሃይል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ጎንደር | 1,660 | 2,742 | 4,402 | 5,066 | 8,142 | 13,208 | 427 | 1,588 | 2,015 | 7,153 | 12,472 | 19,625 | 1,084 | 4,639 | 5,723 |
| 2 | ባህርዳር | 1,247 | 2,058 | 3,305 | 4,065 | 5,850 | 9,915 | 286 | 816 | 1,102 | 5,598 | 8,724 | 14,322 | 765 | 3,634 | 4,399 |
| 3 | ደ/ብርሃን | 570 | 817 | 1,387 | 1,665 | 2,496 | 4,161 | 141 | 309 | 450 | 2,376 | 3,622 | 5,998 | 500 | 1,294 | 1,794 |
| 4 | ደ/ማርቆስ | 497 | 832 | 1,329 | 1,315 | 2,672 | 3,987 | 199 | 338 | 537 | 2,011 | 3,842 | 5,853 | 530 | 1,267 | 1,797 |
| 5 | ደሴ | 2,193 | 2,574 | 4,767 | | | | 415 | 493 | 908 | 2,608 | 3,067 | 5,675 | 799 | 943 | 1,742 |
| 6 | ኮምቦልቻ | 557 | 690 | 1,247 | 1,310 | 2,432 | 3,742 | 205 | 382 | 587 | 2,072 | 3,504 | 5,576 | 668 | 929 | 1,597 |
| 7 | ደ/ታቦር | 480 | 762 | 1,182 | 1,468 | 2,087 | 3,555 | 145 | 230 | 375 | 2,093 | 3,079 | 5,112 | 672 | 1,016 | 1,688 |
| 8 | ወልዲያ | 965 | 1,071 | 1,766 | 734 | 1,425 | 2,159 | 147 | 257 | 404 | 1,846 | 2,753 | 4,329 | 274 | 1,028 | 1,302 |
| 11 | ሞጣ | 828 | 1,399 | 2,227 | | | | | | | 828 | 1,399 | 2,227 | 200 | 550 | 750 |
| 10 | ፍ/ሰላም | 883 | 1,321 | 2,204 | | | | | | | 883 | 1,321 | 2,204 | 211 | 470 | 681 |
| 12 | ሰቆጣ | 746 | 1,155 | 1,901 | | | | | | | 746 | 1,155 | 1,901 | 149 | 413 | 562 |
| 11 | እንጂባራ | 683 | 1,109 | 1,792 | | | | | | | 683 | 1,109 | 1,792 | 155 | 412 | 567 |
| 13 | ደባርቅ | 678 | 1,094 | 1,772 | | | | | | | 678 | 1,094 | 1,772 | 107 | 386 | 493 |
| 14 | ከሚሴ | 704 | 948 | 1,652 | | | | | | | 704 | 948 | 1,652 | 167 | 286 | 453 |
| 15 | ላሊይበላ | 686 | 791 | 1,477 | | | | | | | 686 | 791 | 1,477 | 169 | 241 | 410 |
| 16 | ሸዋሮቢት | 647 | 848 | 1,495 | | | | | | | 647 | 848 | 1,495 | 164 | 347 | 511 |
| 17 | ገንዳውሃ | 399 | 564 | 965 | | | | | | | 399 | 564 | 965 | 39 | 250 | 289 |
| | ድምር | **14,423** | **20,775** | **34,870** | **15,623** | **25,104** | **40,727** | **1,965** | **4,413** | **6,378** | **32,011** | **50,292** | **81,975** | **6,653** | **18,105** | **24,758** |

### የአካባቢ ልማት ስራዎች:-

- በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ላይ 11,849 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 36,483 (43.56%) ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 14,033 (118.43%) የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 35,081 (96.15%) የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በከተሞች ውበትና አረጓዴ ልማት ስራዎች ላይ 6,071 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 18,693 (22.32%) ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 4,820 (79.39%) የቤተሰብ ተጠሪዎች በማሳተፍ 12,409 (66.38%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ 4,472 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 13,769 (16.44%) ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6,164 (137.83%) የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 15,410 (111.91%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በማህበራዊ የመሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች ላይ 2,410 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 7,420 (8.86%) ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2,230 (92.53%) የቤተሰብ ተጠሪዎች በማሳተፍ 5,574 (75.12%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በከተማ ግብርና ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር 2,399 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 7,387 (8.82%) ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,574 (232.34%) የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 13,934 (188.62%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- በአካባቢ ልማት ስራዎች ተሳታፊ ለሆኑ 83,752 የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ብር 388,546,560 ወርሃዊ ክፍያ እንዲተላለፍላቸው ለማድረግ ታቅዶ በዚህ ወር ይተላለፋል ተብሎ ከተያዘው ዕቅድ ብር 219,704,4000 ውስጥ 216,305,742 (98.48 %) በወቅቱ ክፍያ እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡
- በጠቅላላው በ17 ከተሞች የመስራት አቅም ያላቸው እና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 27,200 ሰሪ ሀይሎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች በማሳተፍ 83,752 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በመጀመሪያው ዙር በተካተቱ 17 ከተሞች እና በ2ኛ እና 3ኛ ዙር እንዲሁም በተጨማሪ ፋይናንስ በተካተቱ 8 ከተሞች 24,758 (91.02%) (ወንድ 6,653 ሴት 18,105) ሰሪ ኃይሎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች በማሳተፍ 81,975 (97.87%) (ወንድ 32,011 ሴት 50,292) ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## ግብ 32፡- ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 27,200 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ ማድረግ፣

### የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ሥራዎች፡-

- በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም የሚታቀፉ 27,200 ዜጎች እንዲለዩ ለማድረግ ታቅዶ 25,643 (94.28%) ሰሪ ሃይሎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ ተደርጓል፡፡
- በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ለማግኘት የተለዩ ተጠቃሚዎች 77,709,312 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 73,136,310 ብር (94.11%) እንዲቆጥቡ ተደርጓል፡፡
- በቁጠባ ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎ 50 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ እስከዚህ ወር አፈጻጸም 59.79% ነው፡፡
- በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም የሚታቀፉ 27,200 ዜጎች የድጋፍና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 2,890 ሴት 7,852 ድምር 10,742 ተጠቃሚዎች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙ (39.49%) ነው፡፡
- በመጀመሪያው ምዕራፍ 3ኛ ዙር 1,858 ተጠቃሚዎች ወርሃዊ የምክርና ድጋፍ እና ስልጠና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 606 ሴት 887 ድምር 1,493 (80.4%) ተጠቃሚዎች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች ተሰማርተው በዘላቂነት ኑሯቸውን እንዲደጉሙ ከማድረግ አኳያ 10,720 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በከተማ በግብርና እና በሌሎች ስራዎች በማሳተፍ ብር 47,016,398.00 እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

- ሌላው በሁሉም ከተሞች መረዳጃ እና እቁብ አደረጃጀት የተፈጠረ ሲሆን በዚህ አደረጃጀት እስካሁን ብር 9,018,500.00 ገንዘብ በመሰብሰብ መቆጠብና ለችግራቸው የመጠቀም ባህል ዳብሯል፡፡

ይሁን እንጅ በዋናነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም፡-

  - እጅግ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችን፣
  - የጎዳና ተዳዳሪዎችን፣
  - ሴተኛ አዳሪዎችን፣
  - መስራት እየቻሉ ወደ ስራ ያልገቡ ስራ ፈላጊ ዜጎችን፣
  - አካል ጉዳተኞችን፣
  - የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚዎች፣
  - ጠዋሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያንና ህጻናትን
  - በአጠቃላይ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዜጎችን በአግባቡ በመለየትና በጥራት በመመልመል በኩል ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

- ሌላው ከአካባቢ ልማት ስራዎች አኳያ በተሽከርካሪ እጥረት ምክንያት በሁሉም ከተሞች በአካባቢ ልማት ስራው የተሰበሰበን ቆሻሻ በወቅቱ በማንሳት እና ለከተማ ግብርና እና ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች የሚውል ከ3ኛ ወገን ነፃ የሆነ የከተማ ቦታ በማቅረብ በኩል ችግሮች ተስተውለዋል፡፡
- በመሆኑም ከምልመላና መረጣ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን አሰራሩን ተከትሎ በወቅቱ እየገመገሙ ማስተካከል ይገባል፡፡
- የቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎችንም ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ማሟላት ያስፈልጋል፡፡

## 2.8. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ ስራዎች

**ግብ 33፡- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ 6,100 ባለሙያዎች በተሰማሩበት ዘርፍ የተሟላ ዕውቀት እና ክህሎት ያላቸው መሆኑን በሙያ ብቃት ምዘና ማድረግ፣**

የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫዎት እንዲቻል የሚገነቡ ግንባታዎች የህዝቡን ደህንነትና ጤንነት ያገናዘቡ እንዲሆኑና ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች አካታች መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጥራት ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማስቻል የሬጉላቶሪ እና በዘርፉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ከቢሮው ከኮንስትራክሽን አንጻር የሚጠበቁ ቁልፍ ሥራዎች ናቸው፡፡

ሌላው የዚህ ዘርፍ ዋና ተልዕኮ የክልሉን ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር በማሳደግ ተወዳደሪ ስራ ተቋራጮችን መፍጠር፣ የሚገነቡ ግንባታዎች የአገሪቱን ህንፃ ኮድና ስታንዳርዶች ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡና በዘርፉ የሚስተዋለውን ሌብነት ለመታገል የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡

- ✓ በመሆኑም የኮንስትራክሽን ዘርፉን የሰው ሀይል ልማት በስልጠና አመለካከቱንና ክህሎቱን በማሳደግ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅሙን ለማጎልበት እንዲቻል ከምዘና ማዕከላት ጋር በቅንጅት በመስራት 46 አዲስ መሪ መዛኞችን ለማፍራት ታቅዶ 41 (89.13%) ማፍራት ተችሏል፡፡
- ✓ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ለ6,100 አነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ምዝገባ በማድረግ ለመመዘን ታቅዶ 5,435 (89.09%) ባለሙያዎችን በመመዝገብ ከተመዘገቡት ውስጥ 3,160 (58.14%) ባለሙያዎች ተመዝነው 1,815 (57.43%) ምዘናውን ያለፉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 188 አነስተኛ (10.35%) መለስተኛ ባለሙያዎች ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲያድጉ ናቸው፡፡
- ✓ ምዘናውን ያላለፉ 1,345 አነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ከአሰሪዎቻቸው ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የክህሎት መሟያ የኩባንያ እና ትብብር ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 439 (32.63%) ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

### ግብ 34፡- በክልሉ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚታየዉን የአቅም ክፍተት በመሙላት 350 ተቋራጮች እና 84 አማካሪዎች አገር አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- ✓ ለ350 ሥራ ተቋራጮችና ለ84 አማካሪ ድርጅቶች በሰው ሃይል ማብቃት፣ በግብዓት፣ በአደረጃጀትና በክህሎት የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ186 (53.14%) ሥራ ተቋራጮችና ለ68 (80.95%) አማካሪ ድርጅቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ✓ 10 ስራ ተቋራጮች እና 3 የአማካሪ ድርጅቶች ዘመናዊ የኮንስትራክሽን አመራርና አደረጃጀት (ISO) እንዲኖራቸው እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ለISO የሚያበቃ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና በስታንዳርዱ መሰረት በመለየት የተለዩትን ለማብቃት ታቅዶ ለ8 (80%) ስራ ተቋራጮች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### ግብ 35፡- የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ ስርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ የዘርፉ ተዋናዮች በግብዓት፣ በአደረጃጀት እና በክህሎት ብቃት በማረጋገጥ ምዝገባ ማድረግ፣

- ✓ የክልሉን ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር ከማሳደግ እና ተወዳዳሪ ስራ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን ከመፍጠር አንፃር 4,186 (አዲስ 2,000፣ እድሳት 2,013፣ እድገት 173) ሥራ ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ ለመመዝገብ ታቅዶ ለ1,688 (40.32%) ሥራ ተቋራጮች (አዲስ 502፣ እድሳት 1,127፣ እድገት 59) ምዝገባ ተደርጓል፡፡
- ✓ ለ403 (አዲስ 100፣ እድሳት 300 እድገት 3) አማካሪዎች ብቃት በማረጋገጥ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ 217 (52.92%) አማካሪዎች (አዲስ 62፣ እድሳት 99፣ እድገት 56) ምዝገባ ተደርጓል፡፡
- ✓ ሌላው ለ3,000 ኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ ለ3,979 (ከ100% በላይ) ባለሙያዎች ምዝገባ ተደርጓል፡፡
- ✓ ለ300 ሥራ ተቋራጮች እና ለ100 አማካሪዎች በመስከ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ለማድረግ ታቅዶ ለ215 (71.66%) ሥራ ተቋራጮች እና ለ128 (ከ100% በላይ) አማካሪዎች የመስክ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ተደርጓል፡፡

### ግብ 36፦- በክልሉ የሚከናወኑ ሁሉም ግንባታዎች ከቅድመ ግንባታ እስከ ድህረ ግንባታ ድረስ በህንፃ አዋጁ ኮድና ስታንዳርዶች መሰረት እንዲከናወኑ ማድረግ፣

#### ሰንጠረዥ 38፡- የተሰጠው የግንባታ ፈቃድና የግንባታ ቁጥጥር የዞኖችና ከተሞች አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዞን | የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ | | | የተደረገ ግንባታ ቁጥጥር | | | የመንግስት ግንባታዎች ቁጥጥር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክከንውን | አፈፃፀምበ% | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀምበ% | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀምበ% |
| 1 | ምስ/ጎጃም | 3,300 | 3,323 | 100.70 | 2,240 | 2,400 | 107.14 | 20 | 38 | 190 |
| 2 | ምዕ/ጎጃም | 3,900 | 7,098 | 182 | 2,700 | 5,038 | 186.59 | 20 | 18 | 90 |
| 3 | አዊ ዞን | 2,500 | 2,193 | 87.72 | 1,710 | 2,547 | 148.95 | 20 | | |
| 4 | ደ/ጎንደር | 3,150 | 5,479 | 173.94 | 2,150 | 4,649 | 216.23 | 20 | 22 | 110 |
| 5 | ማዕ/ጎንደር | 3,400 | 3,170 | 93.24 | 2,320 | 2,450 | 105.60 | 20 | 20 | 100 |
| 6 | ምዕ/ጎንደር | 1,900 | 968 | 50.95 | 1,170 | 418 | 35.73 | 20 | 22 | 110 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 1,200 | 1115 | 92.92 | 900 | 899 | 99.89 | 20 | 5 | 25 |
| 8 | ዋግኽምራ | 1,400 | 1265 | 90.36 | 980 | 757 | 77.24 | 20 | 19 | 95 |
| 9 | ሰ/ወሎ | 2,750 | 5,498 | 199.93 | 1,960 | 6,188 | 315.71 | 20 | | |
| 10 | ደ/ወሎ | 4,450 | 3,995 | 89.78 | 2,930 | 3,345 | 114.16 | 20 | 134 | 670 |
| 11 | ኦሮሞ | 1,600 | 1,615 | 100.94 | 1,110 | 838 | 75.50 | 20 | 11 | 55 |
| 12 | ሰ/ሸዋ | 4,250 | 6,914 | 162.68 | 2,900 | 8,069 | 278.24 | 20 | 5 | 25 |
| 13 | ባህርዳር | 8,250 | 4,129 | 50.05 | 7,160 | 3,729 | 52.08 | 20 | | |
| 14 | ደሴ | 3,000 | 395 | 13.17 | 2,700 | 587 | 21.74 | 20 | 6 | 30 |
| 15 | ጎንደር | 3,000 | 1,823 | 60.77 | 2,700 | 1,530 | 56.67 | 20 | | |
| 16 | ደ/ማርቆስ | 1,500 | 4,331 | 288.73 | 1,300 | 1,366 | 105.08 | 20 | | |
| 17 | ደ/ብርሃን | 1,500 | 3,262 | 217.47 | 1,300 | 2,313 | 177.92 | 20 | 13 | 65 |
| 18 | ኮምቦልቻ | 1,500 | 1375 | 91.67 | 1,300 | 3076 | 236.62 | 20 | 17 | 85 |
| 19 | ደ/ታቦር | 1,000 | 558 | 55.80 | 800 | 324 | 40.50 | 20 | | |
| 20 | ወልዲያ | 1,000 | 815 | 81.50 | 800 | 816 | 102 | 20 | 2 | 10 |
| 21 | ቢሮ | | | | | | | 100 | 72 | 72 |
| | **ድምር** | **54,550** | **59,321** | **108.75** | **41,130** | **51,339** | **124.82** | **500** | **404** | **80.8** |

- ✓ የህንጻ አዋጅ አደረጃጀት የተፈጠረባቸው 206 ከተሞች፣ ክፍለ ከተሞች እና መሪ ማዘጋጃ ቤቶች ለ54,350 ፕሮጀክቶች የፕላን ስምምነትና የግንባታ ፈቃድ በመስጠት ለ41,120 ፕሮጀክቶች የግንባታ ወቅት ቁጥጥር በማድረግ አዋጁን መሰረት አድርገው እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ ለ70,901 (ከ100% በላይ) የፕላን ስምምነት እና ለ59,321 (ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች የግንባታ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ለ51,112 (ከ100% በላይ) ግንባታዎች ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በነዚህ ከተሞች ተገንብተው ለተጠናቀቁ 60 ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ126 (ከ100% በላይ) ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡
- ✓ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ፣ የህግና አሠራር ሥርዓት ከማበልፀግ አኳያ የህንጻ አዋጅ አደረጃጀት በተቋቋመባቸው በ206 ከተሞች፣ ክ/ከተሞችና መሪ ማዘጋጃ ቤቶች በተፈጠረው አደረጃጀት መሰረት የሰው ሃይል አሟልተው ወደ ስራ እንዲገቡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ280 (ከ100% በላይ) ከተሞች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**ግብ 37፡- በክልሉ የሚከናወኑ የመንግስት ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና ጥራት እንዲከናወኑ ቁጥጥር ማድረግ፣**

- ✓ በክልሉ በመንግስት በጀት ለሚሰሩ 50 ሕንፃዎች የውለታና የዲዛይን ዝግጅት ወቅት ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ118 ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ✓ በክልሉ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወቅታዊ የግንባታ ዋጋ በየሩብ ዓመቱ 52 የዋጋ ጥናት ሰነድ ተጠንቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ ለማድረግ ታቅዶ 48 ጊዜ ተጠንቷል፡፡
- ✓ በሌሎች የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የተዘጋጁ 80 የጨረታ ዶክመንቶችን በግንባታ በህጉ መሰረት መሆኑን በምርመራ ለማረጋገጥ ታቅዶ 228 (ከ100% በላይ)፣ 150 የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄዎችን መርምሮ ለማፅደቅ ታቅዶ 155 (103%)፣ 60 የአማካሪ ክፍያ መርምሮ ለማፅደቅ ታቅዶ 79 (ከ100% በላይ)፣ በመንግስት ተቋማት ለሚከናወኑ100 የግንባታ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ስራ (varation) ለመመርመር ታቅዶ ለ95 (95%) ምርመራ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ለሚያስገነቡት ግንባታ የዲዛይን ዝግጅት እና አማካሪ ለመቅጠር የሚያስችል 35 ዝክረ ተግባር ለማዘጋጀት ታቅዶ 48 (ከ100% በላይ) ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ በመንግስት በጀት ለሚገነቡ 60 ግንባታዎች ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ በሚደረግበት ወቅት ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ71 (ከ100% በላይ) የመንግስት ግንባታዎች የመጨረሻ ርክክብ ወቅት ሙያ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በመንግስት በጀት በሚገነቡ 500 ግንባታዎች ከጊዜ፣ ከበጀትና ከጥራት አኳያ በመስክ በመገኘት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 404 የቁጥጥር ስራ የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙም 81% ተከናውኗል፡፡
- ✓ በቤቶች ልማት ባለቤትነት ለሚገነባው 200 የአመራር መኖሪያ ቤት ግንባታ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

- ✓ የባህር ዳር ስቴዲዮም የዓለም አቀፍ ስታንዳረድን ያሟላ ሆኖ እንዲገነባ ለማድረግ በተቋራጩ በኩል የተጠየቀውን 3 ቢሊየን የገንዘብ መጠን በአግባቡ የነጠላ ዋጋ በማጥናት እና አላስፈላጊ ስራዎች እንዲወጡ ማድረግ 1.2 ቢሊየን ብር እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በክልሉ ውስጥ በግንባታ ዋጋ ንረት ምክንያት ተጓተው የነበሩ ከ700 በላይ ፕሮጀክቶች የዋጋ ንረት ማካካሻ (Price Escalation) ጥናት በማጥናትና በሚመለከታቸው አካላት በማስወሰን ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ የአማራ ልማት ማህበር (አልማ) የዋንዛየ ሎጅ እና የጢስ አባሊማ የመጠጥ ውሃ ፋብሪካ ዲዛይን በቢሮው በኩል ተመርምሮ እንዲሠጠው ጥያቄ አቅርቦ በህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሰረት የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚፈፀም ቢሆንም አልማ በክልሉ ማህበራዊ የልማት ችግርን ለመፍታት የተቋቋመ መሆኑ ክፍያ ሳይፈፅም ዲዛይኑ ተመርምሮ ተሰጥቷል፡፡
- ✓ በክልሉ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የስሚንቶ ፍላጎታቸው በቢሯችን በኩል እየተረጋገጠ እንዲሄድ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከ200 ሚሊዮን በላይ ውለታ የተያዙትን የመንግስት ፕሮጀክቶች የስራ መጠን እና አመታዊ እና ወርሃዊ የስሚንቶ ፍላጎት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ✓ በዚህም ለ18 ፕሮጀክቶች የስራ ዝርዝር ከስሚንቶ ፍላጎታቸው ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ ለ2015 በጀት ዓመት የሚያስፈልጋቸውን 417,841 ኩንታል የስሚንቶ ፍላጎት ተረጋግጦ ለንግድ ቢሮ ተልኳል፡፡

ይሁን እንጅ የኮንስትራክሽን ዘርፉ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ እየተወጣ ባለመሆኑ፡-

- ➢ ምክንያት የመንግስት ግንባታዎች /ፕሮጀክቶች መጓተት እና የጥራት ችግር ይስተዋላል፡፡
- ➢ ይህን ችግር ለመፍታት የሚደረጉ የቁጥጥር ሥራዎችና የሚወሰዱ የማስተካከያ ርምጃዎችም ጠንካራ አይደሉም፡፡
- ➢ በመንግስት በጀት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የግንባታ ዲዛይንና ስራ ዝርዝር ለሚመለከተው የህንፃ ሹም እየቀረበ የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ ወደ ስራ መግባት የሚጠበቅ ቢሆንም ይህን በማድረግ በኩል አሁንም ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡
- ➢ በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ላይ በተለይም በሲሚንቶ፣ በብረት፣ በኤሌክትሪካል እና ሳኒተሪ እቃዎች ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረትና የአቅርቦት እጥረት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን እየጎዳው ያለ ከመሆኑም በላይ ለስራው መቀዛቀዝ እና በስራ እድል ፈጠራው ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ከዚህ ችግር ለመውጣት

- ✓ በግንባታው ዘርፍ የተሰማሩ መለስተኛና አነስተኛ ባለሙያዎችን ባለድርሻና አጋር አካላትን (የግንባታ ፕሮጀክት አሰሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ ተቋራጮችን፣ ባለሙያዎችን፣ ግብዓት አቅራቢዎችን፣ የስልጠና እና ምርምር ተቋማትን ወዘተ) ማስተባበር ተናበው እንዲሰሩ መከታተል፣ መደገፍና ማብቃት ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ ሌላው መፍትሄ በክልሉ የሚገነቡ ግንባታዎች ላይ የጨረታ ሂደቱን ማስተካከል፣
- ✓ በቢሮው እና በዞኖች ያሉ ፈፃሚዎችን አቅም መገንባት እና ጠንካራ የቁጥጥር ስራ እንዲሰሩ ማስቻል፣
- ✓ የሕንፃ አዋጅ ደንብና መመሪያን በማይፈፅሙ እና በማያስፈፅሙ ተቋማት እና ፈፃሚዎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ
- ✓ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቶች በሚሰሩት ዲዛይን እና የስራ ዝርዝር ላይ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ለግንባታ መጓተት መንስኤ በመሆናቸው በሰሩት ስራ ልክ የሚጠየቁበት አግባብ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

### ግብ 39፡- ከምርምር ተቋማትጋር በመቀናጀት 1 አዲስ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጅ ጥናትና ምርምር በማካሄድ አዋጭነቱ ተረጋግጦ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፣

- ✓ ከተለያዩ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎችና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች 1 አዲስ ወጪ ቆጣቢና የተሻለ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጅ በመቅዳት እና አዋጭነቱን በጥናትና ምርምር በማረጋገጥ ለተጠቃሚ እንዲተላለፍ ለማድረግ ታቅዶ 1 የግንባታ ቴክኖሎጅ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡
- ✓ በክልሉ 250 ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የግንባታ ግብዓት መገኛ ቦታዎችን በማፈላለግና ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ካርታና ፕላን እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ ለ40 (16%) የግንባታ ግብዓት መገኛ ቦታዎች ካርታና ፕላን ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡
- ✓ በክልሉ 60 ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የግንባታ ግብዓት መገኛ ቦታዎችን በአዲስ በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ታቅዶ 20 (33.33%) የግንባታ ግብዓት መገኛ ቦታዎች ተለይተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

## 2.9. የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈፃፀም

- ✓ በተቋሙ የሚወጡ ዕቅዶች የስርዓተ-ጾታ፣ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የአቅመ- ደካሞችና አረጋዊያን፣ የሰብዓዊ መብትና ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ጉዳዮች እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ...ወዘተ ጉዳዮች በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ በወጡ እቅዶችና ሪፖርቶች እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በዘርፉ በሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች (ሥልጠና እና ትምህርትን) 35% ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በተቋሙ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭትን ለመግታት በተቋሙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ ተጠቃሚ ለሆኑ 2 ግለሰቦች በየወሩ 1,000.00 ብር የገንዘብ ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡
- ✓ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የተሰማራው የሰው ሀይል 100% ደህንነቱ እንዲጠበቅ እና የሚከናወኑ ግንባታዎች ለአረጋዊያንና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ከ50 በላይ ሰራተኞች የተሰማሩባቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በስራ ቦታ ላይ የሠራተኞችን ደህንነት መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያ እንዲያሟሉ ቁጥጥር ተደርጓል፡፡
- ✓ ሌላው ከተሞች የሚሰሩ ሁሉም ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተደራሽ ስለመሆናቸው እና ዲዛይን ሲፀድቅም አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ እያደረገ መፅደቁን ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፡፡
- ✓ የኮንስትራክሽን ላይሰንስ ያወጡ ወጣት ባለሙያወች ወንድ 2,798 ሴት 1,181 ድምር 3,979 ናቸው፡፡

## 2.10. የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች

### ግብ 42፡- በቤቶች ልማት፣ በመሰረተ ልማት፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ በደረቅ ቆሻሻና አረንጓዴ ልማት ዘርፎች ላይ ለ282,981 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር፣

- ✓ በከተማ ፕላን ዝግጅ፣ በቤት ልማት፣ በመሰረተ ልማት፣ በኮንስተራክሽን፣ በደረቅ ቆሻሻ እና በአረንጎዴ ልማት ስታዎች ለ282,981 ዞጎች (151,771 ወንድ እና 131,210 ሴት) ከዚህም ውስጥ 70% ለወጣቶች በጊዜያዊነትና በቆሚነት የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 279,602 (99%) ዜጎች (ለ166,638 ወንዶችና ለ112,964 ሴቶች) ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡
- ✓ በመሰረተ ልማት ስራዎች ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ የወጣቶች ድርሻ 70,073 (75.84%) ሲሆን በኮንስተራክሽን ዘርፍ ከተፈተረው ስራ እድል ውስጥ የወጣቶች ድርሻ 64,983 ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 39፡- ለዜጎች በጊዜያዊነትና በቆሚነት የተፈጠሩ የስራ እድሎች**

| ተ.ቁ | የስራ ዕድል መፍጠሪያ ዘርፍ | የአመቱ እቅድ | | | የአመቱ ክንውን | | | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | በከተሞች ስኬች፣ ፕላን ዝግጅትና ክለሳ ስራዎች | 269 | 268 | 537 | 1,687 | 656 | 2,343 | 436 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | በከተሞች በሚሰሩ የተለያዩ የመንግስትና የግል ግንባታዎች | 61,680 | 41,120 | 102,800 | 64,983 | 45,801 | 110,784 | 108 |
| 3 | በከተሞች በሚሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች (ወጣቶች = 92,400) | 66,000 | 66,000 | 132,000 | 60,863 | 43,755 | 104,618 | 79 |
| 4 | ቤቶች ልማት | 20,000 | 20,000 | 40,000 | 33,774 | 18,501 | 52,275 | 131 |
| 5 | በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ | 722 | 722 | 1,444 | 687 | 830 | 1,517 | 105 |
| 6 | ኮምፖስት በማምረት | 100 | 100 | 200 | | | | |
| 7 | በከተማ ግብርና፣ በተፋሰስ ልማትና በተለያዩ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች | 3,000 | 3,000 | 6,000 | 4,644 | 3,421 | 8,065 | 134 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 151,771 | 131,210 | 282,981 | 166,638 | 112,964 | 279,602 | 99 |

## 2.11. የክትትልና ድጋፍ ስራዎች

- ✓ በዝግጅት ምዕራፍም ይሁን በተግባር ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባሮቻችን በታቀደላቸው አግባብ ግባቸውን እንዲመቱ ጠንካራ፣ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋት ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው፡፡
- ✓ ምንም እንኳን ከወቅታዊ ሁኔታው አንፃር በተፈለገው ወቅትና ጊዜ የሚፈለገውን የሰው ኃይል እያገኙ መወያየት ባይቻልም አሉ የሚባሉ አማራጮችን በመጠቀም ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ተግባሩን ለመምራት ተሞክሯል፡፡
- ✓ በመሆኑም ከክረምት ሥራዎቻችንን አኳያ በዙም ኮንፈረንስ፣ በቴሌ ኮንፈረንስ፣ በዋትስአፕና በቴሌግራም ግሩፕ የዞኖችንና የሪጂዮፖሊታን ከተሞችን አመራሮች በተደጋጋሚ ለማወያየት ጥረት ተደርጓል፡፡
- ✓ ወጥ የሆነ ቼክ ሊስትና የሪፖርት ቢጋር በማዘጋጀት በቴሌግራምና በስልክ የሳምንታዊ ሪፖርት ቅብብሎሽ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡
- ✓ የሚቀርቡ ሳምንታዊ ሪፖርቶችን መነሻ በማድረግ በቢሮው ኮር አመራሮች በመገምገም 3 ጊዜ የተደራጀ ግብረ መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡
- ✓ በአካልም በስልከም የተሞክሮ ልውውጥ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡
- ✓ የቢሮው ኮር አመራሮች ዞኖችንና ሪጂዮፖሊታን ከተሞችን በ4 ምድብ ተከፋፍሎ በመደገፍ፣ በመከታተልና ተሞክሮ በማለዋወጥ ከዝግጅት ምዕራፍ ማጠናቀቂያ እስከ ተግባር ምዕራፍ ማስጀመሪያ የሚስተዋሉ ጉድለቶችን ፈጥኖ ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡
- ✓ በየዘርፉ የማኔጅመንት አባሉም በተዋረድ በስልክ በመደገፍና የተሟላ መረጃ በመቀበል በተቀበለው መረጃ ተመስርቶ ጉድለት ሊሞላ የሚችል አቅጣጫ በማስቀመጥ ታቅደው የወረዱ ተግባራት መፈፀማቸውን በትኩረት ይከታተል፡፡
- ✓ ከሪፖርት ግምገማና ግብረ መልስ ባለፈ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉትን ዞኖችንና ከተሞችን በመለየትና በአካል ወርዶ በመደገፍ (ኮምቦልቻ፣ ደ/ማርቆስ፣ ደ/ብርሃንና ባህርዳር ከተሞችን) በተሟላና በተደራጀ መንገድ ጉድለት ሊሞላ የሚችል ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ✓ በቢሮው ኮር አመራሮች የተመራ የመስክ ድጋፍ ቡድን በ4 ቀጠና በመከፈል የዝግጅት ምዕራፍ እና የተግባር ምዕራፍ አፈፃፀማቸውን ወርዶ ለማየት የድጋፍ ቸክሊስት ተዘጋጅቶ ለ16 ዞን መምሪያዎች፣ ለ19 ከተማ አስተዳደሮች፣ ለ11 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች፣ ለ5 ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች እና ለ5 ታዳጊ ከተሞች ድጋፍ ተደርጎ የክልሉ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ባሉበት በድጋፉ የታዩ ዋና ዋና ጉዳዮች የተገመገሙ ሲሆን ለሁሉም ዞኖችና ከተሞችም የተደራጀ የመስክ ድጋፍ ግብረ-መልስ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- ✓ ከዚህ በተጨማሪም ድንገተኛ ሱፐርቪዥን በማድረግ ሠራተኛው የስራ ሰዓቱን አክብሮ እየሰራ ስለመሆኑ እና የመደበኛ አገልግሎት አሰጣጣቸው ምን እንደሚመስልም ተቋማትን በስራ ሰዓት ተዘዋውሮ ለማየትና ከዚያ ተነስቶ ጉድለት ሊሞላ የሚችል የድጋፍና የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት ተደርጓል፡፡
- ✓ ሌላው በተቋሙ አደረጃጀት፣ አሰራር እና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል፡፡
- ✓ በዚህም መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ✓ የUIIDP እና የምግብ ዋስትና /ሴፍትኔት/ ፕሮጀክቶችን በአካል ጭምር ተገኝቶ በማየትና በማበረታታት የCIP እቅድ ጥራት ባለው መልኩ እንዲታቀድ ከመደረጉም በላይ በጊዜውና በወቅቱ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡
- ✓ በምግብ ዋስትና የታቀፉ 8 ከተሞች ላይ ድጋፍ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየትና በመፈረጅ በፕሮግራሙ እንዲታቀፉ ለማድረግ የሚያስችል ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ✓ በአጠቃላይ የተቋማችን ውጤት የሚለካው በምናደርገው ድጋፍና ክትትል ልክ መሆኑን በመረዳት የተሻለ ጥረት ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

# III. በአፈፃፀም ወቅት የታዩ ጥንካሬዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች

## 3.1 በተግባራት አፈፃፀም ወቅት የታዩ ጥንካሬዎችና መልካም ተሞክሮዎች፣

- ከወቅታዊ ስራዎች አኳያ፡-
  - ለ3ኛ ጊዜ በህዎሃት የሽብር ቡድን የተፈፀሙብንን ጥቃት ከልማት ስራችን ሳንነጠል ወረራውን ለመቀልበስ የተደረገው ርብርብ እና ከዘመቻ ማግስት ነፃ የወጡና የወደሙ ከተሞችን መልሶ ለማቋቋምና ለማደራጀት የተደረገው ርብርብ እንደተቋም አበረታች ውጤት የታየበት መሆኑ፣
  - አመራሩ በጦርነት ውስጥም ሁኖ ከልማቱ ሳይነጠል ሁለቱንም ግንባሮች (የልማትና የህልውና ዘመቻ ግንባሮች) ጎን ለጎን አስተባብሮ በመምራት እንዲሁም ከህዝብ ጋር ተቀራርቦ በመስራት የከተማ ልማት ስራዎችን በርብርብ ለመፈፀም ያደረገው ጥረት ትምህርት የሚወሰድበት መሆኑ፣
- ከዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች አኳያ፡-
  - ከክልል፣ ከፌደራልና ከተቋሙ የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅድ ጋር በማናበብ የ2015 በጀት ዓመት እቅድ በማዘጋጀት እና
  - በየደረጃው የእቅድ ኦረንቴሽንና የስራ ማስጀመሪያ የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት ወኔ ሰንቆ ፈጥኖ ወደ ስራ በመግባት በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራትን በተሻለ ውጤት መፈፀም መቻሉ፣

- ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር፡-
  - በተቋሙ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መልክ ለማስያዝ በጥናት ላይ ተመስርቶ እየገመገሙ መምራት መቻሉ፣
  - የኮር አመራሩ ክፍለ ከተሞችን ተከፋፍሎ ይዞ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ጥረት መደረጉ፣ /ለአብነት ባህርዳር/
  - የከንቲባ ችሎት በማቋቋም ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት ጥረት መደረጉ፣ /ለአብነት ደሴና ኬሚሴ/
  - ስራ አስኪያጅ ባለጉዳይን በጋራ በማወያየት ምንም ወረፋ ሳይጠብቁ በፍጥነት ማስተናገዱ እና የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎችን የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ አቋቁሞ በልተገነባ ግንባታ እስከ 12,7 ሚላየን ብር ለማወራረድ ሲሞከር መታገዱ፣ /ለአብነት ጎንደር/
- ከህብረተሰብ ተሳትፎ አንፃር፡-
  - ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ያሉ ከተምች በህዝብ ተሳትፎ ያለመንግስት በጀት ኮብል ስቶን መንገድ መገንባት መቻሉ፣ /ወፍአርግፍ/
  - ቅን ልቦች በሚል የአካባቢ ባለሀብቶች ላይ የተሻለ ስሜት በመፍጠር ቢሮ ማሳደስ መቻሉ፣ /ደሴ ከተማ/
- ህገ ወጥ ግንባታንና መሬት ወረራን ከመከላከል አንፃር፡-
  - ህገ ወጥ ግንባታ የገነቡትንና የከተማውን ህብረተሰብ በውይይት በማሳመን ያለምንም የፀጥታ ኃይል በማስፈረስ ከተማዋን ከህገ-ወጥ ግንባታ ነፃ ለማድረግ የተሰራው ስራ በመልካም ተሞክሮነት የሚታይ መሆኑ፣ /ደ/ወሎ ዞን ቢስቲማ ከተማ/
- ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አንፃር፡-

- የውጭ መጋራት ታሪፍን በማሻሻል በከተማው ሁሉም አካባቢዎች በተደራጁ ማህበራት ቆሻሻ ወቅቱን ጠብቆ የሚነሳበት ስርዓት መዘርጋቱ እና ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን በማሰባሰብና በመጨፍለቅ/በመፍጩት ለፋብሪካ በግብዓትነት ማቅረብ መቻሉ፤ /ባህርዳር/
- ህ/ሰቡን በንቅናቄ በማሳተፍ የፅዳት ስራ ሳይቆራረጥ በተከታታይነት መፈፀም መቻሉ እና ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም (ከፕላስቲክና ከወረቀት የፋይል አቃፊና የወረቀት ትሪ ማምረት መቻሉ እንዲሁም የባኛጅ ጎማን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል መቻሉ፤ /ጎንደር/
- ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በመበጀት ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በመገንባት ላይ መሆኑ፣ ደ/ወሎ ተንታ ከተማ ዘመናዊ የመንገድ ላይ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶችን ማዘጋጀት መቻሉ፣ /ደ/ብርሃን/

- ከአረንጓዴ ልማት አንፃር
  - በአረጓዴ ልማት ማህበራትን በማደራጀት በተለይም የመንገድ ዳርቻና አካፋዮችን በዘላቂነት እንክብካቤ ማድረግ መቻሉ እንዲሁም ከሚሴ ከተማ የዞኑን አስተዳደር ግቢ ደረጃውን በጠበቀ አግባብ በአረንጓዴ ማልማት መቻሉ፣ /ባህርዳር/
- ከአፈፃፀም ክትትል አኳያ ጠንካራ የድጋፍና ክትትል እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት የተቋሙን አፈፃፀም ለማሻሻል ጥረት መደረጉ የሚሉት በበጀት ዓመቱ የተከናወኑና በተሞክሮነት የሚወሰዱ ተግባራት ናቸው፡፡

## 3.2 በተግባራ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች (ተግዳሮቶች)

- የተቋሙ አደረጃጀት አሁን ያለውን የስራ ጫና ሊሸከም የማይችል መሆኑ፣
- የፕላን አፈፃፀም ኦዲትና የፕላን ዝግጅት ተደረሽነት ችግር መኖር፣
- በየደረጃው ያለው አመራር በዘመቻ ስራ ላይ መጠመዱና በየደረጃው ብልሹ አሰራር በሚፈጥሩ አመራሮችና ባለሙያዎች የተጠያቂነት ስርዓቱ ደካማ መሆኑ፣
- በተቋሙ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የሚፈታ አሰራር አስቀምጦ በመፈፀምና የህብረተሰብን እርካታ በማሳደግ ረገድ አሁንም ችግሮች መኖራቸው፣ እንዲሁም በአመለካከት፣ በአቅምና በግል ፍላጎት ምክንያት ተገልጋይን ማጉላላት፣
- በቴክኖሎጅ አለመታገዝ /አሰራርን የማዘመን ችግር፣ የቅንጅታዊ አሰራር ችግር፣ የመረጃ ልውውጥ ስርዓታችን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ከመረጃ ጥራት አንፃር ችግር መኖሩ፣
  - ለአብነትም የተገነቡ የመሰረተ ልማት መረጃዎችን በአግባቡ በመልቀምና ሪፖርት በማድረግ በኩል ችግር መኖሩ፣
  - የገቢ አሰባሰብ መረጃዎችን ለቅሞ ሪፖርት በማድረግ በኩልም ክፍተት መኖሩ፣ /ከተሞች ከዚህ በላይ የሰበሰቡ ቢሆንም ሪፖርት በማድረግ በኩል ክፍተት መኖሩ፣/
  - እንዲሁም የመሬት መረጃዎችን ለዘመናዊ ካዳስተር በሚሆን አግባብ አደራጅቶ በመያዝ በኩል ክፍተት አለ፣
- በስራ መናበብ ጉድለት ህገ - ወጥ የመሬት ወረራና ግንባታ መበራከትና የከፋ ደረጃ ላይ መሆኑ፣
- በአብዛኛው የክልሉ ትልልቅ ከተሞች በፍላጎቱ ልክ በቂ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ባለመኖሩ የቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም፣
- በኮንስትራክሽን ዘርፉ

- የግንባታዎች /የፕሮጀክቶች መጓተትና የጥራት ችግር መኖር፣
- የሚደረጉ የቁጥጥር ሥራዎችና የሚወሰዱ የማስተካከያ ርምጃዎች ጠንካራ አለመሆን፣
- የግንባታ ግብዓቶች በተለይም የሲሚንቶና የብረት እጥረት መኖር በተጀመሩና ባልተጀመሩ ፕሮጀክቶች ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ያለ መሆኑ፣

### 3.3 የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች

- ✓ የዘርፉን ተቋማዊ የአደረጃጀት እና የአሰራር ለውጥ ዳር ማድረስና ወደ ተቋሙ የገባውን አዲስ አመራር አቅም መገንባት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- ✓ በተቋሙ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ ደረጃ በደረጃ መፍታት፣
- ✓ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ማስጀመር እና እስኪጠናቀቁ በትኩረት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ለዚህ ተግባር የተመደበን በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- ✓ በጦርነቱ የተጎዱና የወደሙ ከተሞችን መልሶ የመገንባት ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- ✓ የከተማ አገልግሎት ገቢን አሟጦ በመሰብሰብ የገቢ አፈፃፀምን ማሻሻል፣
- ✓ በሁሉም የልማት ስራዎቻችን የህብረተሰቡን ተሳትፎና በለቤትነት ማጠናከር፣

## IV. ማጠቃለያ

እንደሚታወቀው ወቅታዊ ሁኔታው ካለው ኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ጋር ተዳምሮ የህዎሃት የሽብር ቡድን ለ3ኛ ጊዜ ጦርነት በመክፈት ትኩረታችን በማዛባት ከልማታችን ለመነጠል ሌትም ቀንም እየሰራ ያለበት መሆኑና አለም አቀፋዊ ሁኔታው ኢ-ተገማች በመሆኑ በዚህ ውስብስብ ወጥመድ ተጠልፈን ላለመውደቅ እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ እንገኛለን፡፡

ይህም ሁኖ ክልላችን ካለበት የህልውና አደጋ ለማውጣት እልህ አስጨራሽ የህልውና ዘመቻ ላይ ሁነንም አንድነታችን አጠናክረን የህልውና ዘመቻውን በአሸናፊነት አጠናቀን ይህን እልህ ያነሳሳው የሞቀ አስተሳሰብ ወደ ልማት በማምጣትና ርብርብ በማድረግ ከላይ የዘረዘርናቸውን በርካታ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት በላቀ ውጤት ማከናወን ችለናል፡፡

በመሆኑም ፈተና ውስጥ ሁነንም ባለፉት ዓመታት ከፈፀምናቸው በላይ በመፈፀም ውጤት ማምጣት የምንችልበት እድል እንዳለ አፈፃፀማችን ያሳያል፡፡

**ማዉጫ** **ገጽ**

**I. መግቢያ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------1**

